# አቤቶ ልጅ እያሱ

## ታሪካዊ ድራማ

በጌታቸው ታረቀኝ

## መግቢያ

ከጥቂት አመታት በፊት ሲያትል /ዋሽንግተን ያገኘኋቸዉ አንድ ታላቅ ኢትዮጵያዊ የታሪክ ምሁር ፤ ‹‹እዉነት ሰስት ፊት አላት›› ብለዉኝ ነበር፡፡ ‹‹የእሱ እዉነት፤ የእሷ እዉነት፤ እና ዋናዋ እዉነት››

በተለያየ ዘመን ወደ ስልጣን የመጡ መሪዎች ስልጣን እና ንብረት ከአንዱ ወስደዉ ወደ ሌላዉ ያስተላልፋሉ፤ የሚያወጡት ህግ አንዱን ሲያከብር ሌላዉን ያከስረዋል፡፡ የከበረዉ የተመቸዉ ‹መልካም ንጉስ የአገር አባት› ይላቸዋል፡፡ የከሰረዉ የተጎዳዉ ደግሞ ‹አገር አጥፊ፤ ክፉ ንጉስ› ይላቸዋል፡፡ ታሪክም እንደ ፀሀፊዎቹ ወገናዊነት በሁለት መልክ ይተረካል፡፡ ዘመን ሲቀያየርም ‹ዉሸት› ተብሎ የነበረዉ ‹ሳይንሳዊ ሀቅ› ይሆናል፡፡ የልጅ እያሱም ታሪክ እንዲሁ ከዘመነኛዉ ናሬቲቭ ጋር አብሮ ይሄዳል፡፡

ልጅ እያሱ ወደ ስልጣን የተጠጉበት ዘመን፡ አገራችን መስቀለኛ መንገድ ላይ የቆመችበት እና ወዴት እንደሚኬድ ክርክር እና ጠብ የነበረበት ዘመን ነበር፡፡ የተቀረዉ አለምም እንደዚሁ የሚንተተትበት፡ የአዉሮፓ ሶሻሊስት ህብረት ትልቅ ደረጃ የደረሰበት፤ የቦልሼቪክ ንቅናቄ የሩስያን ነገስታት የአሳሰበበት፤ ወጣት ቱርኮች ከአቶማን አሮጌ ስርአት በድፍረት የተፋጠጡበት፤ የካርል ማርክስ እና አዳም ስሚዝ ሀሳቦችም ከመቶ አመታት በኋላ የእንዱስትሪ አብዮት ላይ ጫና የፈጠሩበት፤ ጋንዲ በደቡብ አፍሪካ የሚኖሩ ህንዶችን እና ጥቁሮችን ከቅጥ ያጣ፤ ቅጣታዊ ታክስ እና ጭቆና ነፃ ለማድረግ የጀመረዉ አመፃ የህንድን ህዝብ በእንግሊዝ አገዛዝ ላይ ተቃዉሞ ያነሳሳበት፤ አመፃ በየቦታዉ የፈነዳበት፤ በአጠቃላይ ዛሬ የመጀመሪያዉ የአለም ጦርነትም የምንለዉ በየቦታዉ የተቀጣጠለበት ዘመን ነበር፡፡

‹ተራማጅ› ‹ኋላ ቀር› ‹መሀል-ሰፋሪ› የሚባሉ ቅጥያዎች ለመጀመሪያ ጊዜ በሰፊዉ የሚነገሩበት፤ እንግሊዝ ፈረንሳይ እና ጣልያን በአንድ ጎን፤ ጀርመን ኦስትሪያ እና ቱርክ ደግሞ በሌላ በኩል ሆነዉ መሪዎቻችንን የሚንተቱበት ዘመን በመሆኑ፤ በልጅ እያሱ ዘመን ይታይ የነበረዉ አመፃ እና ‹አሮጌ› በተባለዉ የወረሱት ስርአት ላይ የታየዉ ‹ንቀት› እና ‹ስርአተ-አልበኝነት› ከላይ ከተዘረዘሩት የአለም ሁኔታዎች ጋር ሲዳመር ያንን ዘመን እጅግ በጣም የተለየ ያደርገዋል፡፡

መለስ ብለን ከተመለከትነዉም፤ ልጅ እያሱ በነበሩበት ዘመን አፍሪካ በቅኝ ግዛት ስር የነበረችበት ዘመን ይሁን እንጂ፤እንደ ዛሬዉ ክሎኒያሊስቶች በአሰመሩት የኢኮኖሚ እና የተፅእኖ ካርታ መገዳደል ማቆም ከፈለጉ ብዙም አስቸጋሪ የሚሆን አይመስልም ነበር፡፡ ዛሬ በአህጉሩ ከሚታየዉም ስር የሌለዉ ብሄራዊ ማንነት እና በየጊዜዉ ከሚነሳዉ የድንበር ጦርነት፤ የተደጋገሚ መፈንቅለ-መንግስት እና የማያቋርጥ ስደትና ጦርነት ታሪክ አንፃር፤ መላዉ አህጉሩ በትክክል መንገድ ላይ ለመሆኑ አጠራጣሪ ነዉ፡፡ ጉዳዩን እንዲሁ አነሳሁት እንጂ ክሎኒያሊስቶች የሰጡንን ካርታ ትተን እንደገና የመካለል ስራ ይሰራ ቢባልና፤ አንዱ ጎሳ በሌላዉ የሚጨቆንበትን እና የበርካታ ጦርነቶች እና አለመረጋጋት ምንጭ የሆነዉን ቁርሾ ለማጥፋት፤ ሁሉም ማህበረሰብ ራሱን መጠበቅ እና ማስተዳደር በሚችልበት መንገድ እንደገና ክልሉ ይካለል ቢባል፤ የተባባሩት መንግስታት ብቻ ሳይሆን የራሱ የአፍሪካ ማህበርም የሚቀበለዉ ተግባር አይመስለኝም፡፡ ትርፍ የሌለዉ ስራ ነዉ፡፡

በዚያ ዘመን የተባበሩት መንግስታት (ሊግ ኦፍ ኔሽንስ) ገና ዉጥን ላይ የነበረበት ዘመን በመሆኑ በስልጣኔ ስም ‹ከቅኝ ግዛት ጭቆና› ወጥቶ፤ ኋላ ላይ የጋናዉ መሪ ንክሩማ እንዳሉት፤ ወደ ‹የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ጭቆና› የሚያስገባዉ በርም ያልነበረበት

በመሆኑ፤ በዘመኑ የታየዉን ‹ስርአተ-አልበኝነት› ምናልባት በዘመኑ የነበሩ ሰዎች የወደፊቱ አስፈርቷቸዉ እና የተያዘዉ ‹የስልጣኔ ጉዞ› መድረሻ የሌለዉ ባዶ ድካም ከመሆን አልፎ፤ ብጥብጡ እና አለመረጋጋቱ ዘለአለማዊ እንደሚሆን ታይቷቸዉም ሊሆን ይቻላል።

‹ብጥንት በዱሮ ጊዜ የቤት ጣራ በሳር በሰንበሌጥ በመሰራቱ የተነሳ ሀይለኛ ዝናብ ሲጥል ዉሃዉ ዘልቆ እየገባ ቤት ያበላሽ ነበር› ተብሎ በሚነገርበት ጊዜ…‹ምነዉ ጣራዉን በቆርቆሮ ወይ በአስቤስቶስ በሰሩት ኖሮ› ብሎ ማለት፤ ‹ቆርቆሮ አስቤስቶስ› የሚባለዉ በተፈጠረበት ዘመን ያሉትን ተቺዎች የዋህነት ያሳያል እንጂ፤ ጣራዉን በሳር ሰንበሌጥ የሰሩትን ሰዎች የኢንጅነሪንግ ክህሎት አይቀንሰዉም። ለነገሩ ዛሬ አስቤስቶስም የሆድ እቃ የሳምባና የሌላም ካንሰር እንደሚያመጣ ሲረጋገጥ ደግሞ ‹አስደናቂዉ ፈጠራ› ‹አደገኛ መርዝ› ተብሎ ጥቅም ላይ መዋሉም ቀርቷል።

ዘመን ከአለፈ በኋላ በተገኘ እዉቀት ላይ ተመስርቶም ያለፈ ታሪክን ስህተቱን ለመማማሪያነት ከመጠቀም አልፎ፤ ፍርድ ለማሳለፍም መሞከሩ አዳጋች የሚሆነዉም በዚህ የተነሳም ይመስለኛል።

ልጅ እያሱን ‹ጀግና› እና ከዘመናቸዉ የቀደሙ አድርጎ የሚያስብ እንዳለ ሁሉ በተቃራኒዉ መልኩ የሚፈርጃቸዉም እንደሚኖርም መገመት አያዳግትም። በዚህ ሀሳብ ላይ ሁለቱን የሚያስታርቅ ሀሳብ ከመፈለግ ሌላ፤ የአንዱን ወይም የሌላኛዉን ሀሳብ አሸናፊ አድርጎ ማቅረብም አስቸጋሪ ይመስለኛል። ዘመን ሲቀያየር ‹ጀግና› የነበረዉ ‹ባንዳ› ይባላል። ደሞ ሌላ ዘመን መጥቶ ቦታቸዉን እስከሚቀያይረዉ ድረስ።

በታሪክ ስማቸዉ ገንኖ ከሚነገርላቸዉ ጀግኖች ሌላም፤ ሁሉም ሰዉ የየራሱ ጀግና ሊኖረዉም ይችላል።

በ1980 ዓ.ም የአስራ ሁለተኛ ክፍል መልቀቂያ ፈተና ለመፈተን፤ ከሌሎች የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ መምህራን ጋር ኤርትራ፤ ደቀ-መሐሪ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በነበረበት ወቅት ከአገኘኋቸዉ ሰዎች መሀል ዛሬም የማልረሳቸዉ ሁለት ታላላቅ ሰዎችን የማግኘት እድል ገጥሞኝ ነበር። አንደኛዉ የመንግስት ወታደር ሌላዉ የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ነበሩ።

በጊዜዉ የደቀ-መሐሪ ከተማ ከአዲ-ቀይህ በሚተኮስ መድፍ የብዙ ሰዎች ህይወት ይጠፋ ነበር። እኔም ከተማዉ ከገባሁ በሁዋላ ይሄዉ መድፍ በተተኮሰ ቁጥር አብረዉኝ ከነበሩት ጋር ወንበር ስር በተደጋጋሚ እንድሸሸግ ስላደረገኝ፤ ይሄ በየአመቱ በፈተናዉ ሰበብ ወደ ጠረፍ አገር እየሄድኩኝ፤ አገር የማወቅ ፍላጎቴ (አድቬንቸር) ድንገት ጦር ሜዳ መሀል እንደከተተኝ ሳስተዉለዉ፤ ስጋቴ በጣም ከፍ ብሎ ነበር። የመድፍ ተኩስ በተሰማ ቁጥር ሁለተኛዉ፤ ሲያርፍ የሚያሰማዉ ድምፅ እስከሚሰማ ድረስ፤ የተጀመረ ንግግር ሁሉ የሚቋረጥበት፤ ሁሉም ጉምታ ያለዉ ድምፅ፤ የጠላ ጋን/በርሜል ግጣም ሲዘጋ የሚሰማዉ ድምፅ ጭምር፤ በጣም አሳሳቢ የነበረበት ቦታ ነበር። ከተማዉ በሙሉ ፀጉሩን ያጎፈረ፤ ባለ ቁምጣ ታጣቂ የተሞላ ስለነበር፤ በአጠገቤ የሚያልፈዉ ‹ወንበዴ› የሚባለዉ ይሁን አይሁን ለማወቅ ለእኔ አዳጋች ነበር።

ስጋቴን ያስተዋለዉ ፈተናዉን የሚጠብቅልኝ የመንግስት ወታደር ‹አይዞዎት ይቺ ሻቢያ በቅርቡ ትደመሰሳለች፤ አሁን ከወር በላይ እድሜ የላትም› በማለት ያበረታታኝ ነበር። እናም በዚያ መሀል ስለ ታቀደዉ የመጨረሻ ኦፕሬሽን፤ እሱም ከሌሎች ‹ጓዶች› ጋር ‹ግምባር ቀደም› በመሆን መስዋእትነት ለመክፈል ‹መመረጡን› በደስታ ነበር

ያጫወተኝ:: ከጦሩ ፊት ለፊት ሆነዉ በመሄድ በእነኚህ የተመረጡ ወታደሮች ላይ የሚተኮሰዉ ጥይት፡ ወይም የሚፈነዳዉ ፈንጂ ቢገድላቸዉም፤ ለሌሎች ጓዶቻቸዉ ‹ጠላት› የአለበትን ቦታ የሚያሳይ በመሆኑ፤ በቀላሉ በትንሽ ሰዎች ሞት የበርካታ ወታደር ነፍስ ማዳን እንደሚቻል ሲያወራኝ እና ከዚያም ‹ጠላት› ሲደመሰስ ለልጆቹ እና ለዘመዶቹ የገበሬ ማህበሩ መሬታቸዉን እንደሚያርስላቸዉ፤ ልጆቹም ዉጭ አገር ድረስ በነፃ ሄደዉ እንደሚማሩ፤ አገራችንም በሰላም እንደምትኖር ሲያስረዳኝ በፊቱ የሚታየዉ ደስታ ወደ ሞት ሳይሆን ወደ ዉጭ አገር ለትልቅ ስራ የታጨ ወይ ትልቅ ሹመት ያገኘ ነበር የሚመስለዉ::

የትምህርት ቤቱ ርእሰ-መምህር ደግሞ የፈተናዉን ጥያቄ ‹መልስ› ነዉ ያሉትን ወረቀት፤ ከአንዱ የፈተና ክፍል ወደ ሌላዉ በሚስጥር እንደሚያቀባብሉ ለሁለተኛ ጊዜ ሲነገረኝ፤ ርእሰ-መምህሩን በስጡኝ በራሳቸዉ ቢሮ አስጠርቼ፤ ይሄን የፈተና መልስ ማቀባባል ካላቆሙ የፈተናዉን ዉጤት፤ አዲስ አባባ ስደርስ ሪፖርቴን አቅርቤ ዉጤቱ እንደሚሰረዝ እና እሳቸዉም ከስራ እስከ መሰናበት እንደሚደርሱ በእርጋታ ሳስረዳቸዉ፤ ድንገት ፊታዉን ይዘዉ ሰቅስቅ ብለዉ ማልቀስ ጀመሩ::

ጉዳዩ ትንሽ ግራ ቢያጋባኝም ለማረጋጋት ስሞክር ‹እርስዎ አይገባዎትም› አሉኝ:: እሳቸዉ እንደሚሉት፤ በጊዜዉ እነኚህ ወጣቶች ፈተናዉን አልፈዉ ወደ መሀል አገር ካልሄዱ፤ የሚኖራቸዉ ምርጫ ሞት ብቻ ነበር:: በጦርነቱ ሁለቱም ተፋላሚዎች ወጣቶቹን ይፈልጓቸዋል:: በጣም ብዙ ወጣቶች በጦርነቱ እንደ ሞቱ እና እነኚህም ለአመታት በትምህርት ቤት ያሳደጓቸዉ ልጆችም ከሞት ሌላ የሚጠብቃቸዉ ባለመኖሩ፤ እኝህ ግለሰብ ጦርነቱን ማቆም ቢያቅታቸዉ፤ የሞከሩት የነፍስ ማዳን ስራ፤ ከራስ ፍላጎትና ጥቅም በላይ በመሆኑ ሁለቱም ሰዎች ለእኔ ‹ጀግና› የሚለዉን ትርጉም ፍቺ ይሰጡኛል:: ደግነታቸዉ ቸርነታቸዉ እኔ ከማስበዉ በላይ ነዉና::

ስለ ደግነት ከአነሳሁኝ አንድ ጆል ኦስቲን የተባሉ ቄስ ሲያስተምሩ የሰማሁትን ልንገራችሁና መግቢያዬን ላጠናቅቀዉ::

ሁለት ሰዎች በአንድ ሆስፒታል አንድ ክፍል ዉስጥ ተኝተዉ ሳለ፤ አንደኛዉ በሽተኛ መስኮቱ አጠገብ ስለነበር፤ ራቅ ብሎ የተኛዉና መነሳት የማይችለዉ ሌላኛዉ በሽተኛ በመስኮት የሚታየዉን እንዲነግረዉ ይጠይቀዉ ነበር::  ያም መስኮቱ አጠገብ የተኛዉ፤ መነሳት የማይችልዉ  በሽተኛ ‹አሁን ምን ይታይሃል?› ባለዉ ጊዜ ሁሉ..‹ዛሬ ደግሞ ሰማዩ የተለየ ነዉ:: ጉሙ ንጣቱ አቀማመጡ የሚጨበጥ ይመስላል:: ዛሬ ደግሞ ህፃናት ከትምህር ቤት ሲወጡ ነዉ መሰል ሲሯሯጡ ደስ ይላሉ›...ብዙ ሰዎች እየሮጡ ይታየኛል...ከኳስ ሜዳ ሲወጡ ነዉ መሰለኝ?...ዛሬ ደሞ ሰልፍ አለ መሰለኝ ሙዚቀኞቹ በሰልፍ ሲያልፉ ልብሳቸዉ ቀለሙ ደስ ይላል›...ይለዋል:: ‹የከተማዉ መብራት በርቀት ስታየዉ ከጨረቃዋ ፊት የተበተነ ከዋክብት ይመስልሃል...›› በማለት በተጠየቀ ጊዜ ሁሉ የሚታየዉን መነሳት ለማይችለዉ በሽተኛ ይነግረዋል::

ይሄዉ ያየዉን የሚነግረዉ በሽተኛ ሲታክም ቆይቶ በመጨረሻ ሲሞት ያ የቀረዉ በሽተኛ፤ በዉጭ የሚታየዉን የሚነግረዉ ሰዉ ባለመኖሩ፤ ነርሶቹን ወደ መስኮቱ አጠገብ ወደ አለዉ፤ ሟቹ የነበረበት አልጋ ላይ እንዲቀይሩት ይጠይቃል:: ነርሶቹም ተጋግዘዉ ከአልጋዉ አንስተዉ ከአስኙት በሁዋላ በመስኮት ዞሮ ቢመለከት ከፊት ለፊቱ ከተጋረጠዉ ትልቅ የድንጋይ ግንብ አጥር እና የሆስፒታሉ ሌላ ትንሽ ክፍል ሌላ፤ ምንም የሚታይ ነገር አልነበረም:: ሰማዩም በትልቅ ዛፍ ቅርንጫፍ ተከልሎ ነበር:: ግራ የተጋባዉ ይሄዉ በሽተኛ፤ ነርሶቹን ይሄ በፊት ተኝቶ የነበረዉ ሰዉ ‹ህፃናቱን ሰዎቹን ሰማዩ› እያለ ይነግረዉ እንደነበር እና አጥሩና ዛፉ እንዴት ከመቼዉ እንደመጡ በጠየቀ

ጊዜ፤ በፊት ተኝቶ የነበረዉ ሚቹ፤ እድሜዉን በሙሉ ማየት የተሳነዉ ግለሰብ እንደነበርና፤ አጥሩም ዛፉም ለአመታት የነበሩ እንጂ አዲስ አለመሆናቸዉ ያስረዱታል።

በዚህ ትንሽ አጋጣሚ የዚህን ማየት የተሳነዉ ግለሰብን ደግነት ጥልቀት መመልከት አያዳግትም። ጀግንነት ሁሌም ከጎራዴ ብቻ እንደማይመጣ ከላይ በጠቀስኩላችሁ ደቀ-መሐሪ ያገኘሁዋቸዉ ሁለት ሰዎችና ከቄስ ኦስቲን ትረካ መመልከትም አዳጋች አይመስለኝም።

ቀደም ብዬ ከላይ የዘረዘርኳቸዉም የልጅ እያሱ ዘመን ተጓዳኝ አገራዊ፤ አህጉራዊ እና አለም-አቀፍ ዉስብስብ ሁነቶችን በመንተራስ እነሆ የራሴን እተያይ ለአንባቢ ያቀረብኩ ሲሆን፤ ሌሎች የዘመናችን ድርሰት ፀሀፊዎችም ይሄንኑ ድንቅ ዘመን በብዕራቸዉ እንደሚጎበኙትና፤ የተለያየ አተያይ ያላቸዉ ድርሳናትን ለአንባቢ እንደሚያቀርቡም ሙሉ እምነቴ ነዉ።

መልካም ንባብ።

ጌታቸዉ ታረቀኝ (ጥቅምት 2008)

## ይቺ ትንሽዬ መጥሀፍ መታሰቢያነቷ

### ስማቸዉ ላልተመዘገበ ጀግኖች

## ምስጋና

ከዚህ በፊትም ሰባት ድራማዎችን የአካተትኩበት ‹‹የእንስሳት ጥናት እና ሌሎች የቲያትር ጨዋታዎች›› በተሰኘዉ ስራም ሆነ በዚች መፅሀፍም፤ ገንዘባቸዉን እና ዉድ ጊዜአቸዉን ሳይሰለቹ የሰጡኝ ብዙዎች ቢሆኑም፤ በተለይ አቶ ሀይሉ ከበደ፤ አቶ ጳዉሎስ አፅምሮ፤ ወንድሜን አቶ ፍቃዱ ወልደ ዮሐንስን እና እህቴን ነፃነት ጌታቸዉን ከልብ ለማመስገን እወዳለሁ።

*Special thanks to my wife Kidest Bekele, and my daughters: Naomi, Christian and Jerusalem; for laughing at my silliness and patiently endure my ignorance.*



<u>ገቢር 1</u>
ትዕይንት 1

መብራት ሲጠፋ መጋረጃዉ ከመከፈቱ በፊት ለተመልካች የሚነበብ

‹‹የተከበራችሁ ተመልካቾቻችን ዛሬ የምትመለከቱት ቲያትር በአገራችን የመንግስት ታሪክ ከ1905 እስከ 1928 ዓ.ም ድረስ የነበረዉን ሁኔታ በመሆኑ ዛሬ ከደረስንበት ግንዛቤ አንፃር እጅግ ኋላ ቀር አስተሳሰብ የሚንፀበረቅበት ዘመን በመሆኑ ይሄንን ቲያትር ታሪካዊነቱን ጠብቀን ለእናንተ ለማቅረብ በምናደርገዉ ሙከራ በጊዜዉ የአገራችንን ህዝቦች ባህል እና ወግ ካለመረዳትም ይሁን ባዶ ኩራት አንፃር፤ ዛሬ ተቀባይነት የሌላቸዉ ግንዛቤዎች በሰፊዉ የናኙበት ዘመን በመሆኑ እናንተም ይሄንኑ አቀራረብ ከዘመኑ ንቃት አንፃር እንድመለከቱልን በታላቅ አክብሮት እንጠይቃለን፡፡››

መጋረጃ ይነሳል፡፡....በጨለማዉ ነጋሪት ይሰማል፡፡...ጥሩምባ ይሰማል....(ጣሴ በባህላዊ



የቤተ-መንግስት ስርአት ለብሶ ይገባል።)

ጣሴ፦ (በአዋጅ ነጋሪ ስልት)...ስማ ስማ...ጆሮ ያለህ ስማ ..የሰማህ ላልሰማዉ አሰማ...ስሚ ስሚ ጆሮ ያለሽ ስሚ..የሰማሽ ላልሰማችዉ አሰሚ.....አፈሩ በጎርፍ ተሸርሽሮ እንዳያልቅ አቧራዉ እየተነሳ በንፋስ እንዳይቦንን ከፈረንጅ አገር እስመጥቼ የተከልኩትን የባህር ዛፍ እየዘነጠፍክ ጥርስህን የምትፍቅ የምትፍቂ...ጥርስ አባታችሁ ይርገፍና በድዳችሁ ነዉ የማስቀራችሁ። ቢሻዉ ጥርሳችሁ በስብሶ ይርገፍ እንጂ የባህር ማዶ ዛፌን እንዳትነኩ ብያለሁ!! የኮረንቲ መብራት ተከተማዉ አልፎ በየባላገሩ እንዲደርስ የዘረጋሁትን የመዳብ ሽቦ እየበጠሳችሁ የእጅ አምባርና የጆሮ ጉትቻ የምትሰሩና የምታጌጡ...እጅ እና እግራችሁን እያስቆረጥኩ መቀጣጫ ነዉ የማደርጋችሁ...(መብራት እየፈካ ይመጣል)...በነገይቱ ተሲአት ላይ ደግሞ የንጉሰ ነገስት እያሱ አምስተኛ...የንግስ በአል በታላቁ ቤተ መንግስት ሰለሚከበር ሙላሽ ሁላ መጥተሽ ምሳ እንድትበይ ተጠርተሻል!! በማትመጡት ላይ ግን...ትዝብት ነዉ ትርፉ!...(ከት ብሎ ይስቃል) ...ዘመን ተቀየረ ምኒሊክም ከአልጋ ወደቁ።...እኒያ የሰማይ ስባሪ የሚያህሉ ሰዉዬ...እንደ ጨዉ ሟሙተዉ...(ትንሽ ጣቱን ያሳያል) ...ይቺን ነዉ የሚያክሉት። ግርማ ሞገሳቸዉ ጥሏቸዉ ሄዶ እንደ ህፃን ነዉ ሴቶች በአንቀልባ እየያዙ ከእዳሪ የሚያወጧቸዉ። የእንጦጦ ማርያምን ግድግዳ ሲያሳድሱ ድንገት ሩሀቸዉን ስተዉ ከወደቁ ጀምሮ እንኳን ቆመዉ ሊያወሩ ተኝተዉም ፍጥጥ ብለዉ ከማየት በቀር ልሳናቸዉ ነዉ የተዘጋዉ።....የት እንዳሉም አያዉቁትም ነዉ የሚባለዉ።...የስልጣን ሽኩቻዉ ግና ተጀምሯል። እንሚባለዉማ...ዘመኑ ተለዉጦ (በሹክታ)...የሴቶች ሆኗል።...ስልጣን ከሸዋ ወደ የጁ እና ወደ በጌምድር እየሄደች ነዉ። መኩዋንንቱም ሚስቱን እየፈታ የት ነች የወረኢሉ የት ነች የሰሜኗ እያለ ነዉ።...ስልጣን በጋብቻ ይመጣል።....ራስ ጉግሳ ወሌ...የእቴጌ ጣይቱ ወንድም ልጅ...የምኒሊክን ልጅ ዘዉዲቱን ሊያገቡ ነዉ። የትግሬዉ ራስ መንገሻ ስዩም ልጅም..ማናት...የሮማ ወርቅ መንገሻን፣ እቴጌ ለልጅ እያሱ አጭተዉለታል ይባላል። እቴጌ አገራቸዉን ይወዳሉ ...ትርምስ አይፈልጉም። ምኒሊክም ተኝተዉ ከማየት ይልቅ ምንም የሚሉት ነገር የለም። አልጋ ወራሹም ገና በቅጡ አልጋዉን አልወረሱም። ችግሩ እቴጌ ራሳቸዉ ‹‹ትርምስ›› ብለዉ የሚጠሩትን የለዉጥ ማእበል ማቆም የሚችሉ አይመስሉም። ጅኒዉ ከጠርሙሱ ወጥቷል። እንግዲህ ማን እንደሚመልሰዉ እንጃ!

(እቴጌ ጣይቱ ብዙ ሰዎች አስከትለዉ ይገባሉ...ጣሴ እጅ ይነሳል። ከተከተሏቸዉ መሀል በነጠላ ተሸፍና የምታለቅስ ወጣትም አለች።)

እቴጌ፦ እንደምን ከርመሀል ጣሴ...

ጣሴ፦ (ለጥ ብሎ እጅ ይነሳል) ክብሩ ይስፋ ለመድሀኒአለም..እርስዎ እመቤቴ፣ ጌታዬ ምኒሊክ እስካሉ ምን ጎድሎብኝ።

እቴጌ፦ (በነጠላ ተሸፋፍና የምታለቅሰዉን)...ኧረ ዝም በይ እቴ..የምን ማልቀስ ነዉ?..ዘር ከልጓም ይስባል ሲባል አልሰማሽም? በዚህ ላይ ሴት ልጅ ከሴትነቷ በላይ አልቃሻ ከሆነች ማንም ነዉ የሚረግጣት። የሚረማመድባት። የሚያስለቅስ እንኳ ቢሆን ጥርሷን ንክስ አድርጋ ቀን እስኪሰጣት መጠበቅ ነዉ። ምንም አይደል ሁሉም በጊዜ ይፈታል።...ላልቅስም ካልሽ የራስሽ ጉዳይ ነዉ። እምባ ለማሸነፊያ ነዉ እንጂ፣ ለሆነ ላልሆነዉ የሚፈስ፣ ለሄደ ላገደመዉ የሚለቀስ አይደለም። ‹የሴት ጉልበቷ ማህጸኗ ነዉ› ሲባል እኔም ከአለፈ ነዉ የገባኝ። ታዲያ ዝም ብሎም አይደል መዉለድ ቢሉሽ..ይልቅ ቢገባሽ። የአንቺ አይነቷ ይሄን አይረባ አይታቀፌዉን ትወልድና፣ ትቀራለች ያለ ወገን በስተ እርጅና። በይ ይልቅ መነፋረቁን ትተሽ

‹‹ልብ የፈቀደዉን አይን የወደደዉን ነዉ የማገባዉ›› ከአልሽ...ኋላ ዘር ከጌኛ ቀይጠሽ...ፍቅሩ ሲደበዝዝ በጣም ታዝኛለሽ። ምነዉ ወትሮም በቀረብኝ ትያለሽ። ይሄ ማነዉ?...የጎበና ዳጬ ልጅ...ማነዉ? ...ደጃች ወዳጆ ጎበና....ምኒሊክ ልጃቸዉ ሸዋረጋን አጋብተዉት ሲያበቁ...ምን ይወለዳል?...ድክድክ የሚል መፃጉ ድንክ! አያነግሱት ወይ አይሸከሙት። ‹ደጃማች› ቢሉትስ ማን ተነስቶለት...(ይስቃሉ)...ኋላ ላይ በይ ተነስተሽ ወሎ ራስ ሚካኤልን አግቢ ስትባል እንደ አንቺ ብትነፈርቅ ታፍር ነበር ዛሬ፤ ግና ጎበዘች ይሄዉ ልጅ እያሱን ወልዳ አደረሰች። ‹ባሌን እወዳለሁ› የሚሉት የሞኝ አማርኛ (ልጅቷ ታለቅሳለች)...በይ ዝም በይ እቴ... ‹‹ፍቅር››ብሎ ነገር...የሞኝ አማርኛ። አሁን ይልቅ የሚነግስ የሚሾም ልጅ የምትወልጂበት ቦታ ነዉ የምትገቢዉ። በይ ይልቅ ሂጂና ተሰናጂ።...(ጣሴ የምታለቅሰዉን ደግፎ ይወጣል።)....ጃንሆይ የደከሙ እንደሆነ...በስንት መከራ የተገነባዉ አገር ሲፈርስ ዝም ብለን አንቀመጥም ...(ይቀመጣሉ)...ገና ሮጦ ያልጠገበ ልጅ ‹‹አልጋ ወራሽ› ብለዉ አገሩ ድንገት ቢበተን እኔ ጣይቱ ብጡል ዝም ብዬ አልቀመጥም። .ለዚች አገር እኔም ተዋግቻለሁ...ደጅ በዱር አድሬአለሁ....ይልቅ ቢትወደድ መንገሻ...

መንገሻ፡- (እጅ ይነሳሉ)..አቤት እመቤቴ...

እቴጌ፡- ይሄ ነቀምቴ የተላከ መልክተኛ አልተመለሰም?

መንገሻ፡- አልተመለሰም እሜትዬ። ዝናቡ አያሻግርም አሁን። ከሳምንት በሁዋላ ብራ ሲሆን ዉሀዉ ሲጎድል ይመጣል። ይልቅ የደጃች ባልቻ አባ-ነፍሶን እንዴት ሊያደርጉት ነዉ?...እሳቸዉም ከሐረር መነሳታቸዉን አልወደዱትም። የእኔም መቸም አገዉ ምድር ግዛቴ ነዉ። ስንት መስዋእትነት ከፍለን ያገኘነዉን ዳረጎት አገር፤ አሁን በዚህ ሰአት ሹማምንቱን መለዋወጡ መቸም ተእርስዎ ባላዉቅም መልካም አይመስለኝም...

እቴጌ፡- የእርስዎን ትተን... በተለይ ባልቻ አባነፍሶ...ከርፋፋ ባላገር....ከጦር ዉጊያ ዉጪ አይችል አገር ማስተዳደር። ብዙ ቅሬታ ስለሰማንበት....በሀረርጌ ደጃች ተፈሪን ሾምንበት። ወትሮም ሐረርጌ የአባቱ ነዉ። የመኮንን፡ አባቱ ያቀናዉን አገር፡ እንደ አባቱ ሆኖ ያስተዳድረዋል። በስንት መከራ ያገኘነዉን አገር ባልቻ ሳፎ ሲያበላሸዉ ዝም አንልም።.../ጣሴ ተመልሶ ይገባል/...

መንገሻ፡- እኔማ መቼም ይሄ ሰዉ የሚለዉን...‹‹ምኒሊክ በሰላም የአሰረዉን ቤት እቴጌ እየፈቱት ነዉ›› የሚለዉን ወሬኛ በቀላሉ እንዳያዩት፤ በማለት እና የራሴንም ጉዳይ ከዚሁ ጋር እንዲያዩት እኛም ከእርስዎ የሚሰጠንን ትእዛዝም ሆነ ማናቸዉንም ጉዳይ..(የአፍ እና እጅ እንቅስቃሴ ቀጥላል)

ጣሴ፡- (ለተመልካች)..እቴጌ ማፋታትና ማጋባት ብቻ ሳይሆን የዱሮ መሳፍንት መኳዋንንትን እያሻሩ የራሳቸዉን ሰዎች ብቻ መሾም ከጀመሩ ቆይተዋል። አደገኛ ነገር ነዉ..አልወደድኩላቸዉም።

እቴጌ፡- (ይስቃሉ)..አይ ቢትወደድ መንገሻ ...ባቡር ስልጣኔ አሉኝ? ቢቻልማ..ይሄን የተገተረ ብረት አወላልቀዉ ቢጥሉት....ዱሮም ይሄ ባቡር የሚባል እሽክርክሪት ...ጠላትን ከዳር አገር አንስቶ ወደ መሀል ለማምጣት ካልሆነ አይጠቅመንም ብዬ ነበር፡ የአገር ነጋዴ በአቅራቢያዉ ሸቅጦ ተመላልሶ እንዳይነግድ ያደርጋል። የባእድ የባህር ማዶ ትርኪምርኪ እያመጣ አገራችን የሚመረተዉን እንዳይሸጥ እና በአገር ያለዉን ፈጠራ ያግዳል። ጥሩም ነገር አይመጣም...

መንገሻ፡- በርግጥ ልክ ነዎት....ባቡሩ ምርት ካለበት ቦታ ወደ ገበያ ለማድረስ ወይ ሰርቶ በሌዉን ወደ እርሻዉ ማድረሻ ወደ ማምረቻ ስፈሩ ማድረሻም ካልሆነ፤ ቦታና

ብረት ማባከን ነዉ። ይሄን ያንዱን ሰፈር ባተሌ ወደ ሌላዉ ባተሌ ማመላለሱ ብዙም ጥቅም የለዉም...ያዉ እርዳታ ከሆነም...

እቴጌ፡- እርዳታስ ከሰጡን ማረሻዉን በቀየሩልን ነበር የሚጠቅመን። አዉቀዉ ነዋ...በእርዳታ በትንሽ ብድር ትጨርሱታላችሁ..ብለዉ ያለችንን ገንዘብ ሲያከስሩን ነዉ እንጂ ከዉጭ የሚመጣ ለእኛ የሚጠቅም አንዳች ነገር የለም። ባቡሩን ጎማዉን ወይ ወንበሩን እንኳ እዚህ አገር ለምን አይሰራም? ቢበላሽ የማናድሰዉ ቢሰበር የማንጠግነዉ ነገር ምንም አይሰራልንም። ደሞ..‹‹በዚህ ባቡር እየሩሳሌም ድረስ ትመላለሽበታለሽ›› የሚሉኝ። እየሩሳሌም በዚህ በሰሜን ሽቅብ መስሎኝ? ይሄ ስዉር ደባ ነዉ። ያኔ በዉጫሌ ሞክረዉን ያልተሳካለቸዉን ቅኝ ግዢ፡ አሁን ባቡር ሰርተን ስናበቃ ከሶማሌ ተቀምጠዉ የሚጠብቁትን ጥልያኖች ማስገቢያ ሊያደርጉት ነዋ...ሞኝ እኮ ነዉ የሚያደርጉን።

መንገሻ፡- መቸም በእነሱ ቋንቋ አለመናገራችን ኋላ ቀር እየመሰልናቸዉ...

እቴጌ፡- ቋንቋ ቢሉኝ አንድ ነገር ትዝ አለኝ....ይሄ ማነዉ የሚሉት?.. የእንግሊዙ ቆንስላ...እንዲህ ብረት ምጣድ የመሰለ የሚንጣጣ ነገር አመጣና...‹‹የእንግሊዟ ንግስት ናት ሰላምታዋን ስሚት›› ሲል ጊዜ፡ ጃንሆይ እንዲህ ከአልጋ ሳይዉሉ ... ተነስተዉ በደስታ ዘለሉ። እኔ ደሞ...‹‹እረ እንዲህ እንደ ተልባ የሚንጣጣ ነገር የንግስት ሰላምታ ይሁን ወይ የአሽከር ቻቻታ በምን ለይተዉት ነዉ? ብዬ ብል...‹‹በይ ዝም በይና የአንችንም ድምጥ በሽክላዉ ካለስቀረጥሽ››ብለዉ አኩርፈዉኝ ከረሙ። እጤ ቴዎድሮስ..መሬቱን ገለባ ያድርግላቸዉና ...‹‹የሚጠቅመኝን የሚበጀኝን ስጡኝ፤ እንደ ህጣን ልጅ ተራ መጫወቻ አትላኩልኝ›› ብለዉ ቢሉ አይደል እንዴ...ስንት ሺህ የህንድ ወታደር ይዞ እንግሊዝ ቋራ ድረስ የመጣባቸዉ? ይሄ የባቡር መንገድም ነገር አለዉ። ዳሩ ማን ሰምቶኝ? ይሁን እንጂ ዛሬ እንደ ትናንቱ ዝም አልልም።

መንገሻ፡- ልክ ነዎት፤ መቀየር የማይቻል ነገር የለም። እርስዎ የጀመሩትም መላ መልካም ነዉ። ቢሆንም... ያዉ ብልሀት እና ዘዴ ይፈልጋል። በታሪካችን ወዳጅን መደገፍ ጠላትን መደቆስ የተለመደ ቢሆንም...መቼም እርስዎን መዳፈር አይሁንብኝ እና... (አፍ እና እጃቸዉ ይነቃነቃል)

ጣሴ፡- ቢትወደድ መንገሻ ዳር ዳር ከሚሉ ለምን ከአገዉ ምድር ግዛቴ አነሱኝ? ...መልሱኝ ብለዉ ቁርጥ አርገዉ መጠየቅ ወይ ከአኩራፊዉ ጎራ ገጥመዉ እቴጌን ለመጣል የማይቻል መሆኑ ገብቷቸዋል ማለት ነዉ?...(ይወጣል)

እቴጌ፡- አይ ቢትወደድ መንገሻ...መች አሰርተዉኝ። ይሄ ተሰማ የሚባል ደንባራ በቅሎ ከኃብተ-ጊዮርጊስ ጋር ሆኖ...በረባ ባልረባዉ ‹‹የልጅ እያሱ እንደራሴ›› ፈቃድ ይጠየቅ› ይለኛል። እሱን ብሎ የዘዉድ ጠባቂ አማካሪ?!! እንደራሴ!! ልጅ እያሱ...ገና ሮጦ ያልጠገበ ልጅ ...ምኑን አዉቆት ነዉ የሚፈቅድ የሚከለክለዉ?? አገር ያለጠባቂ ሲያድር ሲበተን ዝም ልንል ነዉ?

መንገሻ፡- እረ ማንም እሺም አይል!....በተለይ ራስ ኃይሉ...ሌላዉስ የምኒሊክ አርበኛ፡ ከቶም ዝም አይል ከሰማዉ ከእኛ።...ያዉ እንዳሉት ለእጨጌዉ ቢነግሯቸዉ ...የተባለዉ የምኒሊክ ቃለ-ኑዛዜ...ባይሆን እንደገና ቢመክርበት...ሌላ ለአገር ለአንድነት የሚበጅ በሳል ሰዉ በዙፋኑ ቢቀመጥበት...

እቴጌ፡- በኑዛዜዉስ እንደገና መነጋገሩ ባልከፋ..ግና...አባ ማቴዎስ የሚባል...

መርእድ፡- ገባኝ...እጨጌዉ መግፋት ይችላሉ...ወትሮም የግብጥ ቄስ፤ ጳጳስ ቢሉትስ ምን ሊመልስ?

እቴጌ፡- ልክ ነዎት ግና መች ሆነና....

መርእድ፡- ይልቅ የእርስዎ ወንድም ልጅ፤ ጉግሣ ወሌ፤ ዘዉዲቱን ከአገቡ፤ ዘዉዲቱም የምኒሊክ ልጅ ናቸዉ። የልጅ ልጅ ድረስ ምንም የለም የሚያስኬዳቸዉ። በሳል ሰዉ በወንበሩ ሲቀመጥ ሰላም ይሰፍናል። (በሹክታ)...አሁን በሰሜን ባላገሩ እንደሚያወራዉ...ራስ ሚካኤል በርግጥ የፅዮን ንጉስ ከሆኑ....ይሄ ክርስቲያኑ ...የትግሬዉ የበጌምድሩ፡ ሌላዉም የዳር አገሩ፤ሙላዉ ክርስቲያን ማመጡ አይቀርም ለማተብ ለክሩ!

ጣሴ፡- (ተመልሶ ገብቶ እጅ ይነሳል)...እመቤቴ..ስኞር ባንቶሎኒ ገብቼ..ጃንሆይ እና እርስዎን እጅ ልንሳ ይላል...

እቴጌ፡- እጅ ልንሳ አለ?...እጅ የሚነሳዉ ሰዉ ተጋድሞ ተኝቷል...እየሰማ አንቀላፍቷል...ነፍሱ ሳትወጣ ሞቷል። ባንቶሎኒ ወሬ ለመቃረም እንጂ... ለአለቆቹ ጦር አዝምቱ ሲል..ሲሰልለን እንጂ...እጅ አይነሳም። እጁ ና!...እንደምትለዉ... ጃንሆይ ማለዳ ላይ አደን ወጥተዉ ገና አሁን ስለገቡ ደክሟቸዉ ትንሽ ጋደም ብለዋል› በለዉ። ይሄ ነጫጭባ...አንድ ነገር እንዳለ አዉቋል። ልጅ እያሱን በመጫወቻ እንደሚያታልሉት እኔንም ሊሞክረኝ ነዋ።...ወሬ ለማነፍነፍ ነዉ። ሂድ ንገረዉ ‹‹እሷም ብርቱ የአገር ጉዳይ ላይ ናት›› በለዉ።....ይወቀዉ እኔ እንደማልሸነፍ፡ ይሄ ክልፍልፍ!! ‹ማንም አሁን የለም በለዉ፤ ከደፍ ከደጃፍ እንዳይቀመጥ ወዲያ አስወጥተህ አርቀዉ....(ጣሴ እጅ ነስቶ ዱላዉን እያወዛወዘ ሲወጣ ደጃች መርእድ ፈጠን ብለዉ ገብተዉ እጅ ይነሳሉ)

እቴጌ፡- እንዴት ከረሙ ደጃች መርዕድ?

መርዕድ፡- ክብሩ ይስፋ ለላይኛዉ ጌታ..እርስዎስ እንዱት ነዎት? ጌታዬ ምኒሊክስ?

እቴጌ፡- ክብሩ ይስፋ ለመዳህኒአለም..ሁላችንም ደህና ነን።

መርዕድ፡- እኔማ..አሁን ከበተስኪያን መልስ...ከደጃች ወሰን ዘንድ ደርሼ...በእርስዎ እና በዘዉዱ ባለ አደራዎች መሀል ‹‹ጠብ ተፈጥሯል›› ሲሉኝ ጊዜና፤ ጆሮዬን አላምን ብዬ...ተእርስዎም፤ ተእናታችን ዘንድም ተሰዉሮ እንዳይቀር። እርቀ ሰላምም የጌታ ቡራኬ እንዳይርቀን፡ ሰይጣን ተመሀል ገብቶ እንዳይለያየን፤ በጨዋ ደንብ እና ስርአት ተነጋግረን። እንደ ባህላችን ሚስጥራችን ሳይወጣ ...የሚባለዉ እዉነት ከሆንም መላ እንዲበጅለት በማለት ነበር አመጣጤ...

እቴጌ፡- ምን ጠብ አለ ደጃች መርዕድ?....ምኒሊክ ታሞ ቢተኛ፡ ሁኖ የአልጋ ቁራኛ..እሱን እና እኔን እንደ አሮጌ ቁና አዉጥተዉ ለመጣል ...እ? ይሄ አሿራዉን እያራገፈ፤ የልመና አኩፋዳዉን እያስጣለ ባላባት ባለስልጣን ያደረገዉ ሁላ....ዛሬ ጉልበቱ ቢደክም ልቡ ብትታመም፡ አዉጥተዉ ሊጥሉት? እሽቅድምድም ነዉ እኮ የያዙት...

መርዕድ፡- ፊታዉራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ እና ራስ ተሰማ ናደዉም ትናንት ማለዳ ላይ...

ጣይቱ፡- ተሰማ ናደዉ...መዐት ናዳ ይዉረድበትና...እሱን ብሎ የንጉስ ዘዉድ ጠባቂ ባለአደራ...የገንዛ ሚስቱን እንኳ በቅጡ መጠበቅ የማይችል ከርፋፋ። ከዚህ ጨዋነት ከጎደለዉ ስርአተ አልበኛ ጋር ገጥሞ...እኛን ገሸሽ ለማድረግ፤ ስርተን እንዳልሰራን። ለዚች አገር መቅናት ከወንዱ ጎን ተዋግተን ደም እንዳላፈሰስን። ወራሪ ጠላቷን እንዳላሳፈርን፤እንዳልሞትን እንዳልደማን...አሁን ገለል ሊያደርጉን ...አሁን አንቺ ተቀመጭ ነዉ የሚሉኝ። አንቺ አይሽን ዝጊ እኛ እንይበት...አንቺ ዝም በይ፤ እኛ እንናገርበት። ጥልያንስ ቢሆን ከዚህ ወዲያ መች ጠየቀን...እኔ ጣይቱ ብጡል ለእንዲህ አይነቱ ግፌትና ጋጠ ወጥነት ቦታ አልሰጠዉም።

መንገሻ፡- እኔ እምለዉ ደጃች መርዕድ...አገር ሲበተን እና እምዬ ምኒሊክ ያቀኑት አገር

እና ስርአት ዛሬ ታመዉ ከአልጋ ሲዉሉ...ማንም ሲደፍረዉ ማየቱ አግባብ አይመስለኝም:: እቴጌ የፈጠሩት መላ ብልሀት፤ ምኒሊክ ያሰቡ የወጠኑት ላይ ለመድረስ ነዉ:: ፍርድም እንዳይጓተት፤ አገርም እንዳይዋልል በመሪ እጦት ...እርዳታ ማድረጋቸዉ አሁን ምን ክፋት አለበት? እንዲያዉም የራስ ተሰማን ስራ አቀለሉት:: እኛም በደንቡ መጥተን አቤት ማለት፤ ደጅ ጥናት ሁሌም የአለ ነዉ የአባት:: መልስ እናገኛለን ለአቤቱታችን...በደንቡ ምላሽ መጠበቅ ምክክር ማድረጉ፤ ጠላት በመሀል እንዳይገባ ማድረጉ ይበጃል ለስርአቱ... ሳይጣሉ ሳይጓተቱ!

መርዕድ:- ትክክል ብለዋል ቢትወደድ...ለሁሉም ምክክር ጥሩ ነዉ...ምክክር ታዲያ የሁለት ተመካካሪዎችን ትብብር ይፈልጋል:: አንዱ ተናገሪ ብቻ ልሁን ከአለና የሌላዉን አልሰማም ካለ፤ ምክክር መሆኑ ይቀር እና እነኚህ የተማሩት እንደሚሉት ዲስኩር የሚሉትን ይሆናል:: መነጋገር መቀባባል መሆኑ ይቀርና አንዱን ሰጪ ሌላዉን ተቀባይ ብቻ ያደርጋል:: ይሄንን ነዉ እነሱም የሚሉት፤ እንምከር ነዉ ያሉት...‹ኋላ ላይ ችግር እንዳይመጣ› ከአሁኑ እንምከር ነዉ የሚሉት:: መቸም የሚሉትን መንገሬ...

ጣይቱ:- ኧረረረ!...‹ኋላ ላይ ችግር እንዳይመጣ!?› አሉ?.....ይሄ ዛቻ ነዉ...ኋላ ላይ ምን ያመጣሉ!? እኔም የወደቅሁ የታመምሁ መሰላቸዉ? እንተያያለና!!!...መነጋገር መቸ እንደዚህ በዛቻ...ምኒሊክ ታመመ እንጂ አልሞተ..እኔ ነኝ ከእነሱ በትእዛዝ የምመካከረዉ? ለጥልያንም አልተንበረከኩ እኔ ጣይቱ ብጡል.... እንተያያለን!!... (በቁጣ ተነስተዉ ይገባሉ..አጃቢዎቻቸዉም ተከትለዋቸዉ ይገባሉ)

መንገሻ:- /ፋታ/...ይሄ ጦርነት ነዉ!

መርዕድ:- ከእሱ ይሰዉረን..(ወደ ላይ አንጋጥጠዉ)...ሰማይን ያለ ባላ፤ ምድርን ያለ ካስማ ያቆምክ ጌታ፤ ይችን አገር ከመዓት ከጦርነት ጠብቃት:: እባክህ ደጋግፌህ አቁማት:: ለነፍስ ማለበሻ የሚሆን ተስፋ አታሳጣት:: የሌሎችን ዉድቀት እና ሽንፈት እንደ ራሳችን ውድቀት እንዲንመለከተዉ ብርሀን ብልህነቱን ስጠን::

መንገሻ:- በርግጥ ደፍሮ እቴጌን የሚናገር ይኖራል ብለዉ ነዉ?...የምኒሊክም ስራዊት ዝም አይለዉም::...ያንን ሀይል ማንም አያሸንፈዉ:: ከንቱ የጅል ሙከራ ነዉ::...(እቴጌ በወጡበት ይወጣሉ)

መርዕድ:- እሱስ ጉልበት ኃይል ያለዉ ሳይሆን፤ ራሱን መቀየር መለወጥ የሚችልበት ነዉ የሚከርመዉ.../ፋታ...ፊታዉራሪ ኃብተ-ጊዮርጊስ፤ ደጃች ገብረ ስላሴ ባርያ-ጋብር፤ ደጃች ደምሰዉ ነሲቡ እና ራስ ተሰማ ናደዉ ይገባሉ::)

ተሰማ:- እቴጌ የታሉ?

መርዕድ:- አሁን ላይኛዉ ቤት ሄዱ መሰል...(ተሰማን ተከትለዉ ሊገቡ ሲሉ መንገድ ይዘጋሉ/...ኧረ የለም አሁን ጥሩ አይደለም...ተቆጥተዉ ነበር ደሞም ተናደዋል:: ነገሩ አማላጅ ያስፈልገዋል::

ኃ/ጊዮርጊስ:- ምኑ ነዉ አማላጅ የሚያስፈልገዉ?

መርዕድ:- ለሁሉም ትእግስት መልካም ነዉ:: ትእግስት ማር ነዉ::

ገ/ስላሤ:- አይ ማርም ሲበዛ ይመራል:: ከእምዬ ምኒሊክ ጋር የአቀናነዉ አገር ሲበተን ዝም ማለት አንችልም:: አፉ ታስሮ መናገር ባይችልም..ትናንትን ገብቶ ሳየዉ፤ ‹ምነዉ ገብርዬ በጥልያን ያልተሸነፍክ ያልተንበረከክከዉ እንዴት ኑዛዜዬን ችላ አልከዉ› ብሎ ያለ ነዉ ሚመስለዉ::

ኃ/ጊዮርጊስ፡- አይ ጌታ ብርሃን ክርስቶስ እንዲህ እንዳይናገር አርገህ ታስቀምጠዉ? ...ትልቁን ጀግና ቃል ኑዛዜዉን የሚያከብርለት ልታሳጣዉ? ጥልያን ከፊቱ ደፍሮ ማይቆመዉ እንዲህ አርገህ ታልጋዉ ታዉለዉ???..(እንባቸዉን ያደርቃሉ)

መርዕድ፡-(ለተሰማ)..እርስዎ ባይሆን ቀስ ብለዉ ለእቴጌ ቢነግሯቸዉ...ደግ እሩህሩህ እናት ናቸዉ፡፡

ተሰማ፡- እኔ ከአቅሜ ዉጪ ነዉ...ስድብ ቁጣ ግልምጫቸዉ ነዉ የሚተርፈኝ፡፡ ‹እርስዎ እኛን ሳያማክሩ ሹም ሽረት አያድርጉ፤አልኩኝ፡፡ ራሴም በአማላጅም ሞክርኩኝ ...ምን ሳደርግ ነበር ከዚህ በላይ?፣፣ምክር ካለዎት ይንገሩኝ አልኩኝ፡፡

ኃ/ጊዎርጊስ፡- ራስ ተሰማ፤ በልጅ እያሱ ሞግዚትነትዎ ብቻ ሳይሆን የንጉስ ቃል የእምዬ ምኒሊክ ባለ አደራ የዘውድ ጠባቂ በመሆንዎ፤እርስዎ ከእንግዲህ የእቴጌን ቃልና ምክር መቀበል የለብዎትም!

መርዕድ፡- መማከሩስ ጉዳት አልነበረዉም ዳሩ...

ገ/ስላሴ፡- የለም...ውሃ ቁልቁል እንጂ ሽቅብ አይፈስም....ከእርስዎ ሁላችንም እንሰማዋለን እንጂ ከተጌይቱ ወደ እርስዎ አይላክም፡፡

ተሰማ፡- ሞክርኩ እኮ! የለም ይበቃል ከእንግዲህ በልጅ እያሱ ስም እንጂ በምኒሊክ ስም ምንም አይደረግም አልኩኝ ወተወትኩኝ...ታመመ እንጂ ሞተ ያለህ ማነው? አሉኝ፡፡ በዚያ ሰሞንማ መቼም የሚናገሩኝ ንግግር...‹አንተ ወንድ ነህ ወይ› ይሉኛል በጎንዬሽ አማረኛ፡፡ ...ግን መቼም ሲያቅተኝ እንጂ...

መርዕድ፡- ቢሆንም ራስ ተሰማ...እተጌ ሁላችነን ነዉ የሚዘልፉት...መቼም የሚወዷቸው ንጉስ ከአልጋ ቁራኛ ሲሆኑባቸው፤ ሆድ እየባሳቸው...የሚናገሩትን ሁሉ ከክፉ አይውሰዱባቸው...

ተሰማ፡- ደጃች መርእድ...ሆድ ስለባሳቸው አገር ያጥፉ ነው የሚሉት? እግዚያብሄር የማይወደው ትልቅ ስህተት ነው የሚሰሩት፡፡

መርዕድ፡- መቼም...ስህተት ፈጥመው ይሆናል...ሆኖም ስህተት የማይፈጥመው ይሄ የተነገረውንና የተባለውን ብቻ የሚሰራው ባተሌ እንጂ....መልካም ምግባር ልፈጥም፤ አገር ላቅና ብሎ ተነሳስቶ የሚሰራ ሁሌም ስህተት ይሰራል፡፡ ተጌም የተጀመረው የምኒሊክ ውጥን እንዳይፈርስ...ዘዴ መላ ያሉት እንጂ...እሳቸዉ ማንንም አያስቀይሙም፡፡

ኃ/ጊዎርጊስ፡- ለክፋትም ይሁን ለደግነት የተጀመረ የሚፈጠመው በአልጋ ወራሹ ነው! በልጅ እያሱ፡፡ እንግዲህ ሌሎችም ይምጡና መክረን አምነን እንደተስማማነው፤ የንጉስ አገር ህግ...የምኒሊክ ኑዛዜ እንዲከብር ባንድ ትንፋሽና አንደበት መናገር ይገባናል፡፡ ይህን በማለታችን ምንም አናፈርስ ከቃል ማተባችን፡፡ ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው ባህላችን፡፡ ኑዛዜ የመጨረሻ ቃል፤ የማይለወጥ የማይታበል፤ በሰማይ በምድር ሚያስጠይቅ፤ የቋሚ የሰሚን አደራ የክርስቲያን ማህተብ...ሀራም አይበላም..እርም ነዉ! ከቶ የኑዛዜን ቃል መለወጥ የሚችል አለ? ደጃች መርዕድ?

መርዕድ፡- አሱስ ትክክል ነዎት...መቸም ነገር ለማብረድ እንጂ....

ተሰማ፡- እስቲ አሁን ቱግ ብለው ‹ለፈስፋሳ ወንድ› ነውኮ የሚሉኝ፤ አሁን ምን አደረግኳቸዉ?

ኃ/ጊዮርጊስ፡- አይ...እኔንም ‹ዘብዛባ ሽማግሌ› ነው የሚሉኝ፡፡ ዋናው ጉዳያችን ግን

ለጌታችን ለምኒሊክ የሰጠነውን ቃል መጠበቅ መቻላችን ነው፡፡ የማንም ስድብና ዘለፋ አያስቀረንም ከግባችን!

ገ/ስላሴ፡- አይ እኔንም ሰው አያደርጉኝም፡፡ ‹አሁን የገበሬ ምን ባላባት አለው?› ነው የሚሉኝ፡፡ ለእሳቸው ከየጁ ወይ ከጎንደር ያልመጣ ሁሉ ተራ ባላገር ገበሬ ነው፡፡....(አባ ማቴዎስ፤ ከእጨጌዉ እና ከደጃች ወሰን ትርፌ ጋር ይገባሉ)

ማቴዎስ፡- ምንድነው ነገሩ?...ደጃች ወሰን ‹ብርቱ ነገር አለ› ነዉ የሚሉኝ...በደህና ነው አመጣጣችሁ? ቅዳሴን የሚያህል ነገር አስተጓጉዬ እንድመጣ የላካችሁብኝ?... ምንድን አገኛችሁብኝ?...(ሁሉንም በየተራ መስቀላቸውን ያሳልማሉ ‹ይፍቱኝ› ይላሉ)...ፊታውራሪ ኃብተ ጊዎርጊስ ምንድን መጣ?...(በለሆሳስ...አጭር ፀሎት ያሰማሉ)...አቦክሙ ሰማያዊ ዘትፈቅዱ ዘእንበለ ትስኦልዎ.../ፋታ/..አሜን

ሁሉም፡- አሜን፡፡

ማቴዎስ፡- እና ምንድን ነዉ ነገሩ?

ኃ/ጊዬርጊስ፡- አይ አባታችን አቡነ ማቴዎስ...ትንሽ ብርቱ ጉዳይ ገጥሞን ነው፡፡ የእርስዎን እርዳታ የሻነዉ፡፡ ያዉ እርስዎ እንዳስተማሩን መጽሃፉም እንደሚለው ቃል አባይነት መልካም እንዳልሆነና፤ ከደከመ ነፍስም የተሰጠ ኑዛዜም በእግዚያብሄር ፊት የተረከብነው አደራ በመሆኑ፤ ቃለ-ኑዛዜ ሲናቅ ሲጠፋ ዝም ብለን መመልከቱ፤ በጌታ ፈጣሪያችን ፊት እኛም ለፍርድ በምንቀርብበት ጊዜ የሚያስኮንን በመሆኑ፤ ዛሬ የእርስዎን እርዳታ እንሻለን፡፡

ገ/ስላሴ፡- በጣም ነዉር ነዉ፡፡እንኳን ፍታት ተደርጎላቸው ያልተቀበሩትን መልካም ንጉስ ኑዛዜ ቀርቶ፤ የድሃውን ጣረ ነፍስ የመጨረሻ ትንፋሽ እንኳ...ኑዛዜ ቃሉን መጣስ ያስኮንናል፡፡ በክርስቲያን ደንብ የሌለ የአረመኔዎችን ስራ እንደመስራት ነው፡፡ አባቴ...ዛሬ የጌታችን የምኒሊክ ኑዛዜ ተለውጦአል፡፡ በምድር መከራ በሰማይ ኩነኔ ተጋርጦብናል፡፡

ማቴዎስ፡- ማነው የእምዬ ምኒሊክን ኑዛዜ የጣሰው?? ይሄ መቼም ትልቅ በደልና ሃጢያት ነው፡፡ የእምዬ ምኒሊክን፤ የኒህን ጣድቅ የክርስቲያን አገር መሪ፡ ለሃይማኖቱ እንደ ጣዲቁ ዬሐንስ አንገታቸውን ለእምነታቸው የሚሰጡ፤ የእሳቸውን ኑዛዜ የሰበረ የሚጥስ! ውጉዝ ነው ከመ አርዮስ! እንዲህ አይነቱን ሰዉ መገሰጥ እና ሱባኤ ገብቶ ለነፍሱ ይቅርታ መጠየቅ ይኖርበታል!

ወሰን፡- እተጌ ናቸው፡፡ (ማቴዎስ ያማትባሉ)...ከጌታችን ፍቃድና ፍላጎት ውጪ ያሻቸውን ያደረጉና ባላደራዎቹ ባላወቅነውና ባልመከርንበት ጉዳይ ሁሉ ውሳኔና ሹምሽር እያደረጉ ብዙ ችግር አመጡብን፡፡ በላባቱ ርስት ጉልቱን እየተነጠቀ ነዉ፡፡ አገር ሊበጠበጥብን ትንሽ ነው የቀረዉ፡፡ ወሎ ለሁለት ተከፍሎ ሊዋጋ ነው፡፡ ባላባት ለባላባት እንደገና ጦር ሊማዘዝ ነው፡፡ ራስ ወሌ ራስ ሚካኤልን፡ ራስ ሀይሉም ከጎጃም ራስ ስዬም መንገሻም በትግሬው አገር...ብቻ አገሩ ሊታመስ አንድ ሀሙስ ነው የቀረው፡፡ ራስ ተሰማም ምንም ማድረግ አልቻሉም፡፡

ገ/ስላሴ፡-አይ እመብርሃን....መቼም ምኒሊክ እንደበታቸው ቢታሰርም በሁላችንም ላይ እንዳዘኑብን ነው የሚሰማኝ፡፡ አሁን በዚያ በፍርድ ቀን ከላይ ስንገናኝ ምን ብለን እናሳብባለን? ‹ምን አረጋችሁት ቃሌን?› ቢሉን ምን መልስ እንሰጠዋለን?

ኃ/ጊዬርጊስ፡- (ለማቴዎስ)... አባታችን እርስዎ እንግዲህ ጉዳዩን በሚገባቸዉ አድርገዉ ለእቴጌ ጣይቱ ይንገሩልን፡፡ በአባትነትዎ ገብተው ይገስጡልን፡፡ ለእምዬ ምኒሊክ ኑዛዜ ክብር አሰጡልን፡፡ ከእንግዲህ የዘውድ ባለ አደራው ራስ ተሰማ እንጂ እሳቸው በመንግስት ስራ ላይ እንዳይገቡብን፡፡ ይንገሩልን፤ ይምከሩልን፡፡

ወሰን፡- ከዚያም በላይ እንዲሁ ያለ ምንም ምክክር በፈቃዳቸው የሾሟቸው መኳዋንንት ከግዛታቸው እንዲያነሱልን፡ የተሾሙት ሁሉ መሻራቸውን እንዲያሳውቁል። …ይሄንኑ ያስረዱልን።

ገ/ስላሴ፡- ደም መፋሰስ አያስፈልግም…መዋጋት ካለብን ግን ወደ ኋላ አንልም!

ማቴዎስ፡- ኧረ እዛም አትደርሱ..እስቲ ጠሎት እናርግበት…ናኩተከ በቁም ፈቃድከ ትምፃ መንግስትከ…(ሁሉም በለሆሳስ ፀሎት ሲያደርጉ ጣሴ ይገባል።

ጣሴ፡- ጠሎት ጥሩ ነገር ነዉ። እዛም ከላይ ቤት ሲፀለይ ነበር ወጥቼ የመጣሁት።ፈጣሪ ለማን እንደሚፈርድ አሁን እናያለን። .አባታችን ሆይ፤ በሩቅ የምትኖር፤ ጠላታችንን አጥፋልን፤ ወዳጃችንን ደግፍልን፤ የሚናገሩንን ምላሳቸዉን ቁረጥልን፤ የምናታላልላቸዉን አንደበት ብርሀን ከልልልን። ፆም ጠሎት ሲመችን እናደርጋለን …ስህተታችንን ግን፤ ክፉ መስራት ባናቆምም፤ ዝም ብለህ ይቅር በለን!…. (ይወጣል)

ሁሉም፡- አሜን።

ማቴዎስ፡- ግን ሁሉንም የሾሟቸዉን ሻሩልን ከማለት..ለተሻሩት ሌላ ቦታ ቢሾሙስ?…ሌላ ብጥብጥ እንዳናመጣና…

ኃ/ጊዮርጊስ፡ የለም! እንደሱማ አናደርግም…እሳቸዉ ስርአቱ የቆመበትን ምድር ሊንዱት ነዉ። የጁ እና ጎንደሬዉን ነዉ በብዛት የሾሙበት…በተለይ የሸዋዉን መኳንንት እና ህዝብ ለመጉዳት…እኔ ሁሉንም ይነሱ ነዉ የምለዉ።

ገ/ስላሴ፡-. ሁሉም ይነሱ፤ የተነሱት ይመለሱ!

ወሰን፡- እኔም እስማማለሁ በእሱ!

መርዕድ፡- መቼም ከእንግዲህ ወዲያ ባለዉ ቁርጥ ብናደርገዉ አይሻልም…ያለፈዉን ስህተት በሌላ ስህተት መመለሱ…ራስ ተሰማ ምን ይላሉ?

ተሰማ፡- እኔም ሁሉም ይነሱ ነዉ የምለዉ…ሁሉም። ከደጃች ተፈሪ መኮንን በስተቀር፤

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ልክ ነው የሱ ይሁን። የአባቱ አገር ነው ሐረርጌ። ያደገበትን የሚያውቀው በመሆኑ የእሱን ይርጋ ብለነዋል።

መርዕድ፡- መቼም ቅር እንዳይላቸዉ ቀስ አድርጎ በማስረዳት…

ገ/ስላሴ፡-ለእትጌ ከቀን ቀን የመንግስት ስራ ራሳቸው ካገለሉ፤ ለእምዬ ምኒሊክ ተገቢዉን ክብካቤ ለማድረግ ሰፊ ጊዜ ይሰጣቸዋል። ከጸሎት የራቀውን ልባቸውን፤ ይሁነኝ ብለው ፊታቸውን ወደ ፈጣሪያችን መልሰው ቢማለዱት የእምዬ ምኒሊክም ድንገት አፉ ይከፈትና ያን የምንወደው ቃሉን ከአንደበቱ እንደገና እንሰማው ይሆናል።

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እስከዚያ ግን፤ እንደ ወግ ባህላችን በጣዕር ያለውን ሰው የመጨረሻ ቃል ኑዛዜውን እንድናከብር አባታችን ሊረዱን ይገባል። ይቺን አገር ከመበታተን እንዲያድኑልን እኛንም ከመከራ እንዲታደጉን…ዛሬውኑ ገብተው ለእትጌ ያልነውን እንዲያሰሙልን ይሁን።

ገ/ስላሴ፡- መልሳቸውንም ያሳውቁን።

መርዕድ፡- አባቴ ያድኑን።

ገ/ስላሴ፡- መላው መኳንንት ባላባት የእርስዎን ቃል ይጠብቃሉ። አገራችንን ከመከራ አድኗት።

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ልጅ እያሱም ይሄንን የክህደት ነገር ሳይሰሙት ሳያውቁት በቶሎ ይቅጩት፡፡

ማቴዎስ፡- እንዳላችሁ አደርጋለሁ፡፡ የጌታችሁን የምኒሊክን ኑዛዜ መጠበቁና በቃላችሁም ታምናችሁ በመገኘታችሁ የሃይማኖታችሁ መርህ መሰረት የሆነውን የሰው አደራ ታአምኖ መጠበቅና፤ ከስጋዊ ፍለጎትና ጉጉት አጉል ስሜት ታቅባችሁ፤ የመሳሳትና የመሰሰት፤ ራስን ከመውደድ ጋር ከሚመጣዉ ሰይጣናዊ ስሜት...(መኩዋንንቱ መሰላቸታቸው ያስታውቃል)...ተቆጣጥሮና ገትቶ በመያዝ. ውስጣዊ...ዘከመ ቃል ዝንተ ወዝቱ ወቀስጠንጢኖስ ዝሙ ዘአስተርዌ...

ተሰማ፡- እምነት ተሰብሮ፤ የተናገሩት ከሚጠፉ፤ የወለዱት ይጥፉ!

ማቴዎስ፡- በርግጥ...ይሄ አለም ያሳሳል ያታልላል፡፡ ይሁን እንጂ እኔ ሳውቃቸው እተጌ መልካም እመቤት ናቸው፡፡ አውቀው በድፍረት ሳይሆን ስራን ለማቀላጠፍ፡ ፍርድ ሳያጓደል የንጉስ አገር እንዳይገሰስ አስበው፤ ድሮ በሚያውቁት በለመዱት እርስዎን ለመርዳት ስለሚሆን ቀስ አድርገዉ...

ተሰማ፡- አባቴ ሞክርኩ እኮ...በፊታውራሪ ሀብተ ጊዎርጊስ፤ በደጃች መርእድ፤ በደጃች ደምሰዉ በሚቀርቧቸው በቢትወደድ መንገሻ ሳይቀር አማላጅነት አቀምኩኝ ... ‹ይሄ በጎን መሾም መሻር ኋላ ነገር ያመጣል፡፡ ሌላ ስውር የማንቆጣጠረው የጎንዮሽ መንግስት ይፈጠርና፤ ኋላ ሁላችነንም ያፈርሰናል፡፡› አልኩኝ...

ኃ/ጊዎርጊስ፡- በርካታ መኳንንትና የምኒሊክ አሽከሮች የእርሳቸውን ምላሽ በጉጉት እየጠበቁ ስለሆነ፤ ጊዜ ሰፍቶ ሁሉን ሳያበላሽብን መልእክታችንን አባታችን በቶሎ ያድርሱልን፡፡ አገር ታምሶ ሌላ ነገር ሳይመጣብን፤ ገብተው አንድ ይበሉልን፡፡

ገ/ስላሴ፡- ይሄን ጉዳይ፤ ይሄ ድሃው ክርስቲያኑ ቢሰማው፤ ‹የንጉስህ የእምዬ ምኒሊክ ኑዛዜ ተሸሯል› ብንለው፤አገሩ መከራ ቀውጢ ነው የሚሆነው፡፡ ጦርነት ነዉ የሚፈጠረዉ!!

ኃ/ጊዮርጊስ፡- የኛ ጥያቄ ሌላም አይደል፡፡ ደንብ ስርዓት ይከበር ነው የምንለው፡፡ እቴጌን የሰሩትን ስራ የመናቅ ወይ ውለታቸውን የመዘንጋት ሳይሆን፤ አሁን እያረጉ ያሉት ነገር፤ አገር ያፈርሳል፡፡ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝንና የእስካሁኑን ሁሉንም ያፈርሰዋል የሚል ነው ፍርሃታችን፡፡ ከሁላችንም በላይ አገራችን ትቀድማለች አገሪቷ የሁላችን የልጆቻችን እንጂ የእቴጌይቱ የግል ንብረት አይደለችም፡፡

ወሰን፡- እዛ አይድረስ እንጂ...ጦር መማዘዝ ካለብንም ለአገራችን ለልጆቻችን ስንል እንዋጋለን! ...እቴጌን እንዳከበርናቸው እንደወደድናቸው እሳቸውም አሁን ጊዜው የእሳቸው አለመሆኑን መረዳት አለባቸው፡፡

ገ/ስላሴ፡- አገር እንደ እቃ እና ርስት፡ ባልየዉ ሲሞት የሚተላለፍ ንብረት አይደለችም!

ኃ/ጊዮርጊስ፡- አገር ጥሪ ነዉ የሰጠችን...ግልጋሎት መስዋእትነት ነዉ የምንከፍላት፡ እንጂ ጠቅልለን በሳጥን አናኖራትም፡፡

ማቴዎስ፡- እንግዲህ ከአመረራችሁማ አደርሳለሁ፡፡ ለእተጌ ያላችሁትን አስረዳለሁ፡፡ አሁን አፍታም ሳልቆይ እመለሳለሁ...(መስቀል ለማሳለም ያወጣሉ ፊታውራሪ ይሳለማሉ)

ወሰን፡- ሲመለሱ ያደርሰን ነበር እኮ....(በግድ ሁሉም ይሳለማሉ፡፡ ማቴዎስ መንገድ ይጀምሩና ድንገት ቆም ብለው ይመለሳሉ፡)

ሁሉም፡- ምን ነው? ምን ሆኑ?

ማቴዎስ፡- ጥቂት አሳሰበኝ ነገራችሁ። አሁን እተጌ ያልፈቀዱ፤ እምቢ ያሉ እንደሆን ...ምንድነው ሀሳባችሁ? ደም ሊፋሰስ በመሃከላችሁ?

ኃ/ጊዮርጊስ፡-አባቴ፤ ቃል ያጠፋ ምንም አይሁን ይላል መጽሃፉ?

ወሰን፡- እምዬ ምኒሊክ የለም፤ አይሰማም ተብሎ፤ ማንም ተነስቶ ንጉስህ ነኝ ቢል ከቶ ይሆናል?.

ገ/ስላሴ፡- እምነት የማተብ ቃል ዝም ብሎ ይጠፋል?!...ቃል ዋስትና መሆኑም ያበቃል! ሰው ከሰው ከእንግዲህ እንዴት ይተማመናል?

መርዕድ፡- አባታችን መጨነቅዎ...መልካም አባት የሚያረገው ነው። የዚህ የክርስቲያን ህዝብ አባት በመሆንዎ፤ ምንድነው የአሳሰበዎት? አሳቡ ይንገሩን እንዳንከነንብዎት።

ማቴዎስ፡- ለእኔማ ይሄ የተለየ ነው። ደሞ ደርሰዉ ግልፍ ቁጥት ሰለሚሉ..አላዉቅም አሁን ምን እንደሚሉ። ነገሩ የቤተሰብ ጉዳይ ነው። በዘዴና በብልሃት መያዝ የሚገባው። በእርጋታ ልናልፍ የሚገባዉ ብርቱ ፈተና ነው። ይሄ የቤተሰብ ምስጢር ነው። የእናተም ስጋት ችግር እዉነትና ተገቢ ቢሆንም፤ እንዲሁ እውነት ይዘናል ተብሎ ሰዉ ከሌላዉ አይላተምም።

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እና ዝም ይላል ሀብት ንብረቱን ተነጥቆ? መጋጨት መላተም ፈርቶ? እዉነትን ጥሎ እንደ ተራ እንቶፈንቶ?

ማቴዎስ፡-'መከራና ጦርነትን ከሚያመጣ እዉነት እርቅ ያለዉ ውሸት ይበልጣል ይባላል። መቼም በአባትነቴ...ለኔ ሰላም ነች ቤቴ። ሰላም የሌላት እውነት በመጠሃፉም.... ዝንተ ሰማይ ለከ...

ኃ/ጊዎርጊስ፡- ብጡነትዎ እንዴት ነው የሚሉት? አንዱ ቤተሰብ ሌላውን ቤተሰብ ይጉዳው ይንጠቀው ይላል መጣፉ? አንዱ ያኮርፋል ዱር ይገባል ተብሎ ተፈርቶ የተነጠቀዉ አፉን ይዞ ይቀመጥ ነው የሚሉት? እርቅ የሚያመጣ ውሸት... ለመሆኑ እድሜው ስንት ነው? ዉሸቱ የታወቀ ለታ ሀፍረት ነዉ!

ተሰማ፡- ቅዱስ መጥሃፉ አንዱን ከአንዱ ለይቶ ያዳላል? ከአልጋ ወራሹ ከልጅ እያሱ ተነጥቆ ለእተጌ ይሰጥ ይላል??

ማቴዎስ፡- የለም አይልም መጥሃፉ አያዳላም። ወንጌሉ ሁሉን እኩል ያያል።

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እንግዲያው ይበሉ ይፈጥሙልን። ቃለ ወንጌሉን ያስፈጥሙልን።

ሁሉም፡- ቃለ-ወንጌሉን ያስፈጥሙልን

ማቴዎስ፡- (ፋታ)...ይሁን እንዳላችሁት አደርጋለሁ። ከእናንተም ትግስትን እሻለሁ..... የአብርሃምን እምነት፤ የያቆብን ትግስት እንዲሰጣችሁ፤ በውሳኔአችሁ የፈጣሪ አምላክን በረከት እንዲታከልበት እለምናለሁ። እቴጌ ጣይቱም ሳውቃቸው የማርያም ልጅ የክርስቲያን እናት ናቸው። በግል ጠባያችን ሁለታችን ባንስማማ በፈጣሪ ዘንድ ቃላችን አንድ ነዉ። (ሌሎቹ መሰላቸታቸው ያስታውቃል)...ሁሉን ነገር በዘዴ ካልናቸው እምቢ አያውቁም ከአንደበታቸው። ቃላችሁን አሰምቼ ሳበቃ፤ እዚሁ እንዲመጡ እና እናንተ በአላችሁበት የእህት ወንድም ምክክር እና ፍቅር ያልተጓደለበት ምክክር እንድታረጉ አደራዬ ነዉ። ከእናንተ የምፈልገው ትግስትን ብቻ ነው። ጭራሽ ጠብ እና ደም መፋሰስ መኖር የለበትም። የአንድም ባላገር ነፍስም ቢሆን የወገን ደም መፍሰስ እንደማይኖርበት ቃል እንደትገቡልኝ እሻለሁ። እኔም ፈቃዳችሁን እፈጽማለሁ...(ሁሉም በዙሪያቸዉ ተንበርክከው እጃቸዉን ወደ

መስቀሉን ይዘረጋሉ።)

ሁሉም፡- ደም አንፋሰስም!

ማቴዎስ፡- (በድጋሚ መስቀል ያሳልማሉ) እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

ሁሉም፡- አሜን አሜን...(ማቴዎስ ከእጨጌዉ ጋር ይወጣሉ)...(ፋታ)

መርዕድ፡- መቼም ፈጣሪ አምላክ ይቅር ይለናል። ከእቴጌ ጋር ሳያኮራርፈን፤ ከእተጌ ጋር እንዴት እንደምንተያይ....ያ ጀግንነታቸው፤ደግ አሳቢነታቸው...የቤተ ክህነት እናትነታቸው፤ ይሄ አሁን በአማላጅ የላክንባቸውን እሺ ቢሉን...ሰላም ወረደልን።

ተሰማ፡- ደጃች መርዕድ...ምንም ክፉ ምግባር አልፈጸምንም። ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ ቅድም እንዳሉት፤ የኛ ጥያቄ የመንግስት ስርዓት በደንቡና በወጉ እንዲቀጥል....ይሄ ዘመን በተለወጠ ወይ አንድ መሪ በሸሸ ወይም በደከመ በሞተ በታመመ ቁጥር እንደገና ህዝቡን የሚያውክ ነገር ከመፍጠር፤ ይልቅ በደንብ በስርዓቱ ይካሄድ ብለን ማለታችን፤ የሚያስኮንን አይደለም ተግባራችን።

ወሰን፡- መንግስት በተለወጠ ጊዜ ሁሉ ህዝቡ እንደ ቅቤ መናጥ መቅለጥ የለበትም። መንግስት ሳይሆን መቀየር ያለበት የሚያገለግሉት ባላባት ሎሌዎች ናቸው እንጂ በስርዓቱ የተገነባው መዋቅርና ወግ ሁሉ መነቃቀል የለበትም።

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እርግጥ ነው...የመንግስት ስርዓቱ ስርዓት የሚሆነው ሁላችንም ስናከብረው። ሁሉም ስርአቱን ጠብቆ በወጉ ሲፈጸም ሁሉም ድርሻና ግዴታውን ቢረዳ ምን ገዶ! ዳሩ እሳቸው ከስርአቱ ወጥተን ጋሻ ጃግሬዎቻቸውን አስታጥቀው የራሳቸውን ዘመድ አዝማዱ ሹመው፡ የተቀረዉን አባርረው የጎንዮሽ መንግስት ልፍጠር ካሉ፤ ለእሳቸው የገባሁትን መሃላዬን አነሳለሁ። ለጌታዬ ለምኒሊክ የሰጠሁትን ቃል ማንም አይለውጥብኝም። (በጃቸው ወደ ውስጥ እልፍኝ ያሳያሉ) ስተት ብዬ ገብቼ ነው የምነግራቸው። አማላጅ መላካችን ከወጉ ከስርአታችን ሳንወጣ የጨዋን ደንብ ማክበራችንን ያመለክታል። እምቢ ብለው ካሉ ግን...

መርዕድ፡-እስቲ በረድ በሉ...እርጋታ መልካም ነው...

ገ/ስላሴ፡- እርጋታ አሚመጣው...ለልጆቻችን የመልካም ምግባር ተምሳሌትን ለማሳለፍ ስንልችል ብቻ ነዉ። አለበለዚያ ባርነት ነዉ የምናስተምራቸዉ። (ጣሴ ይገባ እና እጅ ይነሳል)

ተሰማ፡- ብርቱ ስነበትክ ጣሴ?

ጣሴ፡- ( እጅ ይነሳል)..ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ...ደህና ነኝ እስከ አሁን....(ጣቱን ይቆጥራል)...አምስት፡ አራት ሶስት ሁለት አንድ!

ድምጾች፡ (በድንገት ጫጫታ ሁካታ ከውስጥ ይሰማል።) ዉጣ...ውጣ...ውጣ...ውጣ! ሰላቢ የአረብ ውሻ! (ጫጫታ ኡኡታ ይሰማል /ፋታ/..ሁሉም አሳልፈዉ ወደ ዉጭ ይመለከታሉ።

ጣሴ፡- (ተመልካች)...ብያችኋለሁ..ከሁለቱ ጠሎቶች አንዱ ነዉ መልስ የሚያገኘዉ። ሁለት ጠሎተኛ ተፋላሚዎች ተደባድበዉ ሲጨርሱ አንዱ ነዉ ከላይ ሆኖ የሚገኘዉ። አባታችን በእቴጌ ሰዎች ተደብድበዉ ነፍሳቸዉን ይዘዉ አምልጠዋል። እንደገና ጠሎት የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ነዉ።

ሁሉም፡- ምን ተፈጠረ? ምን መጣ? (አባ ማቴዎስ ቆባቸውን እያጠለቁ ...ትንሽ ተሸብረዉ ይገባሉ።)...ምነው ሰብአት ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ...አባቴ ተርፈዋል።...(ጣሴ ሸማቸዉን ቆባቸዉን ያስተካክላል)

መርዕድ፡- ምነው ፊጣሪዬ ይሄንን ሳታሳይ በገደልከኝ!!. ከአድዋ የመለስከኝ ይሄንን ጉድ ልታሳየኝ ነው?? ኧረ ምን አልኩህ ፈጣሪዬ....

ማቴዎስ፡- (መሃል ስቴጅ ተደግፈው ይቀመጣሉ። በረጅሙ ይተነፍሳሉ)...ቤተስኪያን እንደገባች ውሻ በደንጊያና...የእቴጌ አሽከሮች አልባሾቹ ሳይቀሩ በመጥረጊያ ....(ይተነፍሳሉ) ሳዕለን ቅድስት...ማንም ሰው ‹ውሻ አረብ› ብሎኝ አያውቅም። ስብአተ....(ያነበንባሉ) (ሲኞር ፓንታሎኒ ይገባል)

ፓንታሎኒ፡- (እጅ ይነሳል ለፊታውራሪ) (ማቴዎስን ያያል)...ምነው ምን ሆኑ??

ወሰን፡- እተጌ ጣይቱ አስደበደቧቸው።

ፓንቶሎኒ፡- ሳንታማርያ!...እኛ በሰለጠነው አለም ከሁሉም በላይ የእግዚያብሄርን አገልጋዮችን እናከብራለን። በሰለጠነዉ አገር በሮማ ውስጥ...

ፊታውራሪ፡- ኧረ እኛም እናከብር ነበር...እሱስ።

መርዕድ፡- ስብአት ለመንፈስ ቅዱስ (ያማትባሉ)...

ፓንታሎኒ፡- አሁን ይሄን የምመለከተውን፡ የሰለጠነው አለም መሪዎች ቢሰሙት.... ሳንታማሪያ!! ይቺ አገር ‹ያልሰለጠነች አገር ናት› በማለት የክርስቲያን ጦር ሊያዘምቱባት ይችላሉ› ተሳሳትኩ እንዴ? (ፊታዉራሪ ያዩታል)...ህዝቧም ደደብ ኋላቀር፤ ሪባስቶ!... ምን ቢማር ፊደል ቢቆጥር...ተመልሶ ካፊር!! ነው የሚሉት። ምንም የማይገባው ሪባስቶ ቀርቀሮ ራስ ነው የተሰበሰበው ብለው ነው የሚያስቡት...ማማሚያ...ቴስታ ጋሊና! ሪባስቶኒ!!!...የገናናዉ የሮማ መንግስት ቢሰማዉ ጦርነት ነዉ የሚሆነዉ!

ገ/ስላሴ፡- ጌታ ሲኞር ባንቶሎኒ... እዚህም የምኒሊክ ጦር አለ። ለማተቡ የሚሞት፡ ለእምነቱ ቀናዔ...ለቤተ ክህነት የተገዛ ለአገሩ ከገባው ቃልኪዳን እምነቷ፡ ከቶ የማያፈገፍግ አንገቱን ለካራ ከመስጠት ወደ ኋላ የማይል። የእሱን እምነት ከናቁት የእምዬ ምኒሊክን ቃል ጥለው ካዋረዱት....

ፓንታሎኒ፡- ምኒሊክ ታሟል ነዉ ነበር የሰማሁት...ምንድነዉ ታዲያ ረብሻ..ልጅ እያሱ የታሉ?

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ሁሉም ደህና ናቸዉ..እቴጌን ነዉ ትንሽ ያመማቸዉ።

ማቴዎስ፡- በክብር በእልፍኛቸዉ በግቢያቸዉ ብሄድ እንዲህ ክብረ-ነክ ተግባር ከፈፀሙ ...ዛሬዉኑ እዚች መጥተዉ የሚነገራቸዉን ካልተቀበሉ...ከእንግዲህ በኋላ ሙላው አገር ለተጌይቱ እንዳይታዘዝ እገዝታለሁ...(ጣሴ ፈጠን ብሎ ይወጣል)...በእናንተም በጦር መሪዎቹ በእንደራሴዎቹ በወኪሎቹ ላይ የጣልኩትን ግዝት መሃላም አነሳለሁ።

ሁሉም፡- ይፍቱን...ይፍቱን አባቴ ( በሰልፍ ዙሪያውን ይከቧቸዋል፤ ይሳለማሉ።)

ማቴዎስ፡- እጨጌውንም እምቢ ብለዉ..እተጌ ጣይቱ ዛሬውኑ እዚህ ችሎት መጥተው የእምዬ ምኒሊክን ኑዛዜ ተቀብለው፤ እሺ ብለው በአስታማሚነታቸዉ ብቻ ካልተቀመጡ። ልመናችሁን ረግጠዉ ከወጡ፤ በእናንተ ላይ ያለውን ግዝት አንስቻለሁ! ያሻችሁን ሁሉ እባርካለሁ! (ማቴዎስ ከደጃች ወሰን ጋር በፍጥነት ይወጣሉ...)

የቀሩት፡- አሜን አባቴ፤ አሜን...አሜን አባቴ...

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ጦርነት አበቃ ብለን ነበር...ካልሆነ እንግዲህ ትጥቃችንን ላንፈታ ነዉ ማለት ነዉ።...ይልቅ ከበጅሮንድ ዘንድ ጉዳይ ስላለኝ ሳይረፍድ ልሂድላቸዉ።..እቴጌ

እሺ ብለዉ ከመጡ አስልኩብኝ፡፡ አሻፈረኝ ካሉም ጦር ጋሻችንን እናነሳለን.. (በእቅፍ ሁሉንም ይሰናበታሉ...ፋታ)

መርዕድ፡- ይኸው እንግዲህ ለልጅ እያሱም ይነገራቸው፡፡

ተሰማ፡- ልጅ እያሱንማ ..ያዉ ቀስ እየተባለ እናለማምዳቸዋለን፡፡

ደምሰዉ፡- ቀስ እያልን አገር እያያዝ ፍርድ አሰጣጥን እናለማምዳቸዋለን፡፡ አያታቸዉ እምዬ ምኒሊክ የፈቀደዉን በጅምር የቀረዉን እንጨርሳለን፡፡

ፓንቶሊኒ፡- በእውነቱ በዚች የተቀደሰች አገር ያላችሁ ሰዎች ሰነ ስርዓታችሁ፣ ለሃይማኖታችሁ ያላችሁ ቀንዓዊ አመለካከት ያስገርመኛል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለመሪዎች ለነገስታት የምታሳዩት ክበሬታ፣ ለእውቀትና ስልጣኔ ያላችሁ ፍቅር የተለየ እና የሚደነቅ ነዉ፡፡ ማማማሪያ ስማርት ናችሁ!!...(ትርምስ ይሰማና እቴጌ ከቢትወደድ መንገሻ ጋር ታጅበው ሲገቡ ሁሉም በክብር እጅ ይነሳሉ፡፡ እቴጌ ተገላምጠው ችሎት ወንበር ላይ ይቀመጣሉ፡፡)

ጣይቱ፡- ስኞር ባንቶሎኒ ከዚህ ምን አመጣህ!

ፓንቶሎኒ፡- (ተነስቶ ይነሳል በድጋሚ)...ክብርት እመቤት ንግስት ጣይቱ፣ ከገናናው የጣልያን መንግስት መልካም ሰላምታ ሳደርስና...

ጣይቱ፡- የገናናዉ ጣልያን ሰላምታንማ ሰማነዉ፡፡ ወይስ ለክቡራን ባላባት የሚሆን መጫወቻ... እሽክርክሪት ነገር አገኘህ እንዴ?... (ፓንታሎኒ ሊናገር ይቃጣል)...በል ይሄ የቤተሰብ ጭውውት ምክክር ስለሆነ ያንተን ቀንሰላ የሚያገባው ጉዳይ አይደለም፡፡ የውስጥ ጉዳያችንን ስለምንመካከር...ራስህን እንድታገል ያሁን ( እጅ ነስቶ ይወጣል...ከመድረኩ ከወጣ በሁዋላ ጣሴ ዱላዉን እያምዘገዘገ ከአንዱ በኩል ወጥቶ ፓንታሎኒን እንደሚያባርር በወጣበት ይከተለዋል... (ፋታ).../..ብርቱ ጉዳይ አለ፡ ስለተባለኩኝ አጨጌውንም አክብሬ መጥቻለሁ፡፡ የምትሉትን እሰማለሁ፡፡

ተሰማ፡- እርስዎ እመቤታችን ከዚህ በመምጣትዎ ተደስተናል፡

ጣይቱ፡-እውነት?...ይገርማል፡፡ የእርስዎን ደስታ ለመስማት በመቻሌም ተደስቻለሁ፡፡ ሁሌም አዘንተኛ ነበር የሚመስሉኝ፡፡

ተሰማ፡- ለምን ብዬ አዝናለሁ...ምኒሊክ የሰጠንን ይዘን ስለምንሄድ አዘንስ የለኝም፡፡

ጣይቱ፡- አሁን የሽሙጡን ትተው ለምን ዋናውን ጉዳይ አይነግሩኝም፡፡ አይንሽን ለምን አየነው...በዚህ ችሎት ዝር አትበይበት ነው ምትሉኝ?

ተሰማ፡- ኧረ እንደሱም አልወጣን!

ጣይቱ፡- ታዲያ ምንድነው የምትሉኝ?

ደምሰዉ፡- እናታችን እቴጌ ጣይቱ...እኛ ያልነው ለጌታችን ለእምዬ ምኒሊክ የሚያደርጉላቸው እንክብካቤና እርዳታ ታክሎበት በመንግስት ስራ ላይ ብዙ በመቆየት ጫናው እንዳይበዛብዎት...ለራስ ተሰማ ናደው የመንግስቱን ስራ በመተው፣ እንደ ጌታዬ ኑዛዜ እንደ ፍቃዱ እንዲሆን ብለን ነው፡፡ ለልጅ እያሱ ሞግዚት የመንግስቱን ስራ እንዲተውልን ነው ልመናችን፡፡

ገ/ስላሴ፡- ልጅ እያሱም በመንግስት ስራ እውቀት እንዲያዳብሩ...መቼም ከእንግዲህ ልጅ እየሆኑ አይመጡም፡፡ ‹እኔ ነኝ የማውቅልህ› ካሏቸውም ሁሌም ልጅ ሆነው በራሳቸው መቆምን ፈርተው፣ ካለ ረዳት ድጋፍ በራሳቸው መቆም እንዳይችሉ ሆነው እንዳይቀሩብን በመፍራትም ጭምር ነው፡፡ አሁን... ይቺ የምትበረው ቢራቢሮ የሚሉዋት ትንሽ ፍጡር...‹በራስዋ ተፍጨርጭራ ተእንቁላሉዋ ራሷን

በራሷ ገፍታ ስትወጣ...ይሄ መፍጨርጨሯ፣መፈራገጥዋ፣ ክንፏ ውስጥ የሚፈስገውን ደምና ፈሳሽ ይሞላላታል። ገፍታ ጨርሳ ስትወጣም ተነስታ መብረር ትችላለች። ያቺ ሳይሆን ግን፣ ሌላው ሰው ከእንጭጩ፣ ከእንቁላሉ ውስጥ ሰብሮ ፈልቅቆ ቢያወጣት...ክንፏ ውስጥ መግባት የነበረበት ደምና ፈሳሽ ሳይገባ ይቀርና፣ መብረር የማትችል፣ በምድር ብቻ የምትድህ ድውይ ፍጡር ትሆናለች› ብሎ አንድ ገበሬ ድሮ አጫውቶኝ ነበር። እናም አልጋ ወራሹ በርትተው መብረር እንዲችሉ ራሳቸውን ችለው እንዲቆሙ መፍጨርጨር ልናስተምራቸዉ ይገባል።

ጣይቱ፡- ደጃች ገብረ ስላሴ...እኔም የሰማሁትን ልንገርዎት። የክብት እረኛ ሁሌም እረኛ ነው። አነጋገር የማያውቅ ጨዋነት የሚጎድለው የበግ እረኛ፣ ካባ ቢያጠልቅ ቢያጌጥ፣ ቢንቆጠቆጥ...ሁሌም ያው... ያልታረመ እረኛ ነው። ስርዓት የለቀቀ ጨዋ ያልሆነ የበግ እረኛ እንደሚናገረው ነው....‹ብራቢሮ ምንጥሴ›...ምንድነው ይሄን አይነት የተዘባረቀ አማርኛ? የእረኞች ጨዋታ ነው የሚመስለው።

ገ/ስላሴ፡- ልክ ነዎት እቴጌ። እድሜ ለእምዬ ለምኒሊክ ሁላችንንም የበግ እረኛ ሆነን እንዳንቀር ካባ ለባሽ ባላባት አድርገውናል። እናም ዛሬ ምስጋናው አይጓደልበትና ከበግ ሌላ የሰዎች ጠባቂ እረኛ አድርጎናል።

ደምሰዉ፡- እተጌ መቼም የደጃች ገብረ ስላሴ አነጋገር....እርስዎ የጌታዬ ጠባቂ የጤናው መድህን አገልጋይ በመሆንዎ ብዙ ጊዜዎን የኛን ጭቅጭቅ በመዳኘት እንዳያጠፉ ለጌታችን የሚያደርጉት እንክብካቤ እንዳይቀንስ ለራስ ተሰማ ናደው ሁሉንም ስራ ቢተውላቸውና በተሰጣቸው የባላደራነት፣ የምእዬ ምኒሊክን ኑዛዜ እንዲያስፈጽሙ አልጋወራሹንም ስርአት እና አስተዳደር እንዲያስተምሩ በማለት መቼም...

እቴጌ፡- (ራስ ተሰማን) ለመሆኑ እርስዎ በቀን በቀን ከስሬ መቶ ጠፍተው ነው?? ኸ?.. ዛሬ ይሄን አደረግሽ ተብዬ መላክተኛ የሚላክብኝ?....(ተሰማ ሊናገሩ ይቃጣሉ) ‹እርስዎ በመንግስት ስራ ከእኔ የተሻለ ልምድ አለዎት› ቢሉኝ አይደል መስራት ያቃተዎትን የሰራሁት? ለመሆኑ እርስዎ በአንዲት ጉዳይ ተገቢው ውሳኔና መልስ ሰጥተው ያውቃሉ? (ተሰማ ሊናገር ይቃጣል) ‹በርስዎ ያምራል› አልነበር እንዴ ሲሉኝ የቆዩት? ፍትህ ጥያቄ እንዳይጓደል መልካም መኩዋንንትና መሳፍንት አሰባስቤ ስራ ባሰራሁኝ፣ በተሲአት ጠሃይ ጨለመብን ያሉትን ተበዳዮች ፍትህ ባሰጠሁ፣ የራሷም ሰዎች ሰበሰበች› ትበሉኝ?... (ተነስተው ወደፊት በትካዜ ያመራሉ) ሊጠፋ ያለዉን አገር በአቃናሁኝ...የተደናገረውን ባላገር ባረጋጋሁኝ? እንዲህ ታረጉኝ?. እንደኛውኑ ጦር አሳምፃችሁ እንደ እሮጌ ቁና አውጥታችሁ ልትጥሉኝ?

ደምሰዉ፡- እመቤታችን መቼም እርግት ብለዉ ከተመለከቱት..ጥያቄ ልመናችን የእምዬ ምኒሊክ ኑዛዜ ቃሉ ይከበር ለማለት እንጂ...

እቴጌ፡- ምንድነዉ ቃሉ ይከበር ማለት? አገሩ ይፍረስ ብሏል..በመከራ በደም በአጥንት የተገነባዉ አገር ይፍረስ ብሏል?

ደምሰዉ፡- እንደሱ አይለም የምለዉ...በርጋታ ካልተነጋገርን መፍትሄ አናገኝም

እቴጌ፡- አነጋገርም አታዉቂም ሊሉኝ ነዉ?

ደምሰዉ፡- አባባሌ..

መንገሻ፡- እኔ መቼም ደጃች ደምሰዉ ነሲቡ..እንዲህ ይላሉ ብዬ በዉኔም በህልሜም አስቤዉ አላዉቅም...ከወንዱ ጎን ለጎን በአድዋ በዉጫሌ የተዋጉትን ጀግና እናታችን እንዲህ ክብር በጎደለዉ ከፍ ዝቅ አድርጎ መናገር...መቼም መቼም...

ደምሰዉ፡- ቢትወደድ...ነገርን ከስሩ ዉሀን ከጥሩ እንደሚሉት...ሳያጣሩ መሀል መግባት

ነገር ለማበላሸት ካልሆነ...

መንገሻ፡- ማነዉ ነገር ያበላሸዉ?!...(በንዴት ይፋጠጣሉ)

ደምሰዉ፡- እርስዎ አሁን በማያዉቁት ገብተዉ የጠራዉን ለማደፍረስ ካልሆነ..

መንገሻ፡- ማነዉ የጠራዉን የሚያደፈርሰዉ?!...ጋጠ ወጥ ስነ ስርአት የሌለዉ ሰዉ...(ጡጫ ይሰናዘራሉ...መርእድ ቢትወደድን ገ/ስላሴ ሁለቱን ለየቅል ይይዛሉ...ይገላገላሉ፤ ሁለቱም ይሰነዝራሉ...ጣሴ ይገባል)

ጣሴ፡- ብዙ አላመሰጠኝም አይደል?..እርግጠኛ ነኝ ሁለቱም ሰዎች በጠሎታቸዉ ‹ጠላቴን ከፊቴ ጣለዉ› ብለዉ ነዉ በጧት የወጡት።

ጣይቱ፡- ይበቃል። ይበቃል።...በእኔ የተነሳ ችግር እንዲመጣ አልፈልግም። እዚህ እንዳናይሽ ከሆነ የምትሉኝ...ይገዬ ሄጄ እንዳስታምመዉ ፍቀዱልኝ።

ገ/ስላሴ፡- የት ይዘዋቸዉ ሊሄዱ እመቤቴ?

ጣይቱ፡- ይገዉ ልሂዳ ወደ ጎንደር፤ የጁም ብወስደዉ አየሩ ይስማማዋል..እንደበቱን ወይ ይፈታዋል።

ገ/ስላሴ፡- ጎንደር ወይ የጁ?? (የሚያስቡ ይመስላል)...

ጣይቱ፡- ወይ እዚህ ቡልጋ፤ ካልሆነም ጥሩ ጠበል ካለበት ወደ ደብረሊባኖስ ብወስደዉ...ማን ያዉቃል...ተነስቶ ይቆም ይሆናል...

ገ/ስላሴ፡- (መርእድን እና ነሲቡን በሹክታ) ጎንደር የጁ..ቡልጋ?

ጣሴ፡- ይሄ ነገር አለዉ አደጋ!..እቴጌ ጎንደር ወይ የጁ ከገቡማ..ከራስ ወሌ ጋር የጉግሳን ጦር ይዘዉ ከተፍ ሊሉ ነዉ፤..ምኒሊክንም ‹የጦር አለቆቹ አሽቀንጥረዉ' ጣሉት› ነዉ የሚባለዉ..

መርዕድ፡- ለነገሩ አየሩ ደጋ ለጤና ተስማሚ ነዉ...

ጣሴ፡- እኚህ ሰዉዬ ተሸወዱ!

ገ/ስላሴ፡- ለደጋ ለንፋስ ለቅዝቃዜዉማ...እንጦጦ ነበር ጥሩ።

ጣሴ፡- እንጦጦማ ግዞት እስር ቤት ነዉ!

ተሰማ፡- እንደ እኔ እንደ እኔ...ምኒሊክ እዚሁ ከሞቀ አልጋቸዉ ይቀመጡ..በምን አቅማቸዉ ነዉ የሚጓዙት?...እዚሁ ሆነዉ የሚፈልጉትን ያድርጉላቸዉ..እርስዎም አይድከሙብን።

ጣይቱ፡,- ለእኔ ሰራተኞቼን ብቻ ይገዬ እንድሄድ ፍቀዱልኝ። እሱን በቃሬዛ እንዲይዙልኝ።

መንገሻ፡- ይሄ መቼም ትልቅ በደል ነው። ከበደል የከፋ ክህደት፤ ጌታዬ ምኒሊክ ታሞ ቢተኛ ካቀናው አገር፤ ከተቀመጠበት መንበር ለማስወጣት ማደምና መዶለት ...እንዲያዉ ምን ይላል ጭልጋ አንክበር፤ ወሎ በጌምድር የታመመ ንጉስ አገር ያቀና ስመ ጥር፤ የከበረ ጀግና ከቤተ-መንግስቱ ሲባረር፤ ዝም አይልም የሸዋ ባላገር! ቢሰማው ይህንን የክህደት ተግባር። የምኒሊክን የቁም ውርደት ሲሰደድ ካቀናው ቤት! የባለሚሎቹን ክህደት...ሲያባርሩት ከተኛበት!

ገ/ስላሴ፡- ቢትወደድ...ንግግርዎት መልካም አይደለም። ነገርን ዝም ብለዉ ሳያጣሩ ...አንዱን ከአንዱ ቢያላክሩ...የጅብ ችኩል ቀንድ ይነክሳል እንዲሉ...አይበጅም ለነገሩ...

መንገሻ፡- አይ...እኔን ጅብ አይበሉኝ...

ገ/ስላሴ፡- ጭራሽ ያልወጣኝን...ነገርን ከስር አጥርተው ተረድተው ሲያበቁ...እንዲሁ ካንድ ወገን ሆነው ቢያጎኑት...

መንገሻ፡- ነገር የሚያጎኑትስ እርስዎ!

ተሰማ፡- የለም ይበቃል...ክቡራን ነገር ማብረድ መልካም ነው፡፡ ስርዓት ለማስከበር ስርአት ማጥፋት የለብንም፡፡ አንዳችን በአንዳችን አምጠን፤ የፈጠርነውን ስርአት ምኒሊክ ያቀኑትን አገር አናፈርሰውም፡፡

ጣይቱ፡- እኔ ነኝ የዚህ ሁሉ ጠብ መነሻ፡፡ የባላባቱ መካሰሻ...ከእንግዲህ ፍቃዳችሁን ብቻ ነው የምጠብቀው፡፡ እምዬ ምኒሊክ ከእኔ ማንም አይለየውም፡፡ ጌታዬን ይገቬው ነው የምሄደው፡፡ ነፍሱ ከስጋው እስክትለይ ከኔ ዘንድ ነው የሚቆየው፡፡ ከአረፈም የተቀደሰውን አፈር እንዳቀምሰው...ልሂድ እንጂ ይገቬዉ...

መርዕድ፡- እቴጌ ጣይቱ...እርስዎም ጃንሆይም አይንገላቱ ተባባልን እኮ

ጣይቱ፡- ታዲያ ምንድን ነበር ስትሉኝ የነበረው ነገሩ? አይንሽን አንየው መስሎኝ ንግግሩ...

ገ/ስላሴ፡- የለም እንደሱስ አላልንም!!...እኛ...የመንግስት ስራዉን ብቻ ለራስ ተሰማ ተዉላቸዉ ነዉ የምንለዉ፡፡

ጣይቱ፡- እና ከዚሁ ቤተ-መንግስት ኑሪ ነው የምትሉት? ...

ሁሉም፡-፡ አዎን! አዎን!...

ጣሴ፡- የመጀመሪያዉን ዙር እቴጌ ያሸነፉ መሰለኝ፡፡

ጣይቱ፡- እንግዲያው...አስቤ አውጥቼ አዉርጄ....ከፈጣሪዬ ተማክሬ...ውሳኔዬን ተሰምኑ እነግራችሁዋለሁ...(ሁሉም እጅ ይነሳሉ...እቴጌን ተከትልዉ መንገሻ ጣሴ እና ባለሟሎቻቸው ይወጣሉ፡፡)....(ፋታ)

ገ/ስላሴ፡- ከእንግዲህ ምንም ባለጉዳይ ወደ ቤተ-መንግስት መጥቶ እተጌይቱን እንዳያነጋግር ይሁን፡፡ ከባላደራው ከሞግዚቱ ከራስ ተሰማ ፈቃድ ውጪ ምንም ጉዳይ ሹም ሽር እንዳይፈፀም፡፡

ወሰን፡- ከሀኪሞቹ በስተቀር በዚህ ማንም እንዳያልፍ ይሁን፡፡ ከአልጋወራሹ አቤቶ ልጅ እያሱ ትእዛዝ ውጪ ማንም ጉዳይ እንዳይፈጸም፡፡ (ማቴዎስ ደጃች ወሰን እና ፊታዉራሪ ኃ/ጊዮርጊስ ጋር ይገባሉ)

ማቴዎስ፡- እተጌ መምጣታቸውን ሰማሁ፡፡..(ጣሴ ገብቶ ይሳለማል)...

ተሰማ፡- አዎን መጡ፡፡ከእንግዲህ በመንግስት ስርዓት እንዳይገቡ ተነግሯቸው ተስማምተዋል፡፡

ኃ/ጊዎርጊስ፡- ጎሽ! ከእንግዲህ በምኒሊክ ኑዛዜ መሰረት...አቤቱ ልጅ እያሱ ፈቅደው ጎልምሰው እስኪነግሱ ድረስ፤ የዘውድ ተረካቢ ንጉስ ነገስት በመሆናቸው ከእሳቸው ፈቃድ ውጪ የተፈጸመ የምዬ ምኒሊክ ኑዛዜ የተጋፋ አማጺ ስለሚሆን በጥኑ ቅጣት ይቀጣ!!...

ተሰማ፡- በአገሩ ያሉት መኩዋንንት መሳፍንት ዳኞች ራስ ፊታውራሪዎች ከእንግዲህ ጉዳያቸዉን ሁሉ በልጅ እያሱ ስምና ማህተም የሚሰጣቸውን ብቻ ይፈጽማሉ፤ ያስፈጽማሉ ተብሎ አዋጅ ትእዛዙ ይድረሳቸው፡፡ ( ጣሴ ይጽፋል፡፡)

ገ/ስላሴ፡- የተሻሩትም ከግዛታቸው ተነስተው እንዲመለሱ ባስቸኳይ ይላክባቸው፡፡

ወሰን፡- ለደጃች ተፈሪ መኮንን...ሐረርን ፈቅደንለታል፡፡

ተሰማ፡- አዎ በእሱማ ተስማማን፡፡

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ልጁን አልጋወራሹን የሚክድ እምዬ ምኒሊክን ኑዛዜ የናቀ...አይቀጡ ቅጣት ይደርስበታል፡፡

ማቲዎስ፡- (መስቀላቸውን ወደ ላይ ያነሳሉ) ለአቤቱ ለልጅ እያሱ የማይገዛ፣ ስልጣናቸውን የተቃወመ ያመፀ ያሳመፀ ውጉዝ ከመአርዬስ! ነፍሱ እስከ ሰባት ቤቱ የተረገመች ትሁን!

ሁሉም፡- አሜን!

ማቴዎስ፡- በህይወቱም ከስጋው ደሙ እንዳይካፈል! ስጋውም የረከሰ ሲሞትም ለሬሳው ፍታት የማያገኝ ይሁን!!

ሁሉም፡- አሜን!...ይፍቱኝ....(ሁሪያቸው ከበው ያጎነብሳሉ፣ እሳቸዉ መስቀላቸውን ሽቅብ ይዘው በለሆሳስ ይጸልያሉ...) አቦክሙ ሰማያዊ ዘትፈቅዱ፣ ዘእንበለ.. ./ፋታ/...አሜን!

ሁሉም፡- አሜን!

ደምሰዉ፡-(እየተንጎራደዱ ይፎክራሉ..ሌሎቹም ወዲህ ወዲያ እያሉ ያበረታታሉ..ድራም ሮል..)..ዘራፍ የምኒሊክ አሽከር! ዘራፍ ዘራፍ! የእያሱ ባሪያ...የእያሱ አሽከር!.. ግንባሩን ለጦር..ልቡን ለምንሽር...በዱር በገደል ያልተደፈረ...እያሱን የደፈረ...ከደጅ አደረ!...የእምዬን ኑዛዜ የቀየረ...እግሩ ተሰበረ! በለዉ!..በለዉ! ...መትረዉ አንገቱን እግሩን ድገመዉ!...ካልተቀመጠ ጉድጓድ ቤቱ ነዉ! ..በለዉ!..በለዉ! ዘራፍ የእያሱ አሽከር!..ዘራፍ! ዘራፍ!..( ሙዚቃዉ ከበሮዉ ማበረታታቱ..እንደቀለጠ...መብራት በዝግታ ይጠፋል፡፡)

## ትዕይንት 2

መብራት በዝግታ በቤተ-መንግስት ችሎት ሲበራ ልጅ እያሱ ከትልቁ ወንበር ስር ባለች በርጩማ ላይ ተቀምጠው የውጪ አገር ጋዜጣ ሲመለከቱ ይታያል፡፡ ጥላሁንም አብሮ አለ፡፡)

ጥላሁን፡- እኔ እንጃ...ብቻ የሚቻል አይመስለኝም....

እያሱ፡-አይቻልም አትበለኝ...ይቻላል፡፡ ወግ ባህል ማለት አብሮ በመኖር የሚፈጠር እንጂ በደም ያለ ፈሳሽ ነገር አይደለም፡፡ መሞከር ያስፈልጋል ካሰቡት ለመድረስ፡፡

ጥላሁን፡- እንዳልከው ከወግ ከልማድ ለመላቀቅ መስዋዕትነት እርአያነት ይጠይቃል፡፡ የኔ ሃሳብ ግን ብዙ ጊዜ ይፈልጋል ባይ ነኝ፡፡ አንዳንዱ ጉዳይ ጊዜውም አይደለም፡፡...አሁን የሚናወራው ምናልባት ከመቶ ዓመት በኃላ ተራ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ዛሬ ግን አስደንጋጭ ነው የሚሆነው፡፡

እያሱ፡- (ከጋዜጣው አይኑን ሳይነቅል)...ጋንዲ የህንድን ህዝብ፣ ከእንግሊዝ ያለ ምንም መስዋዕትነት እንዲሁ በኩርፊያ መሰል አድማ ብቻ ነጻ አወጣዋለሁ ማለቱ የማይቻል ነው ትላለህ? የእንግሊዝ ጥንካሬና ብልሃትን አልተረዳም ብለህ ታስባለህ? ጊዜ ከመረጠማ መቼ ያረገዋል?...ይልቅስ ቱርክ ነው በቅርቡ ተስፋ ያለው አገር፡፡ ድንበር ወሰናቸውን አስከብረው የጋራ ማንነት እየፈጠሩ ናቸው፡፡ (ይጠቁማል ጋዜጣውን)...‹የቱርክ ወጣቶች ከኦቶማን የጭቆና አገዛዝ ወጥተው ህዝባቸውን የአዲስ ፍትሐዊ ስርዓት ተጠቃሚ ለማድረግ በአንድነት እየሰሩ ነው›

በርግጥ ቱርኮች ብሩህ ተስፋ አሳቸው፡፡

ጥላሁን፡ አንድ ነዋ ሃይማኖታቸው፡፡ ብዙ የሚለያይ ባህል ቋንቋ ምናምን የለም በመሄላቸው፡፡ እንደኛ ብዙ ትርምስ የለውም ድንበራቸው፡፡ የኛ ገና ተጋግሮ ያላለቀ እንጀራ ነዉ፡፡ ገሚሱ ጎሳ ወንድም ዘመዱ ገና ከዉጭ ከጎረቤት አገር፤ ከድንበር ካርታ ዉጭ ነዉ፡፡

እያሱ፡- እኮ ማነዉ ያንን ድንበር ያሰመረዉ?...(ይነሳል)...ቀዳዳዉን እንደፍነዋለን፡፡ ሶማሌን ከጣለያን ነጥቀን ከኛ ሶማሌ ጋር እንቀላቅለዋለን፡፡ ሱዳን ያሉት ባሮችም ከወንድሞቻቸዉ፤ ጂንካ አሶሳ ካሉት የጋምቤላ ሰዎች ጋር እንቀላቅለዋለን፡፡ ከዛ በሁዋላ እንደ ባህል ልማዳቸዉ እየኖሩ የጋራ የሆነችዉን አገራችንን እናለማለን፡፡ በጣም ሰፊ አገር ነዉ የሚኖረን፡፡ ገና መረብን ተሻግረን ‹ኤርትራ› ብለዉ የሰየሙትን አገር እናስመልሳለን፡፡

ጥላሁን፡- ሀሳቡ አይከፋም...ግን ዉህደቱ እንዲሁ ግዛት ለማስፋት፤ገባር ለማበራከት ከሆነ ሁሌም ከጦርነት ነፃ አይሆንም፡፡ ብሶት የሚፈጥረዉ ትግል...

እያሱ፡- ጥላሁን..እሱን ተነጋገርንበት...አንዱ የበላይ ሌላዉ የበታች ከሆነ እና አንዱ አሰልጣኝ ሌላዉ ስልጠና የሚያስፈልገዉ መሀይም ብለን ከአልን..ብጥብጡን አንዘልቀዉም፡፡ ከጣልያን ጋር ጦርነት የተማዘዝነዉ..ጣልያን ከበላይ ልሁን እና ‹ይሄን ያልሰለጠነ ህዝብ ላሰልጥነዉ› ብሎ ቢል አይደል??...እንደ ባህሉ እንደ አገሩ እንዲያድር እናደርገዋለን...ራሱን በራሱ እንዲያስተዳድር ከአደረግነዉ..ዛሬ በምኒሊክ ጦር ያዘነ የተቀየመዉ ሳይቀር የጋራ የሆነች አገር ለመመስረት የምናደርገዉን ጥረት ያግዘናል፡፡ ፈቅዶ ከማህበራችን ይገባል፡፡ ጣልያን በምስራቅ እና በሰሜን፤እንግሊዝ በደቡብ እና በምዕራብ የሚሸርበዉን ሴራ ዋጋ እናሳጣዋለን፡፡

ጥላሁን፡- ሀሳቡ ጥሩ ነዉ..ግን እንግዲህ ድሀ በበዛበት አገር ብዙ አርቆ ማሰቡም ችግር ይኖረዋል፡፡ በድሀ አገር...

እያሱ፡- አንተ ደግሞ ድህነትን ለምን እንደ...ለምን እንደ በሽታ እንደምታየዉ አይገባኝም

ጥላሁን፡- እሱማ በሽታ ነዉ፡፡

እያሱ፡- በጭራሽ...እዚህ ጋር ተሳስተሃል፡፡ ድህነት በሽታ ሳይሆን፤ የኤኮኖሚ ፍትህ ሲሰፍን ሁሉም ለድካሙ ተገቢዉን ዋጋ ሲያገኝ የሚጠፋ ነገር ነዉ፡፡

ጥላሁን፡- አይመስለኝም፡፡ ድህነት በሽታ ነዉ፡፡ የአእምሮ በሽታ፡፡ ምን ቢያገኝ ቢደላዉ፤በድህነት ያደገ ነፍሱ የዛገ ነዉ...

እያሱ፡- ጥላሁን???

ጥላሁን፡- ከአምሮዉ የአደገበትን የድህነት ፍርሃት ማዉጣት ስለማይችል..ፍርሀቱ ለራሱም ለሌሎችም አደገኛ ነዉ፡፡ ድንገት በትንሽ ነገር ነዉ እብድ የሚሆነዉ፡፡

እያሱ፡- ጥላሁን...ይሄ ንግግርህ ጭራሽ መሰረት የሌለዉ ነዉ፡፡ እንግዲያዉ በድሃዉ አገር ሁሉ ያለዉ ችግረኛ የአእምሮ በሽተኛ ከሆነ፤ መፍትሄ ማግኘቱም አዳጋች ሊሆን እኮ ነዉ?...ይልቁንስ ችግሩ...ለዘጠና ሰዉ የሚሆነዉ ቦታና ንብረት ለአንድ ሰዉ መሰጠቱ፤ የንብረት ክፍፍሉ ሁሉ አንዱ የዘጠናዉን ድርሻ መዉሰዱ ነዉ ክፉ ያረገዉ፡፡

ጥላሁን፡- ረጅም ጊዜ ይፈጃል፡፡ ያልከዉ የኤኮኖሚ ፍትህ ሰፍኖ..አዲስ ትዉልድ ያለ ፍርሀትና መራብ መታረዝ ማደግ ከቻለ..አሁን አንተ የምትለዉ ሁሉ ሊሳካ ይቻላል፡፡..አሁን ግን እብዱ ከጤነኛዉ ቁጥሩ ብዙ ነዉ፤ ፈተናዉ ብዙ ነዉ፡፡

እያሱ፡- (ይስቃል)...እብዱ ብዙ ነዉ??..

ጥላሁን፡- (ይስቃል)..እዉነቴን ነዉ፡፡

እያሱ፡- ግዴለም ዛሬ ደህና አትመስለኝም...

ጥላሁን፡- እምነት ምኞትህን ለመሸርሸር ሳይሆን...ያለህን ጥሬ እቃ እንደታዉቀዉ ነዉ፡፡ ግመል በሚሰራ ጥሬ እቃ፣ በሬ አትሰራበትም...( እያሱ ይስቃሉ)...በርካታ እምነትና ቋንቋ ባለበት አገር፣ ቱርክ ወይ ግብፅ የሆነዉን ለማድረግ ማሰቡ፣ ቱርክን እና የእኛን አገር አንድ አድርጎ መመልከቱ ነዉ በቅጡ ይታሰብ የምልህ፡፡ ሁሉም አንድ ዘር እና ሀይማኖት ቢኖረዉ ኖሮ ይሄን የመሰለ የጦርነት ታሪክም ባለነበረን፡፡ባጭር ጊዜ ይሄን ዉስብስ ችግር እፈታዋለሁ ብሎ መነሳቱም..መቸም...

እያሱ፡- ‹‹እምነት በቀቢጽ ታውራ፣ እንዴት ማየት ይቻላታል አሻገራ፡፡ መሞከር ያሻል ሁሉን፣ ብትፈራም፣ ፍርሃትን ሳይሆን አሳይ ተስፋህን›› ሲሉ አልሰማህም አለቃ ገሞራዉ ፡፡ ይሄን ድሃውን ተስፋም የለህም እብድ ነህ ብትለው፣ ‹ከቶ መኖር ለምኔ ነው?› ይላል፡፡ ተስፋው ነው ከተኛበት ጠዋት ቀስቅሶ የሚያስነሳው፡፡ እምነትህን ቁርጠኝነትህን ሲመለከት ነው ሌላዉ ለለውጥ የሚዘጋጀው፡፡ ከዚያች በርቀት ተሰቅላ ምታንጓው ቁጣ ዘንድ ለመድረስ ይደክማል፡፡ ተስፋዉ ጉልበት ሆኖት ተራራዉን ይወጣል፣ ከላይ ተጫፍም ይደርሳል፡፡ እብድ በሽተኛ ነዉ ብለህ ከተዉከዉ ጭራሽ ያብድና አገር ያዉካል፡፡ ተስፋዉን ያጣል

ጥላሁን፡- ተስፋ በምን ቋንቋ፣ ተስፋ በስንት ባህል ይሰበካል? ለአንዱ ‹ተስፋ› ያልከው ለሌላዉ ‹ነጠቃ› ይሆንበታል፡፡ የዚህ ጎሳ ተስፋ የዚያኛው መከራ፡፡ የዚህኛው ሃይማኖት ሲከበር የዚያኛው የተናቀ ነው የሚመስለው፡፡ የአንዱ ክብር ለሌላው ውርደት ነው የሚሆነው...የዚህ አገር እዳው ልዩነቱ ነው፡፡

እያሱ፡- (ትከሻቸው ይሰብቃሉ)....እንግዲህ ሌላ አገር የለንም፣ ይሄው ነው አገራችን፡፡ ‹ከመጣንበት መልሱንና ሌላ ቦታ ወስዳችሁ ፍጠሩን› ተብሎ አይባል፡፡ እናት ሆድ ተመልሶ አይገባ!... ምርጫ አለን? ሌላ ቦታ ችግረኛ ያልበዛበት፣ ደሞም ብዙ ብሄር እና እምነት በሌለበት አገር ፍጠሩን ማለት እንችላለን?

ጥላሁን፡- እሱማ እንዴ እዚሁ ተወልደናል፡፡

እያሱ፡- እንግዲያዉ የቻልነዉን ሁሉ እናደርጋለን፡፡...ደሞም አንተ እንደምትለዉ ሳይሆን...የዚች አገር ልዩነቷ እዳ መከራዋ ሳይሆን ጉልበቷ ነዉ፡፡ አሁን የቤት ጣሪያ ምን ቢወጥሩት፣ በቢርቢራ በቀርከሃ ቢያስሩት፣ ሲወጠር ቢዉል በተጠረበ እንጨት፣ ከላይ ሳር የስንደዶ ነዶ አስረዉ ጣራ ካላረጉበት አያስጥልም ከበረዶ ከዝናም፡፡ እንጨት ማገሩ፣ ይፈልጋል እርዳታ ከቅጠል ከሳሩ፡፡ እንዲሁ ዝም ብሎ ቢገተር፣ ጣሪያ አይሆን ባዶ ማገር፡፡ ልዩነት ጉልበት ነዉ፡፡ አንዱ የጎደለዉን አንዱ ሲሞላዉ፡፡...ይሄን የልዩነት ጥንካሬ ማየት ከተሳነህ...እንደኛዉኑ እዉር ነህ፡፡ ይቺን አገር ዞረህ እንደ እኔ ብታያት የምልህ ብዙ አይርቅህም፡፡ አሁን የምንሰራዉ ስራ፣ መላዉ የአፍሪቃ አህጉር ከቅኝ ገዥዎች ስር ሲወጣ አንድ ትልቅ አገር እንዲኖረን መሰረት ነዉ የምጥለዉ...

ጥላሁን፡- ድንበር ማክለሉም ብርቱ ስራን ይጠይቃል...ብቻ ሩቅ ማሰቡ ጥሩ ነዉ...

እያሱ፡- ሩቅ አሳቢ ቅርብ ያድራል??...(ይስቃሉ)..አይዞህ የማይሆን አይደለም፡፡ ከሽማግሌዎቹ በስተቀር የሙላዉ ህዝብ ድጋፍ አለን፡፡ ባላገሩን እየዞርን የብሔራዊ ማንነታቸዉን፣ እምነታቸዉን፣ ባህላቸዉን እዉቅና እና ክብር እንሰጠዋለን፡፡ ራሳቸዉን በራሳቸዉ ያስተዳድራሉ፡፡ ብዙ አስገባሪ ጦር አያስፈልገንም፡፡

ጥላሁን፡- ራሱን በራሱ እንደ ባህሉ ያስተዳድር የምትል...ይሄ ባለ እርስት ጉልቱ የት

ሊሄድ ነዉ? አሁን ባልቻ አባነፍሶን ከሐረር ብታነሳ እና እዛዉ ያለዉ አደሬ ቆቱዉን በራሱ ወግ እና ስርአት ይተዳደር፤ ቢባል የአባ ሳፎ ጦር እሺ ይላል?

እያሱ፦ (በሹክታ)...ታዲያ ለምን ይመስልሀል፤ ስርአት እስከባሪ የመንግስት ጦር፤ ፖሊስ የምናቋቁመዉ?...ትንሽ ጊዜ ነዉ የቀረዉ።...ጥልሽ ዛሬ ደግ አይደለህም ...የት ሄደ ያ ሁሉ ራእይ?..(ይስቃሉ)

ጥላሁን፦ ይሁን እስቲ...ይልቅ ዛሬ ለምን አትወጣም? አንድ ቦታ ድግስ ነበር፤ ታላቅ ፌሽታ

እያሱ፦ አይ...ዛሬስ አልወጣም ወደ መሽታ። የበቀደሙ የግብጦ ጠላ...(ይሳሳቃሉ) ..ሀይለኛ ነበር!

ጥላሁን፦ ከመሽታ ሳይሆን ከላይ ከእነ አስካለ ማርያም ቤት ነበር ድግስ ደስታዉ..

እያሱ፦ የትኛዋ ነበረች አስካለ ማርያም?..ያቺ አጭሯ?

ጥላሁን፦ የለም እሷ የደጃች ባይከዳኝን ልጅ ነዉ የምትለኝ..አስካለማርያም የበጅሮንድ ለጥይበሉ ልጅ...ትልቋ

እያሱ፦ አከናፌር አሳሳቋ...አወቅኳት..ግሩም ልጅ ነች...

ጥላሁን፦ ይሄዉ ጧት ማታ እያስላከች...መች ነዉ እያሱን የማየዉ ትላለች።

እያሱ፦ ከእኛ ጋር ዳግማዊ ምኒሊክ አስኳላ ስትማር አዉቃታለሁ። ከሷስ ያቺ መልካሜ ነች የናፈቀችኝ።

ጥላሁን፦ መልካሜ የቷ?

እያሱ፦ (በሹክታ)... ያቺ ባለ ትልቅ ደረቷ...አቤት ተረከዝ ባቷ...አቤት ሰዉነቷ

ጥላሁን፦ እህ..የደጃች ደምሰዉ አሽከር ነዉ አባቷ

እያሱ፦ አባቷ ለደምሰዉ ነዉ ያደረዉ?

ጥላሁን፦ አዎ...እዛ በግቢአቸዉ..ዉሃ ሲቀዳ እንጨት ሲፈልጥ ነዉ የማየዉ።

እያሱ፦ በል በል...በምታምነዉ ይሁንብህ!....ንሳማ እሱን ከቤተ-መንግስት አምጣና ስራ አስጠዉ። ኩነኔ ነዉ ለደምሰዉ መስራት። ደሞም ጥሩ ቦታ ይገባዋል...እሷን የአሳደገ አባት።

ጥላሁን፦ (ይስቃል)...ፈቃድህ ከሆነ እሷን ላምጣት እንግዲያ...ሁሉም ናፍቀዋል... አንተም ትንሽ እረፍት ያሻሀል..ሰሞኑን እኮ ትንሽ ተጎድተሃል..

እያሱ፦ (ሳቅ) ተጎድተሃል ጥሩ አማርኛ ነዉ። (ሳቅ) የነገረኛ አማረኛ ነች

ጥላሁን፦ (ያዜማል)...አንቺዬ አንቺን ያለ ማነዉ..ሰዉ ነገረኛ ነዉ! ...መልካሜ ነይልኝ እናቱ፤ ሳይደክም ጉልበቱ። መልካሜ ቁርጥማቱን እይዉ፤ በዳሌሽ አክሚዉ። ዋግምቱም ይቅርብኝ ይሻላል ጣቶችሽ፤ ስብራት ይታሰር በዘንፋላዉ ጠጉርሽ ...ገለጥለጥ አድርጌ ከንፈሯን ብቀምሰዉ፤ እንትፍ ሳልል ዋልኩኝ እንደ ቆረበ ሰዉ። (በጣቱ ያጨበጭባል)..መልካሜ አንቺን ያለ ማን ነዉ፤ ሰዉ ነገረኛ ነዉ..

እያሱ፦ (ይስቃሉ)..በል አሁን ማንን ለማነሳሳት ነዉ?..ይሄኮ ከፉከራ ከቀረርቶ በላይ ያነሳሳል...(ሳቅ)...

ጥላሁን፦ እኮ እንሂዳ!

እያሱ፦ ሰሞኑ ከራስ ተሰማ ናደዉ ጋር እርቅ ፈጥረን እየሰራን ነዉ...አሁን

እስኪደክመኝ ድረስ ልስራዉና..በኂላ ላይ በረጅሙ እርፋለሁ ብዬ ነዉ፡፡..ይልቅ ወደ ማታ... ( አቡነ ማቴዎስ ይገባሉ)...እንዴት አደሩ አባቴ...(ለመሳለም ያደገድጋሉ)

ማቴዎስ፡- (ሁለቱንም ያሳልማሉ፤)..አቤቶ እያሱ መቸም ከቅዳሴዉ መሀል አሻግሬ ሳስተዉል አለመኖርዎትን ተገንዝቤ ‹በደህና ነዉ ወይ ብዬ ነዉ አመጣጤ› ..በደህና ነዉ?

እያሱ፡- ማታ በስራ አምሽቼ ነው መሰል ማለዳ ሳልነሳ ስለዘገየሁ፤ ሆዴንም ሲጎትጠኝ ጊዜ...አኪሙም ‹የለም አትዉጣ› ቢለኝ...እንዲሁ ቅዳሴ ገብቼ አላስታጎጉልም ወጥቼ...ብዬ ነዉ እንጂ የዛሬዉንስ እቆማለሁ ብዬ ነበር፡፡

ማቴዎስ፡- ፆሙስ?

እያሱ፡- እሱንማ እያፆምኩ...በሱ መሰል የታመምኩት...ግን አሁን ተሽሎኛል..ክብሩ ይስፋ፡፡

ማቴዎስ፡- ፀሎቱሳ...የየእለቱን ጠብቀዉ...የሰኞ የረቡን፤ የጠዋት የመአልቱን፤ የአዉዳመት የአዘቦቱን..የፆም የጋድ የፍልሰታን የነነዌን የአስተረዌ የፅጌን ..ሁሉን ማወቅ ይገባዎታል፡፡

እያሱ፡- ይሄ ሁሉ አይበዛም አባቴ?

ማቴዎስ፡- አይ ልጅ እያሱ...‹ፀሎት በዛ› አይባልም፡፡ አባቶቻችን ቅዱሳን ነቢያት...ቀን ከመአልት ሳይሉ በጠሀይ በዉርጭ ደከመን ራበን ሳይሉ ሁሌም ፀሎት ያደርጋሉ፤ ከቅዳሴ ይቆማሉ፡፡ ይቆርባሉ...በፀሎት ራሳቸዉን ያተጋሉ፡፡ ህዝባቸዉንም ቃለ-እግዚአብሄር ያሰማሉ

እያሱ፡- እኔም እፀልያለሁ...ሁልጊዜም ባይሆን...ስፈራ ወይ ድንገት ከአቃዠኝ ድርሳኑን ተነስቼ እደግማለሁ፡፡

ማቴዎስ፡- ፀሎትማ መቼም መቅረት የለበትም፡፡ ለነቢያት ለመልአክት የምናቀርበዉ በረከት..ለጌታችን የምንሰግደዉ ስንፈራና ስናጣ ሲቸግረን ብቻ አይደለም የምንማለደዉ፡፡ ሁሌም በመንፈሳዊ በረከቱ እንዲዳስሰን፡ ይችንም አገርዎን የክርስቲያን ደሴት እንዲያደርግልን መፀለይ ይኖርብዎታል፡፡ ጌታም ይሰማዎታል፡፡ ...ሁሉን በእኩል የሚያየዉ ጌታ ከላይ ተቀምጦ ይፈፅምልዎታል፡፡

እያሱ፡- ለሁሉም እኩል የሆነ ጌታ...መቼም እሱ ይሄን...‹ጥቁሩንም ነጩንም እኩል ነው የሚያየው› ብለውኛል?

ማቴዎስ፡- እንዴታ! ሁሉን በእኩል የሚያይ ጌታ የማያዳላ፤ አንተ ጥቁር አንተ ነጭ የማይል...ሁሉን በአምሳሉ ፈጥሮ ሲያበቃ....

እያሱ፡- በአምሳሉ ሲባል...በየቱ ብዬ ነዋ...እሱ ጥቁር ነው ነጭ ወይ የቀይ ዳማ? ከየትኛዉ ነዉ እሱ?

ማቴዎስ፡- (ፈገግታ)...አይ አቤቶ ልጅ እያሱ...እሱ መንፈስ ነው፡፡ በቀዩም በነጩም በጥቁሩም ያለው አንድ ነው፤ መንፈሱ...ፈጣሪ ከላይ ከቆዳችን ቀለም ዘልቆ የገባ ሁሉንም በአንድ የሚያይ፤ የማያዳላ ሁሉን የሚረዳ፡፡ አንዱን ከአንዱ የማይለይ ሁሉንም በፍቅሩ በምህረቱ የሚኀበኝ፡፡ ለእሱ ሁሉም አንድ ነው፡፡ በእሱ ፊት ሁላችንም ልጆቹ ነን፡፡ የአንድ አባት እናት...የአዳምና ሄዋን ልጆች ነን፡፡

እያሱ፡- ይገርማል፡፡ ታዲያ ፈረንጆቹ ሽቅብ ወደ ምእራብ እና ከእኛም በታች ያለዉን ሻንቅላ ከመላው አፍሪቃ እያስፈነገሉ የሚያግዙትን ባርያ መቼ በምህረቱ ኀበኙት?

ጉድጓድ የመሰለ ጨለማ ውስጥ እንደ ከብት ከመርከባቸው ሲያጉሩት፤ ፈጣሪያቸዉ ሁሉን በኩል አይን የሚያይ መሆኑን ሳያውቁት ነው? ወይስ የእነሱ የፈረንጆች ክርስትና ለየቅል ነው? መንፈሱ ወንድሙን ሳይሆን ቆዳ ብቻ ነው የሚያየው? ‹መልኩ ከጠቆረ ብትገርፈው፤ ፊቱ ካላማረ ብትገለውም ብትሰነክለውም ኩነኔ የለውም› የሚል ነው የሚመስለው መፅሀፋቸው። አሁን በዚህ በአዉስትሪያ አገር የተፃፈዉ ጋዜጣ እንደሚለዉ...ስራቸዉ ለየቅል ነዉ። ይሄውሎት ያንብቡት ...(ጋዜጣውን ገፋላቸዋል)...በርግጥ ሀይማኖተኛ ከሆኑ በዚህ አምላክ በፈጠረዉ ድሀ እንዴት ጨከኑ?

ማቴዎስ፦ (ለአፍታ ጋዜጣውን ተመልክተው) ...ይሄ...እርስዎ የሚሉኝ የተለየ ነገር ነው። ሃይማኖት ያለውና ይሄ ዘላኑ ጅሌውን፤ ገና በአፍሪቃ በዱር ያለዉን ያልተጠመቀዉን አንድ አርጎ ማየቱ ያስቸግራል። የጌታን ሃይማኖት አምኖ...ቁርባን ስጋወ ደሙ የተቀበለውና ሃይማኖት የለሹም.......

እያሱ፦ ሃይማኖት ባይኖረውስ? ወንድም በወንድሙ ይጨክን ይላል? ያንብቡት ይሄን...ቆዳዉን እንደ በሬ እየሸነተሩ፤ እርጉዝ ድርሷን፤ የታመመዉን ከባህር እየወረወሩ፤ አመጠኛ የሚሉትን ሰቅለዉ በቁሙ እያቃጠሉ፤ ጥያቄ ያበዛል ያሳምጣል የሚሉትን አፉ ዉስጥ ሌሎቹ በግድ ሽንት እያሸኑበት እና...ብቻ ብዙ የማይነግር ግፍ ነዉ የሚፈፅሙት።...ሀይማኖት ባይኖረዉ እንዲህ ያለ ግፍ ማድረጉ ተገቢ ነዉ?

ማቴዎስ፦ መቸም ልጅ እያሱ...በዚህ ላይ ብዙው ሰው ገና ሃይማኖት የለውም።

እያሱ፦ ኧረ እኔም ራሴ ሐይማኖት ይኑረኝ በምን ይታወቃል?

ማቴዎስ፦ ሳአልነ ቅድስት...(ያመትባሉ)...እንደሚቀልዱ ይሰማኛል...(ይስቃሉ)፣.. የጣዲቁ ምኒሊክ ዘር...አሁን እንዲህ ቢሉ ማን ያምንዎታል? ይልቅ አመጣጤ...

እያሱ፦ አባቴንም አይርሱ

ማቴዎስ፦ በሚገባ እንጂ የጣዲቁ የራስ ሚካኤል ዘር።

እያሱ፦ መሃመድ አሊ አባ-ዱላ ነበር ስሙ።

ማቴዎስ፦ (ይስቃሉ)...እሱማ ቀረ ከቦሩ ሜዳ። ጣዲቁ አጤ ዮሐንስ ያጠመቋቸው፤ የእግዚያብሄር ባለሟል የፅዮን ጠባቂ ዛሬም የሃይማኖቱ ተሚጋች ናቸው፤ ታላቅ መንፈሳዊ አባት ናቸው።

ጥላሁን፦ መንፈሳዊ አባትስ ናቸው በርግጥ።....እስቲ ልጠይቅዎት አባቴ...ሃይማኖት ሳይኖረው መንፈሳዊ ሊሆን የሚችል ሰው አይኖርም?

ማቴዎስ፦ እንዴት ይሆናል ካለ አባቱ? ሀይማኖት ከመንፈስ፤ መንፈስም ከሃይማኖት ሊነጣጠሉ ከቶ እንዴት ይቻላል?

እያሱ፦ ሀይማኖት እግዚአብሄር ማፍቀርና መፍራት ነው። መንፈሳዊነትም እንዲሁ እግዚያብሄርን ማፍቀር ግን ሳይፈሩት መልካም የሆነውን ማድረግ ይመስለኛል። እንዲሁ...የራበውን ድሃ ሁሉ...‹እግዜር ይስጥህ› ቢሉት ሆድ ይሞላል?

ማቴዎስ፦ እርሱማ የፈጣሪን ስራ መውሰድና ፈጣሪ ልሁን እንደማለት ይቆጠራል። ከጥድቅ ያርቃል። ፈጣሪ በረቂቅ መንገድ የተራቡትን ይረዳል። የሞቱትን ከትቢያ...ዳንኤል ከአንበሳ መንጋጋ፤ ዮናስን ከአሳነባሪ ሆድ ያወጣ...ልዩ ረቂቅ ሃይል ያለው ጌታ ነው። ያለእሱ ምንም ጥድቅ የለም!

ጥላሁን፦ ለመጽደቅ ደግሞ ሐይማኖት ያስፈልጋል።

እያሱ፡- ሁላችንም ሀይማኖታችንን ለግላችን ይዘን... ‹ያመንኩትን እመኑ› ብሎ ሳያከራክር፤ ሳያስገድድ፤ የሌላውንም ሳያናንቅ...በተቀረው ነገር ብቻ ተስማምቶ መኖር አይቻልም?

ማቴዎስ፡- የአመነ እና የተጠመቀ ብቻ ይድናል፡፡ መንግስተ ሰማያትን ይወርሳል.... በመጥሀፉም እንደተጠቀሰው መንግስት ሰማያትን የሚወርሱት ቃሉን ከአጠናፍ አጥናፍ በማዳረስ...

እያሱ፡- የአባቴ ወገኖች ከልባቸው ያልተጠመቁት...ከነብዩ ቀጥታ ዝምድና ዝርያ ስላለን ገነተ-ሰማይ እንገባለን ይላሉ፡፡ የእናቴ ወገኖች ደግሞ ከንጉስ ሰለሞን...በነገደ ይሁዳ መስመር ያሉት ደግሞ ‹እኛ ብቻ እንጠድቃለን› ይላሉ...መቼም ትንቅንቅ ነው የሚሆነው እገነት በር ላይ...አይመስልዎትም አባቴ?

ማቴዎስ፡- የመጥደቂያ መንገድ አንድ ብቻ ናት፡፡ ሐይማኖትን ከስር መሰረቱ ካላዩት እንዲህ ቀላል አይሆንም ለመረዳትም ለማስረዳትም፡፡ ለዚህ ነው አበክረው ከደጅ ሰላም እየተገኙ ተዓምራትን መማር አለብዎ የምለው፡፡ መንፈሳዊትን ከሀይማኖቱ ነው የሚያገኙት፡፡.

ጥላሁን፡- ግና አባቴ፤መንፈሳዊነት ስላለፈው ሳያስቡና ሳይጨነቁ የዛሬንና የወደፊትን ብቻ በመመልከት ለመፅደቅ ለሽልማት ሲሉ ሳይሆን፤ እንዲሁ መልካም ሁኑ መልካም ተግባር ፈጽሙ ይላል...መልካም ደግ ነገር መስራት፤ ቀና መሆን እና ቀና መስራት ነዉ ከባዱ ፈተና፤ እንጂ ቤተስኪያን ደጅ መታየቱ በተግባር ካልተባረከ ምን ይጠቅማል?

ማቴዎስ፡- እየሀ ጥላሁን...አሁን ያልከዉ ጥሩ ነዉ፡፡ መልካም ለማድረግ ቡራኬ መባረክን ይፈልጋል፡፡ እየሀ ያለፈዉን ካላወቁ ካልተመረኮዙ፤ እንዲሁ በዛሬና በወደፊት ብቻ ከተከበቡ...መነሻና መድረሻችንን ማወቁ ያዳግታል፡፡ ታሪክን ሁነትን ድርሳናትን አጣርቶ ማወቅ ይበጃል፡፡ በተለይ ልጅ እያሱ... የዚች የክርስቲያን አገር ንጉስ በመሆንዎ አንክረው...አባትዎ ምኒሊክ የጀመሩትን ክርስትና ደጀ ሰላም ግንባታ እና የዚችን አገር የክርስትና ደሴት ለማድረግ የተጀመረውን ቅዱስ ስራ ሳያሰልሱ እንደሚሰሩ እምነትና ጸሎቴ ነው፡፡

እያሱ፡- ልክ ነዎት...(ለጥላሁን) ለመሆኑ የቀጨኔ መዳኒአለም ግንባታ እንዴት ሆነ?

ጥላሁን፡- ቀጨኔ መዳኅኒአለም...ትንሽ ነዉ የሚቀረዉ፡፡ ራስ ተሰማ የቀረዉን ወጪ በነጋድራስ ሀይሌ በኩል ስለፈቀዱ ብዙም ጊዜ ከእንግዲህ የሚፈጅ አይመስለኝም፡፡

ማቴዎስ፡- እኔም ሄጄ አየሁት...መቼም ትልቅ ስራ ነው በስምዎ የሰሩት፡፡ መንግስተ-ሰማይን የሚወርሱበት የልጅ አዋቂ የተስተኙበት...ይቺን አገር ምድረ ገነት ነው የሚያደርጓት፡፡

እያሱ፡- አቡነ ማቴዎስ.... ይች አገር የተለያየ ቀለም...የተለያየ ቋንቋ ያላቸው የብዙ ዘሮች መኖርያ ቦታ ነች፡፡ እናም ሁሉንም አንድ አይነት ቀለም ካልቀባሁት ብዬ መነሳቱ ይሄን ቤቱ የተሰራበትን የተለያየ መልክ ያለውን ማገርና ካስማ መልክ ማሳጣት አይሆንም? አገሩ የክርስትና የእስልምና የሌላም እምነት ተከታይ ያለበት መሆኑን መዘንጋት የለብንም፡፡

ማቴዎስ፡- ማስተማርና ማጥመቅ የቤተ-ክህነት ስራ ነው...ህዝቡን እያስተማርን ፊቱን ወደ ፈጣሪው እንዲመልስ እናደርገዋለን፡፡

እያሱ፡- አባቴ...ይሄን እስላሙን ለምን ሰለምክ ብዬ እንደ አጼ ዮሃንስ ካልተጠመቅክ ብዬ ብል ዛሬ እሺ የሚል ይመስልዎታል? ጊዜው ተለውጧል፡፡ አስቸጋሪ ነው

የሚሆነው...

ማቴዎስ፡- ከንጉስ ትእዛዝ የወጣ መቼም ቅጣቱን ያውቀዋል።

እያሱ፡- አባቴ...ይሄዉ ከአድዋ ማግስት ጀምሮ...ጠላት ዙሪያውን ከቦናል። አሁን አንድ አመጽ ቢነሳ ጣልያን እና እንግሊዙ ይፈልገዋል። እንደኔ ከሆነ ህዝቡ የሚመቸውን ይምረጥ። አንዱ ሌላውን አይናቅ። እንደ ባህሉም ሲሰግድ ቢውል፣ ጫቱን እየበላ ድቤውን ቢመታ...የመንግስት ግብር ከፍሎ የአገሩን ህግ ካከበረ፣ እኛም ልናከብረው ይገባናል።

ማቴዎስ፡- ይሄን የጌታ ቃል ከዳር እስከ ዳር ተደርሶ ለማየት ብዙ ነቢያት ቅዱሳት ተዋግተዋል። ምኒሊክም ሀዋርያ እንደነበሩ በድርሳናቸው ተጠቅሷል። በሌላውም አገር ዛሬ በሰለጠኑት እምነቱን ከእየሩሳሌም አንስተው ከአጥናፍ አጥናፍ ያደረሱት በብዙ ችግርና መከራ ነበር። የጌታ ሃይል ደግሞ ልክ የለውም.... ምን የሰለጠነ ሰራዊት ቢመጣ...እንደ አድዋው ቅዱስ ጊዮርጊስን በነጭ ፈረሱ ልኮ ከትቢያ ይቀላቅለዋል። ንፋስ ውርጩን ይለቅበታል...የበረዶ መዓት ይዘንብበታል።

እያሱ፡- አባቴ ትምህርቱ ይገባኛል። ይሄው በዚያ ሰሞን የእጨጌ ሰዎች በዚህ አሰሳ በሚባል ቦታ ከሼህ ቃወጀሌ ሰዎች ጋር በመጣላት፣ ግብሩን እያሰባሰቡ ቤተስኪያን ካልሰራንበት በማለታቸው በሱዳን ያሉ እንግሊዞች ሳይቀሩ ይቺን ቅሬታ ተጠቅመው በኢትዮጵያ ላይ አመጻ እንዲያነሱና ወደ መህዲ ሰራዊት.... ወደ ሱዳን ሄደው እንዲቀላቀሉ...የኛን ወገን እንዲወጉ ጠመንጃ በድብቅ ሲያስገቡ ነበር። ያንን አገር ቀርሰው ለሱዳን ሊሰጡብን እንግሊዞች መርዛቸውን እየረጩት ነው። የሀይማኖት አባቶች ሃይማኖቱ እንዲሰፋ ማድረጋቸው መልካም ነው፣ ይሁን እንጂ...እንደ እኔ እምነት አገራችን እንድትሰፋ እወዳለሁ። ታላቅነትዋ እንዲጎላ እፈልጋለሁ። ለኔ ሁሉም ወዳጄ ነው። የሰሩትን አከብራለሁ፣ ወደ ሱዳንና ሶማሌ ከሚሄዱብን እዚሁ የሚያምኑትን እያመኑ ቢቀዩልኝ እመርጣለሁ። ቤተስኪያኑንም መስጊዱንም እገነባለሁ።

ማቴዎስ፡- ቤተስኪያኑን ቢገነቡት...ሰውን ወደዚያ ካላስገቡት...ምን ይጠቅማል ባዶ ቤት? ይሄ በሻንጉል ያለው ህዝብ የባሮ ወንዝን ተከትሎ ያለዉ ሻንቅላ መዳንና መጠመቅ አለበት። (ጥላሁን ለእያሱ በምልክት ዝም እንዲሉ ያሳያቸዋል)

ጥላሁን፡- ልክ ነዎት አባቴ..ይፍቱኝ! (ይንበረከካል..እያሱንም ይባርካሉ)

ማቴዎስ፡- (እጃቸዉን በእያሱ ራስ ላይ አድርገዉ በለሆሳስ ፀሎት ያሰማሉ) ስብአት ለአብ ስብአት ለወልድ...እመእሰረ ኩሉ.../አፋቸዉ ይንቃነቃል/...

ጣሴ፡- (ይገባል ለተመልካች) የኢትዮጵያ ጠላቶች ዙሪያው ከበው እያዩን ነው ዛሬ። የምኒሊክ የጦር መሪዎች አርጅተዋል። ዛሬ ኢትዮጵያን የሚያድናት ነጋሪት ሲጎሰም የሚወጣ ጦር በጣም ጥቂት ነዉ። ባላባቱ እርስ በእርሱ እየተሻኮተ ነው። ዛሬ ጎበዝ ጦር ሳይሆን ፍቅር ብቻ ነው አገራችንን ከመፈራረስ የሚያድናት። ይኸው በጣሊያን ስር ያሉት ሶማሌና ቆቱዎች ‹ከባርነት ነጻነት› በማለት ከበርበራ እና መቃድሾ በሚባል አገር እያሸፈቱ ወደ ኢትዮጵያ እንቀላቀል እያሉ ነው ይባላል። እኛ ከዚህ ሄደን በሉ ይሄን ጥምጣም ኮፍያችሁን አውልቁና ጣሉ ካልናቸው። ‹ከእናንተ እጣን ቀበርቾ ይሻለናል የጣልያን ከልቾ› ብለው ጥለውን ጠላት ይሆኑናል። ከኛ ጋር ያለውንም ያሸፍቱብናል።...ይቺ አገር በጉልበት እና በማደናገር ሳይሆን በፍቅር ትሰፋለች...(ከእያሱ ጎን ይንበረካካል)

ማቴዎስ፡- እማእሰረ ሐጥያት ሁሉንም ይፍታ...የሰማነዉን ይባርክልን! .

ሁሉም፡- አሜን!..(ይነሳሉ፣ይሳለማሉ)..ይልቅ ሳልረሳዉ..ቅድም ያቃዠኛል ያሉኝ

ምንድነዉ?..

እያሱ፡- አዎ ከወር በላይ ሆነዉ..አንድ አይነት ነገር ነዉ የማየዉ

ማቴዎስ፡- እኮ ምንድነዉ?

እያሱ፡- የሆነ ጥላሸት የመሰለ ፊት ያለዉ...ይሄ ከባሮ ወንዝ ባሻገር ያሉት ሰዎችን ነዉ የሚመስለዉ...ይመጣ እና በዙፋኑ ሆኖ ሲያነጋገረኝ..(ማቴዎስ ያማትባሉ)...ደሞ እንዲሁ ቆቱ የምትመስል አብራኝ ተኝታ..

ማቴዎስ፡- ተኝታ?

እያሱ፡- እንደሱ ይመስለኛል..የምትናገረዉ አማረኛዉን እየቀላቀለች...ከዚህ በደቡብ በታች ያሉትን ባሮች ነዉ እሷም የምትመስለዉ...በዙፋኑ ተቀምጣ ትናገራለች..እኛን እያየች...

ማቴዎስ፡- ይሄማ ህልም አይባልም...ቅዠት ነዉ።

እያሱ፡- በተደጋጋሚ እኮ ነዉ የማየዉ...ጥቁረቷ ልዩ ነዉ። ታዲያ የተቀረነዉ ተስማምተን በትልቅ ገበታ...እዚህ በግብር ቤት ተቀምጠን ስንበላ...በተለያየ ቋንቋ እያወራን..እሷም በልጆቿ እና በባሏ መሀል ተከባ..እንደዚህ ቀስ ብላ ከዙፋኗ ተነስታ ትመጣና ከማእዱ እንጀራ እየቆረሰች ስትሰጠን ሁላችንም የየራሳችንን ወጥ እያጠቀስን የየባህላችንን ልብስ ለብሰን፤ እንዳንዴም እርቃናችን...(ያማትባሉ)..በቃ ራቁታችንን ሆነን ነዉ የማየዉ። ያን ጊዜ ታዲያ ከአልጋዬ ተነስቼ እፀልያለሁ ...ድርሳነ ማርያንም እደግማለሁ። አቤቱ እንደ ፍቃድህ ይሁን እላላሁ።

ማቴዎስ፡- አይ...ይህንን ከምንም አይቁጠሩት። ምናምንቴ ናት....ብቻ ቅዠት ነዉ። እጨጌ ነገ ረፋድ ላይ መጥተዉ ሙላዉ ቤቱን ጠበል ይረጩታል።..ይሄን ምናምንቴዉን ከዚህ ግድም ያጠፉታል...እርስዎም ያለቅዠት በሰላም ይተኛሉ።...ይልቅ ከደጅ ሰላም አይጥፉ...

እያሱ፡- እሺ አባቴ፤ ኧረ እመጣለሁ...( ማቴዎስ ሁለቱንም አሳልመዉ ከጣሴ ጋር ይወጣሉ....ፋታ)..

ጥላሁን፡- መጥፎ ህልም ወዳጄ....ለመፍታትም ይከብዳል። ብልህ እና አዋቂ መሆንን ይፈልጋል...በጣም ከባድ ህልም...

እያሱ፡- (ጋዜጣዉን ተመልክቶ)...መሀንዳስ ጋንዲ እድለኛ ነዉ...የሚሰማዉ የሚከተለዉ ብዙ ህዝብ አለዉ። ድጋፉ ከፍተኛ ነዉ።

ጥላሁን፡- ህንድም እንደሰማሁት አንድ ህዝብ አይደለም። ብዙ ብሄር እና ቋንቋ ያለበት ነዉ..አሁን በእንግሊዝ አንድ ሆነዉ ቢያብሩም ኋላ መዘዝ ይኖረዋል።

እያሱ፡- ህዝቡ ብዙ ባህል ቢኖረዉም..መለያየቱ ጌጥ ነዉ...ጉልበት ነዉ...አንዱ የሌለዉን አንዱ እያዋሰዉ...ፌደራሲዩን የሚሉትን አይነት...

ጥላሁን፡- ፌደራሲዮን እንደ ጀርመን እንደ ፈረንሳይ?...

ጣሴ፡ (ይገባል)... ፌደራሲዮን አሉ??

እያሱ፡- አዎ ሁሉም እንደ ባህሉ፤ ሁሉም እንደ አመሉ!..

(በርካታ ሴቶች የተለያየ የብሔር ልብስ ለብሰዉ ይገባሉ። የተለያየ የባህል ጭፈራ በጭብጨባ እያፈራረቁ ይጫወታሉ..እያሱ ከሁሉም ጋር ይጨፍራሉ...ጨዋታዉ ሲያበቃ..ሁሉንም በፍቅር አይን እየተዘዋወሩ ይመለከታሉ)

እያሱ፡- እንዲያዉም..ሁሉንም አግብቼ ሚስት አደርጋቸዋለሁ!!

ጣሴ፡- ፌደራሲዮን ነዉ ያሉት? ወይስ ፍትወት-አሲዎን!...(ሴቶቹ ብትን ብለዉ ይወጣሉ)

ጥላሁን፡- ይሄማ ሴሰኛ ነዉ የሚያሰኝህ!

እያሱ፡- እሰቲ ማነዉ በሚስቱ ያልደረበ፤ ዉሽማ ያላስቀመጠ?...ዲቃላ ያልወለደ ባላባት?...በየባላገሩ ተደብቆ ከሚያያት ምናለ አንድኛዉን ቢያገባት?.

ጣሴ፡- ሁሌም ዉሽማ ታምራለች..ሚስት ካረጓት አታምርም...ትደብራለች።

ጥላሁን፡- መቼም ባህሉ ሀይማኖቱ የሚከለክለዉን ማድረጉ ኋላ ላይ ከቤተ-ክህነት ጭምር ያጣላናል።

እያሱ፡- እንደዛ ከሆነ ባህሉም ሀይማኖቱም ይቅርብኝ...ምን አለ ቱርክ ህንድ ባደረገኝ! አታ ቱርክን ወይ ጋንዲን ምነዉ ባደረገኝ!

ጥላሁን፡- የለም....ጋንዲንም የሚጠላዉም አይጠፋም አልኩህ እኮ...እሱ በሰላም ‹ያለ ምንም ደም› ሲል ጓደኞቹ ደግሞ ‹የለም! በጦርነት እንጂ ያለ ደም ሰላም አይመጣም›› የሚሉትም አሉ። እኛ እንደምናስበዉ ተወዳጅ እና ዝነኛም አይደለም። ‹ደካማ የእንግሊዝ አሻንጉሊት፤ አቋም የለሽ ተንሸራታች› የሚሉትም አሉ። ምናልባት ከሞተ በሁዋላ ክብር ይሰጡት ይሆናል።

እያሱ፡- ትርጉሙ ያልገባዉ..ራዕዩ ያልታየዉ....የማይቻለዉ መቻሉ ሲያየዉ....ነገ ህንድ ነጣ ሲወጣ... ይሄ እኛ አገር ከአዱሲስ እስከ መቱ የሚመላለሰዉ ቅመም ነጋዴዉ ህንዱም ያኔ ልቅም ብሎ አገሩ ይገባል።

ጥላሁን፡- የእኛ ህዝብ ላለመስማማት ፈጣን ነዉ። ለማዉገዝም ለማመስገንም ችኩል ነዉ። የታመመዉ ሁሉ አኪም ነዉ። ለዚህ ነዉ ታሪካችን ሁሉ ‹‹ነገሰ ገደለ አባረረ ተባረረ ሞተ›› ብቻ የሆነዉ። ፍቅር አልባ ክብር አልባ..አንዱ ሌላዉን ሲንቅ ሲያጣጥል...መጣል መጠላለፍ። ለሚያልፍ አመል ሱስ፡ አገር ማወክ ማመስ።

ጣሴ፡- በፈረቃ ማፍረስ!

ጥላሁን፡- ድህነት የሚሉት የአእምሮ በሽታ ነዉ ችግራችን።

እያሱ፡- የለም አትድገመዉ.....የእኛ ህዝብ በርግጥ አብዛኛዉ ድሀ ነዉ። በሌማቱ ካለችዉ ትንሽዬ እንጀራ፤ ያ ሁሉ እጁን ሲሰነዝር ሲዘግነዉ፤ ከሚጎርሰዉ ይበዛል በባዶ ጣቱን የሚልሰዉ። አኗኗሩ ከአሉት በታች ከሞቱት በላይ ሲያደርገዉ፤ ስምምነት ያጣል...ክብሩን ይሸጣል። ከእሱ ከራሱ አልፎ ስለ ሌሎች ማሰቡም ይከብዳል። ግና ...ቢኖረዉ ካልተነጠቀ የሚበላዉን....የሚለብሰዉን ልጆቹን የሚያሳዳግበትን ዳረጎት ከተቸረዉ፣ ሲበደል የሚከራከርለት የፍትህ ስርአት ከአለዉ፤ ይለወጣል...ለዚህ ነዉ አዲስ መንገድ የሚያስፈልገን። አሮጌዉ ስርአት ሳይንኮታኮት አዲሱን መገንባት አለብን። በጀመርንበት ያለማፈግፈግ መቀጠል አለብን።

ጥላሁን፡- እንግዲያዉ...በቶሎ ለመጀመር። የንግስና በዓሉ ለምን ተላለፈ? ቶሎ ቢደረግ መልካም ነበር። በተለይ ወጣቶቹ ናቸዉ የጓጉት። ይሄን የምኒሊክ ሙክት መቼ ነዉ በአዲሱ ሀይል የሚተኩት እየተባለ ነዉ። ‹‹ንጉሰ ነገስት እያሱ አምስተኛ፡ ሞ አንበሳ ዘ-እምነገደ ይሁዳ!...ሞት ይገባዋል እሱን የከዳ!›› እየተባለ ነዉ።...ጣሴ ምን እየተባለ እንደሚዘፈን ለምን አትነግረዉም?

ጣሴ፡- ኧረ ብዙ ነዉ የሚባለዉ...ይልቅ የኪነት ባለሙያዎቹም ጧት ጀምሮ መጥተዉ ቆመዋል..ምን ልበላቸዉ?

እያሱ፡- ቅድም አትነግረኝም ነበር? ለመሆኑ በልተዋል?

ጣሴ፡- ከጠጁም ከቁርጥ ስጋውም ሙዳ ሙዳውን ሲሰነድሩት ነው ያረፈዱት፡፡

እያሱ፡- እነሱም እንደ ቄሶቹ ናቸው…አኩራፊ!

ጣሴ፡- ከቄሶቹስ አዝማሪዎቹ ይሻሉኛል…ቄስ ያስፈራራል፡ አዝማሪ ያጫውታል፡፡ ኑሮንም ሞትንም ቀለል ያደርጋል፡፡

እያሱ፡- ብዙ መኖር አትፈልግም?

ጣሴ፡- መኖር? እንደማቱሳላ?

እያሱ፡- እህ!.

ጣሴ፡- አንዲት ነገር ሳልሰራ ብዙ ዘመን ከምኖር የልቤን የሃሳቤን ፊፅሜ በጊዜ ብገላገል እመርጣለሁ…ለመኖር ስል ብቻ መኖር ምን ያረገኛል?

እያሱ፡- አዎ በሬም ከብትም ይኖራል፡፡ ግና የታደለው በሬ ብቻ ሲሞት ቆዳው አታሞ ይሰራበትና ስርግ ያደምቃል፡፡

ጣሴ፡- ያልታደለው በሬ መስሎኝ፤ ሲሞትም ቆዳው ክበሮ የሚሆነው?

እያሱ፡- ኸረ በጭራሽ! የታደለው ነው እንጂ፡፡ አትረሳ ያለው፡፡ ቆዳው ተለፍቶ የንጉስ ነጋሪት የሚሆነው…እልፍኝ የሚያሳምረው፡፡ ያልታደለውንማ ማን አስታውሶት? ይኑር አይኑር ማን አውቆት? የጃጀው ሲደናበር፤ ለመኖሩ አንዲት ማስረጃ ሳይተው እንዲሁ ያልፋል፡፡ ቆዳዉን ጭምር ጅብ ይበላዋል፡፡

ጣሴ፡- መቼም ሳውቀው….‹ያልታደለ በሬ ሲሞት ቆዳው ክበሮ ይሆናል› ነው የሚለው ተረቱ፡፡

እያሱ፡- እሱ አይደለ ስህተቱ?! እሱ ነው የታደለው ባለ ክበሮው! ድምፁ አልጠፋ ያለው… ይሄን የግልብጥ እምነት ነው ዛሬ መቀየር ያለብን፡፡ ይልቅ አዝማሪዎቹን አስገባቸው፡ ‹‹ከደጃፍ ጎልቶን ዋለ›› ብለው ዘፈን ሳያወጡብኝ፡፡

ጣሴ፡- በልተዋል እስኪበቃቸው… አዝማሪ ሆዱ ከሞላ ብዙ አይፈልግም፡፡ ከጠጁም ሲወርዱበት ነው ያረፈዱት፡

እያሱ፡- ሰክረዋል በለኛ

ጣሴ፡- አዝማሪ አይሰክርም ጌታዬ፡፡ ምን ቢጠጣ ሳይንገዳገድ፤ ሳይወላገድ ቀጥ ብሎ ቤቱ የሚገባው፤ እሱ አዝማሪው ብቻ ነው፡፡

እያሱ፡- ግሩም ችሎታ ነው፡፡ አዲስ ዜማ አላቸው?

ጣሴ፡- አዲስ ነው ሁሉም፡፡ እነኚህም አዲሶች ናቸው፡፡

እያሱ፡- በል አስገባቸው፡፡ …(ይቀመጣሉ…ጣሴ ይወጣል)… ጥበብ የነፍስ ምግብ ነች፡፡‹‹ጥበብ በጠፋበት አገር የሚኖር ህዝብ ነፍስ አልባ እንስሳ ነው፡፡›› ማን ነበር እቴ ያለው? (ጣሴ ማሲንቆ፡ ክራርና ክበሮ የያዙና አንድ በትንሹ የሚንገዳገድ ሰዎች ይዞ ይገባል፡ እጅ ነስተው ይቆማሉ፡፡)

ጣሴ፡- (ፈንጠር ብሎ ይቆማል) ….ጃንሆይ ‹እንዴት ዋላችሁ› ይላሉ!

ኪነቱ፡- እግዚያብሄር ይመስገን፡ ይባርክልን እድሜ ይስጥልን፡፡ (ክራሩን ማሲንቆውንም ማስተካከልና መቃኘት ይቀጥላሉ .. ባለ ክበሮውም እያገላበጠ በትንሹ በእጅ ይሞክራል…ባለ ድምፁ ጉሮሮውን ያፀዳል…ረጅም ጊዜ ያጠፋሉ በመቃኘት…ጀምረው ይቋረጣል፤ አንዳቸው በአንዳቸው በለሆሳስ ያመሃኛሉ…እንደገና ይቃኛሉ፡፡)

ባለ ክራር፡- (መደርደር ይጀምራል...አቁሞ መቃኛዉን ያጠብቃል ያላላል...እንደገና ይሞክራል...)...ጅማቱ ነዉ..በደምብ አልወጠር እያለ...(ይቃኛል...)...እንጨቱ እያዳለጠዉ ዜማ አልይዝ ስላለ..ነዉ..(ሲቃኝ ይሞክራል)....ገመዱ ጅማቱ ነዉ...ከላይ አልይዘዉ ብሎ ነዉ...

ጣሴ፡- እሺ...ክራሩን ሌላ ጊዜ እንሞክራለን..አዲስ ዜማስ ምን አለ?

ዜመኛዉ፡- (ወደ ፊት ወጣ ብሎ..ጉሮሮዉን ከአፀዳ በኋላ፤ ጆሮዉን ይዞ ሽቅብ እያየ)...ኸኸኸኸ...እእእ...ቆይ..(ጉሮሮዉን ያፀዳል)...ኸኸኸኸ...እእእ...የለም ልክ አልመጣልኝም.....(ጉሮሮዉን ያፀዳል)...ኸኸኸኸ...እእእ...የለም...ቆይ ከላይ ልዉጣዉ...ኧረ ባቲ ባተኢኢኢ....(ጉሮሮዉን ያፀዳል)...ማለዳ ስነሳ ትንኝ ነገር በጉሮሮዬ ገብታ ነዉ መሰል...

ጣሴ፡- ይበቃል...ወደ ቅኔዉ እንሂድ...

ባለቅኔዉ፡- (ጆሮዉ ላይ ያለዉን ወረቀት ፈትቶ ያነባል)...እያሱ እያሱ እያሱ እያሱ፡ የልጅ ትልቅ ...አለም ጤና ፈረሱ....ከመቼዉ መጣና አገሩን...አገሩን...ቆይ አገሩን ....አገሩን አይደለም...ከላይ ልዉጣዉ እንደገና...እያሱ እያሱ እያሱ፤ እያሱ..እያሱ ...ምነዉ ተለየኸኝ፤ በመስከረም መባቻ...(ሁሉም ከት ብለዉ ይስቃሉ)

እያሱ፡- (ይስቃሉ)...ማነዉ?...እንዴት ነዉ ከኪነት ጥበብ የገባችሁ?.

ጣሴ፡- (ባለከበሮዉን ወደፊት እየገፋ ያመጣዋል)..ይሄ ነዉ አለቃቸዉ..(ባለ ከበሮዉ ገድገድ ብሎ ይቆማል)...

እየሱ፡- እንዴ...‹አዝማሪ ይጠጣል እንጂ አይንገዳገድም› አላልክም ነበር?

በረደድ፡- አዎ ነበር!! ይሄ እንግዲህ አዝማሪ አይደለም ማለት ነው፡፡

እያሱ፡- አንተ ባለ ከበሮዉ ከየት ነው ያመጡህ? ማንስ ትሰኛለህ? .

አለቃዉ፡- አቤቶ ጌታዬ እያሱ! ሀብተማሪያም ነው ስሜ...ስራ ጠፋ ምን ልሁን የት ልውደቅ?! ልጆቼን ምን ላብላ? ከበሮ ‹አታሞ ነው ማንም ይመታዋል› ቢሉኝ ከኪነቱ ገባሁኝ....

እያሱ፡- የለም ይሄ ስነ-ጥበብ የሚሉት ብርቱ ሙያ ነው፡፡ ታዲያ ክፉ አዙሪት አለው፡፡ የማይወዳቸውን አመዳም ነው የሚያረገው፡፡ በሉ ባይሆን እኔ ሌላ ስራ ልስጣችሁ፡፡ አገር ትረዱበታላችሁ፡፡...(ሁሉም እጅ ነስተዉ ያጎነብሳሉ)...ይሄ ክራሩ ዘፈኑ እና ቅኔዉ ለእናንተ አይሆንም፡፡ ኪነጥበብ ከልብ ሳይወዱ እንዲሁ ከገቡበት እንዳልኳችሁ እከካም አመዳም ያደርጋል፡፡ ሆዳችሁ ጠግቦ እንኳ ረሀብተኛ ጅብ ነዉ የሚያረጋችሁ፡፡

ሁሉም፡- ልክ ነዎት!..ጅብ አረገን!..ጅብ ብቻ ነዉ ሌላዉን ወንድሙን ጅብ የሚበላ...

እያሱ፡- እንግዲያ ታዲያ ለምን የመንግስት ሰራዊት፤ የአገር ጠባቂ አትሆኑኝም? ጦርነት መዋጋት ሰላም ማስከበር..በሰላሙ ጊዜም አገር ግንባታ መንገድ መቀየስ፤ ቤት መስራት ደካማዉን መርዳት ትማራላችሁ፡፡ ...ጥላሁን...ያኔ የተነጋገርነዉ የመንግስት ጠባቂ...ወጥቶ አደር የመንግስት አሽከር ያልነዉ የት ነዉ የሚመዘገበዉ? .

ጥላሁን፡- ‹ወጥቶ አደር› ብለን ያልነዉ...ምዝገባዉ ሮብ ሮብ አራዳ ጊዮርጊስ ፍርድ ቤቱ ግቢ ነዉ፡፡ ትንሽ ሰዉ ቢጎድለን ነዉ ለመጀመሪያዉ ስልጠና፡፡

ጣሴ፡- ወጥቶ አደር?...ወታደር?

እያሱ፡- አዎ...ይግቡ እነዚህ ሰዎች...አገራቸዉን ይወዳሉ፡፡ አይደል እንዴ?

ኪነቱ፡- አዎ እንወዳለን!!

እያሱ፡- እንግዲያዉ...ይሄን ዱርየዉን ከተማዉን ሌትና ቀን የሚያሸበረዉን....እርስ በእርስ በዉሽማ የሚጣላዉን የየባላባቱን ጦር እና ነጋዴዉን የሚነጥቀዉን የከተማ ሽፍታ ማጅራት መቺ ትከላከሉልኛላችሁ፡፡ ባለ ጋሪዎቹን ማታ ማታ እያጠበቁ የሚነጥቋቸዉን ትይዙልኛላችሁ፡፡....አኪም ሚሼል..በሰለጠዉ አገር ‹ፖሊስ› የሚባል በሰላም ጊዜ ህግ ስርአት የሚያስከብር ሀይል ያስፈልጋል ሲል ነበር፡፡ ከተማዉም የጦር ግንባር አይመስልም፡፡

ጣሴ፡- ነጭ ለባሽ፤ ጥሩምቡሌ...ወጥቶ አደር...ቡሊስ?

ጥላሁን፡- ዕረቡ ጊዮርጊስ ከመጣችሁ...ልብስ ዳረጎት ታገኛለችሁ...ስልጠናም ቁጥሩ ሲሞላ ትጀምራላችሁ፡፡

እያሱ፡-አገራችሁን ትጠብቃላችሁ..ሰላም ታስከብራላችሁ...የባላበት የንጉስ ሳይሆን የህዝቡን ደህንነት ትጠብቃላችሁ...ህጉን ታስከብራላችሁ...(እያሱ ተመልሰዉ ወደ ወንበራቸዉ ሲመለሱ..ሰዎቹ እጅ ነስተዉ ይወጣሉ..ደጃች መርእድ ይገባሉ)...እንደምን አደሩ ደጃች መርእድ?

መርእድ፡-ክብሩ ይስፋ ለመድሐኒ አለም..እርስዎስ እንዴት ከርመዋል?.

እያሱ፡- ደህና ነኝ...ከእቴጌ ዘንድ ምን ጉዳይ አለ?

መርእድ፡- እቴጌን እዚሁ ከቤተ-መንግስት ሆነዉ እምዬ ምኒሊክን እንዲያስታምሙ አማላጅ ልከን እሺ አሰኝተናቸዋል...

እያሱ፡- ስንት ጊዜ ነዉ አማላጅ የሚላክ?...ልሂድ ካሉ ለምን አይሄዱም?..ጊዜዉ ተቀይሯል...

መርእድ፡- እሱስ ተቀይሯል..ግና ግዴለም ሁሉን በዘዴ ማድረግ አይከፋም...በእሳቸዉ የተሾሙት ሁሉ ተሽረዋል..

ጥላሁን፡- ሁሉም ተሻሩ?

መርእድ፡- አዎ የታጩት ሴቶችም ቀርተዋል...የሄዱትም ተመልሰዋል፡፡

ጥላሁን እና ጣሴ፡- ምን?

መርእድ፡- አዎ...ያዉ የታጨችዉ የሮማንወርቅ መንገሻ ቀርታ ሰብለወንጌል ተለዉጣለች...መቸም ጉዳዩ..

እያሱ፡-እሱንስ ሰማሁ...ግና ሮማን ወርቅም መልካም ነበረች...ሰብለ ወንጌልም ጥሩ ልጅ ነች፡፡

መርእድ፡- ቢሆንም ሰበለ ወንጌል ሀይሉ ትሻላለች...የራስ ሀይሉ መንገሻ ልጅ...ጎጃም ይገብራል፡፡

ጥላሁን፡- የሮማን ወርቅ ዘመዶች...ትግሬዎቹ እንዳያምፁ እንጂ...ብቻ እቴጌ የወጠኑት ስለማይታወቅ መፍረሱ ልክ ነዉ፡፡

እያሱ፡-ለእኔስ ሁለቱንም ቢድሩኝ አገባለሁ...

ጣሴ፡- ፌዴራሲዮን፡፡

መርእድ፡- (ይስቃሉ)..አይ ልጅ እያሱ..እንደ እሱማ አይሆንም፡፡ በባህል በሐይማኖታችን ጋብቻ ከአንድ ብቻ ነዉ፡፡...ይሄን እያዉቁትም ብዬ ሳይሆን ወሬዉ እንኳ ቢሰማ...ተቤተ-ክህነት ሰዎች ብቻ ሳይሆን ተሌሎችም ጭምር ያጣላዎታል፡፡

ጥላሁን፡- የተሸሙት ከተሻሩ...የደጃች ተፈሪ ለምን ይርጋ ተባለ? ባልቻ አባነፍሶ የት ሊሄዱ ነዉ?

መርእድ፡- ደጃች ባልቻ ወደ ነቀምቴ ናቸዉ፡፡.

እያሱ፡- የተፈሪን ሹመት ራስ ተሰማ ነግረዉኛል:: ደጃች ተፈሪ ደህና ሰዉ ነዉ፡፡ የእህቴን ልጅ መነንን አጭቼለታሁ፡፡

ጥላሁን፡- መነን ባሏን ትታ ልትሄድ?

እያሱ፡- አዎ ፈቅዳለች፡፡ ወላድ ናት...ለተፈሪ ልጅ ትሰጠዋለች፡፡

መርእድ፡- ይልቅ ደስ ያላለኝ...መቼም መጠራጠር ሳይሆን...የጉግሳ ወሌ እና የዘዉዲቱ ጋብቻ ነዉ፡፡

እያሱ፡- እሱማ ጥሩ ነዉ፡፡ ዘዉዲቱ ከማጀት ወጥታ ከሰዉ ትታይበታለች፡፡ ሁሌም ከሰራተኞቹ ስር እኮ ነዉ የምትዉለዉ፡፡ እቴጌ ጣይቱ በዚህስ ጥሩ ነገር ነዉ የሰሩት፡፡

ጣሴ፡- (ለተመልካች).. ይሄኛዉ ንግስና ከፈረሰ፤ የእቴጌ የወንድማቸዉ ልጅ በዘዉዲቱ በኩል ነገሰ ማለት ነዉ፡፡

መርእድ፡- መቸም እቴጌ ባላባቱን ሁላ ስላስከረፉ፤ ሁሉንም ስራቸዉን መጠርጠር ይዘን ነዉ እንጂ...

ጥላሁን፡- ልክ ነዎት...‹እቴጌ ፍቅራቸዉ ሀብት በረከት፤ቁጣቸዉ መብረቅ ነዉ መቅሰፍት›› ነዉ የሚባለዉ፡፡ ጣልያን ጭምር ነዉ የሚፈራቸዉ፡፡

መርእድ፡- አሁን በረድ ብሎላቸዋል፤ በእሳቸዉ ብዙም መፍረድ አይቻልም.. (ለእያሱ)...ይልቅ እርስዎ ከደጀ ሰላም አይራቁ፡፡ ከእንግዲህ ልጅነት የለም፡፡ ጃንሜዳ በጨዋታ ከሚያጠፉት ጊዜ እየቀነሱ ባላባቱን እየጠሩ ምክር ማድረግ፤ ህዝብ አያያዝ እና የመንግስት ስራን አሰራር መማር አለብዎት፡፡ ለወሬኛዉ ቀዳዳ አይስጡት፡፡

እያሱ፡- መልካም ምክር ነዉ ደጃች መርእድ፡፡ እንደ እርስዎ ያሉ ሰዎች ያስፈልጉናል፡፡ ምክርዎትንም ተቀብለናል፡፡

መርእድ፡- (እጅ ይነሳሉ)..ሁሌም ታዛዥዎ አገልጋይዎ ነኝ...ራስ ተሰማንም አበክረዉ ሊሰሟቸዉ ይገባል፡፡ ትልቅ መላ ዘዴ አዋቂ በመሆናቸዉ ከእሳቸዉ ጋር ብዙ ጊዜዎን በማጥፋት...እስከ በዓለ ንግስናዉ ተግተዉ መማር ችላ እንዳይሉ..(እጅ ይነሳሉ)...እኔም ወደ ፊታዉራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ዘንድ ስሄድ በደጁ ሳልፍ ዝም ብዬ ‹እንዴት ሰነበቱ ሳልል› አላልፍም ብዬ ነዉ የገባሁት..

እያሱ፡- ለመሆኑ ፊታዉራሪ እንዴት ናቸዉ? ቆየሁኝ ካየኋቸዉ....

መርእድ፡- ክብሩ ይስፋ ደህና ናቸዉ....ባለፈዉ ጉንፋን ቢጤ አሟቸዉ ሰነበቱ፡፡ አሁን ደህና ናቸዉ፡፡...ሁሌም ‹ልጅ እያሱ በምኒሊክ የተሰጠን የአደራ ልጅ ናቸዉ› ይላሉ..ስለ እርስዎም ስለ ዙፋኑም ብርቱ አሳብ አላቸዉ፡፡

ጥላሁን፡- እንግዲህ ሰላምታ ያድርሱልኝ ዛሬ ካዩአቸዉ፡፡

መርእድ፡- አደርሳለሁ...እንግዲህ ነገ የአመቱ ስላሴ በመሆኑ..ማልደዉ መድረስ እንዳይረሱ፡፡

እያሱ፡- ኧረ እመጣለሁ..እንዴት እረሳለሁ??

መርእድ፡- እሺ ደህና ይዋሉልኝ...(እጅ ነስተዉ ይወጣሉ፡፡ ጣሴ ተከትሎ

ይወጣል፡፡..ፋታ)

ጥላሁን፡- ጉግሳ ወሌ...ከበጌምድር ሸዋ ድረስ...ዘዉዲቱን እንዴት...

እያሱ፡- ራስ ተሰማ ነዉ፤ ‹ከእቴጌ ሁሉን ነጥቀን አናስኮርፋቸዉም› ብሎ ነግሮኛል...

ጥላሁን፡- እንዲያዉ ብቻ ነገሩ አላማረኝም...

እያሱ፡- ኧረ ጥሩ ነዉ...ለዘዉዲቱስ ያድርግላት፡፡ አረጀች እኮ በማጀት..ወይ እንደሌሎቹ መኳኳል አታዉቅበት..ይልቅ የራስ ተሰማን ሚስት ብታየት..

ጥላሁን፡- ወይዘሮ በለጥሻቸዉ??

እያሱ፡- በሹክታ...አንድ ፍሬ ልጅ ናት፡፡ ደሞ የአይነ ዉሃዋ ማማር..የሰዉነቷ ...ኧረግ..ደስ ማለቷ፡፡...በለጥሻቸዉ ሲያንሳት ነዉ!

ጥላሁን፡- ታዲያ እንዴት ብለዉ ያሳድሯታል እሳቸዉ?...የስኳር የጉበት በሽታ ደሞ አላቸዉ፡፡ እሳቸዉ ደም ብዛታቸዉ ወጣ ወረደ ሲባል ነዉ የምሰማዉ፡፡

እያሱ፡- የሳቸዉስ የራሳቸዉ ጉዳይ...ልጅቷ ነች የምታሳዝነኝ፡፡ በሐምሌ ብርድ ጥቅልል ብላ ብቻዋን ማደሯ፡፡...አይ አይን አገላለጥ፤ አከናፈሯ፡፡ የዳሌ አወራረድ...መቶ ፐርሰንት ሚት!!..አለ ሰዉየዉ!?

ጥላሁን፡- ምንም ፋት የሌላት!!

እያሱ፡- ኧረ ተወኝ ወዳጄ...እንዲያዉ ከሽማግሌዉ ላይ ምን ጣላት?

ጥላሁን፡- ‹እጅ ንሺ› ብለን እዚህ እናምጣት?..ወይስ ሰዉ በጎን እንላክባት?

እያሱ፡-አይ ቆይ አትንገሯት..ይልቅ ተፈሪን አስልክበትና ወደ አመሻሽ ጉግስ እንጫወት...

ጥላሁን፡- ደህና...አንተም ደህና መዉጫ ይሆንሀል፡፡ ስንት ቀን ተቀምጠሀ....(ከዉጭ

ድምፅ ይሰማል፡፡ ራስ ተሰማ ታጅበዉ ከጣሴ ጋር ይገባሉ...እጅ ይነሳል)

እያሱ፡- እንዴት ሰነበቱ ራስ ተሰማ...

ተሰማ፡- ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ...ከትናንት በስትያ እመጣለሁ ብዬ ወገቤን ቀስፎ የያዘኝ ነገር መቼ አስተኝቶኝ..

ጥላሁን፡- አኪሙን አማከሩት?

ተሰማ፡- አኪሙ ምኑን አዉቆት?...ከእሱስ ምክርና መዳኒት..ሰሞኑን አንድ ወዳጄ ከመሬቱ ተኛበት ብሎኝ..ይልቅ እሱ አሻለኝ፡፡ አሁን ሰሞኑን ደህና ነኝ...ያንን አዋጅ ስሰራ ከረምኩኝ..

ጥላሁን፡- መቼም እድሜዎ ረጅም ነዉ..አሁን እኮ ምነዉ ጠፉ ስንባባል ነዉ የመጡት..

ተሰማ፡- ስራዉ መቼ ፋታ ሰጥቶን..የሽግግር ዘመን አይደል..አሮጌዉ እንዳይወድቅ አዲሱም እንዲጠብቅ ብዙ ስራ አለብን፡፡...ቢሆንም የተባባልነዉን አዋጅ አርቅቀናል...

እያሱ፡- አለቀ ተፅፎ?

ተሰማ፡- አዎ ረቂቁ ይሄዉ..ና እስቲ ጣሴ ንሳማ አንብበዉ...(ጣሴ ወረቀቱን ይቀበላል)...የሳዩን ትተህ..ይሄ ‹አንደኛ› ከሚለዉ አንብላቸዉ...

ጣሴ፡- (ጉሮሮዉን ያፀዳል)...አንደኛ! ከዛሬ ጀምሮ ህፃናትን ልዩ የማሰብ ተሰጥኦ ይሰጣል፤ ትምህርት እንዲገባቸዉና ስዉር ነገር ጭምር እንዲመለከቱ ይረዳል፤ እየተባለ በግድ የሚጋቱትን የመንደር አብሾ የተባለ መዳኒት ብዙ ህጣናትን የውስጥ ደዌ የሚሰጥ ሆኖ በመገኘቱና አጉል የአእምሮ በሽታ የሚያመጣ በመሆኑ፤ ይህን

ምናምንቴ ቀላቅሎ ለህጣናት ሲሰጥ የተገኘ መዳኒተኛ፤ ወላጅ፤ ዘመድ፤ አሳዳጊ፤ ሰማንያ ጅራፍ በአደባባይ እንዲቀጣ።

ሁለተኛ፡ አባወራ የቤተሰብ ሀላፊ የሆነ ሰው፡ በፍርድ ችሎት አጥፊ ወንጀለኛ ሆኖ ሲገኝና ሲፈረድበት፤ ከአሁን ቀደም እንደሚደረገው... ሚስቱንና ንብረቱን ጭምር መነጠቅ መወረስ አይገባውም። በሱ ጥፋት ከራሱ በስተቀር ማንም እንዳይቀጣ። ልጆቹና ሚስቱም ምንም በደል እንዳይደርስባቸው። ንብረት ቤታቸዉ እንዳይነጠቅ እንዳይወረስ ይሁን። ከሳሽና ተከሳሽም በሰንሰለት ተቆራኝተውም በችሎት ፊት መቆማቸው ከዛሬ ጀምሮ የተከለከለ ይሁን። ከእንግዲህ ማንም በሰንሰለት አይታሰር።

ሶስተኛ፡ ከእንግዲህ በኋላ ማዕረግና ሹመት፤ ከአባት ወደ ልጅ፤ ከባል ወደ ሚስት፤ የማይወርድ የማይተላለፍ፤ በመወለድና በዘር ቆጠራ ሳይሆን በችሎታና በትምህርት ብቃት ብቻ እንዲፈፀም ይሁን። ኢትዮጵያ የጋራ ሀገራችን በመሆኗ በችግር በጦርነት ጊዜ የችግር የመከራዉ ብቻ ሳይሆን፤ በሰላሙም ጊዜ ከሚገኘዉ ጥቅሞም ሙላዉ ባላገር ተካፋይ እንዲሆኑና ንብረት እንዲያፈሩ ይሁን። (ጣሴ ወረቀቱን ይመልስላቸዋል)

እያሱ፡ የቆቱ የኦረሞዉ የጊሚራው የሻንጉሉ የከፋው፤ የጉራጌ የሸዋም የትግሬም የሌላውም አገር ባላባቶች የራሳቸውን ሹማምንት እየመረጡ አካባቢያቸውን እንዲያስተዳድሩ፤ ያልነዉስ?

ተሰማ፡- የትኛዉ?

እያሱ፡- ‹የብሄር የጎሳዉ አስተዳዳሪዎቹ ሁሉ ከዛዉ ከብሄሩ የወጡ እንጂ በምስለኔ በአፈንጉስ አይገዙ ያልነዉና...የአንዱን ባህል ሌላዉ ሊቀይረዉ ሊወቅሰዉ አይገባም፤ እንደ ባህሉ እንደ ሀይማኖቱ ይደር፤ ‹አንዱ ቅዱስ ብልህ ሆኖ ሌላዉን እርኩስ ተላላ ብሎ ሊያጠዳዉ ስልጣን የለዉም› የተባባልነዉ የት ገባ?

ተሰማ፡- እሱን...ባላባቱና መኳንንቱን የጦር ሹማምነቱን ሁሉ..የሚያስከፋ..ቤተ-ክህነትን ጭምር የሚያስቆጣ ስለሆነ...

እያሱ፡- ይከፋቸዋ!...እነሱ ይከፋሉ ብለን አገር ይበተን?

ተሰማ፡- አገርማ እንዴት ይበተናል?...የሚያምጥ ካለ ምሱን ያዉቀዋል። ይልቅ ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሯ ትሄዳለች እንደሚባለዉ...

እያሱ፡- አይ...ምንም ጊዜ ያለን አይመስለኝም። አሁን በጦር ያስከበርነዉ አገር..ጊዜ በሰጠዉ ቁጥር ህዝቡ ማመፁ አይቀርም። ይልቅ እርቀ-እግዚአብሄር እየፈጠርን..የታሰረዉን እያፈታን...በራሳችሁ ተዳደሩ..በጋራ በምናቋቁማት አገራችን ሁላችንም ተከባብረን እንኑር ካላልን...ለነገ ችግር ነዉ የምንፈጥረዉ።

ተሰማ፡- መቼም እንደኔ ሁሉም ችግር በአንድ መዓልት የሚፈታ አይደለም..ሽግግሩን ቀስ እያልን ነዉ የምናካሂደዉ።

እያሱ፡- ለምን ቀስ ያስፈልጋል!?

ጥላሁን፡- እዚህ ላይ ራስ ተሰማ ልክ ናቸዉ። ቀስ ብሎ መሄዱ መልካም ነዉ። በርግጥ ወጣቱ ለሽግግር ጓጉቷል...ለዉጥ እየጠበቀም ነዉ። ግና አሮጌዉም ያለዉን ማቆየት ስርአቱ እንዳይቀየር ይፈልጋል። ታዲያ እሳቸዉ እንዳሉት...ረጋ ብሎ በትንሽ በትንሹ እያደረጉ መሄዱ ብልህነት ነዉ።

ተሰማ፡- እኔም እንደሱ ነዉ የምለዉ...በርግጥ ወጣቱ በጣም ቸኩሏል...ታዲያ እሱን ለማስደሰት ሲባል ከአሮጌዉ መጣላት አያስፈልግም። ማቻቻል ነዉ የእኛ ስራ።

እያሱ፡- ይሁን...ይሁን ልበል እንጂ...ግን አንድ ነገር ማድረግ አለብን፡፡ የከተማዉን ወጣት እና ሽማግሌ ሰናስብ...ሌላዉ ብሄር በጦርነቱ በደል ግፍ ያኮረፈን...ቂም በቀል ለልጅ ልጅ እንዳያስተላልፍብን...በቶሎ ይቅርታን ማግኘት አለብን...አለቆቹን አመፀኛ ተብለዉ የታሰሩትን ሁሉ መልቀቅ በፍታት አለብን፡፡

ተሰማ፡- ሁሉንም?

እያሱ፡- አዎ ሁሉንም..ይሄ እጁን በወርቅ ሰንሰለት ታስሮ ቤተ-መንግስት ያለዉ የቁም እስረኛዉን ጭምር፡፡

ተሰማ፡- እነሱ ብዙ አይደሉም..የከፋዉ ንጉስ ጋኪ ሺሮኮ የሚሉትና የወላይታዉ...ኧ...

ጥላሁን፡- ሁሉም ቢፈቱ መልካም ነዉ፡፡ ያኮረፈንን ሁሉ ማሰር መቅጣት የለብንም፡፡ አድርባይነትን እና የዉሸት ወገንተኛነትን ነዉ የምንናበረታታዉ፡፡..የዉሸት ወገናዊነት መሰረት የለዉም፡፡ ይጥለናል ኋላ...

ተሰማ፡- መቸም...ፊታዉራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ እና ደጃች ወሰንን ጨምረን ለምን የእስረኞቹን ጉዳይ አንመክርበትም?..ግዳይ ምርኮዉ የእነሱዉ ስለሆነ...

እያሱ፡- በዚህ ምንም ምክክር አናደርግም!...መልካም ፈቃዳችንን የምናሳያቸዉ ለንጉሶቻቸዉ ለሀይማኖት መሪዎቻቸዉ ለባህላቸዉ የምናሳየዉ ክብር ነዉ...ያመፀዉን ሁሉ አስረን ገድለን አንጨርሰዉም ነዉኮ የምልዎት...

ጥላሁን፡- ይሄን እርስዎም ቀስ ብለዉ ማስረዳት አያቅትዎትም...

እያሱ፡- ይልቅ የሹመቱ ነገር ምን ደረሰ?

ተሰማ፡- ሁሉም ተላልፏል...ሲጋባዉ ዘንድ ነዉ ያለዉ..ሁሉም አልቋል...የፊታውራሪ ጥላሁን ስምም አብሮ ገብቶአል፡፡

ጥላሁን፡- ፊታውራሪ??...እኔ ነኝ ፊታውራሪ?

ተሰማ፡- እንዴት አልሰማህም? በከተማዉ የተናኘዉን ወሬ አንተ ዘንድ እንዴት አልደረሰም?

እያሱ፡- ራስ ተሰማ...ሁሉም ነገ በጃንሜዳ አዋጅ በአደባባይ ይነገር፡፡ አንዳንዱን ነገር መፍጠን አለብን፡፡

ተሰማ፡- እሱስ ልክ ነዉ..ህመም ይዞኝ መሬት እያስተኛኝ እንጂ.....ምኒሊክ ታመሙ ሲባል..ዝም ማለታችን ችግር ቢኖር ነዉ ብሎ ለሚያወራዉ አሉባልተኛ ክፍት መስጠት ነዉ፡፡

እያሱ፡- መልካም እንግዲህ... ይበቃል ይሄው ይታወጅ በየአጥቢያ ዳኛው ይተላለፍ... እርስዎም ትንሽ ይረፉ፡፡

ተሰማ፡- አይ ልጅ እያሱ..ምን እርፊት አለ...ቅዳሜ ማርቆስ ገብቼ ማደር አለብኝ...ዛሬ አመሻሽ ላይ እነሳለሁ ብያለሁ...

እያሱ፡- ምን ሊሲሰሩ?

ተሰማ፡- ማርቆስ የደጃች ሐይሉ ወንድም ልጅ ትዳራለች...ክስርጉ አልቀርም ብዬ ነዉ፡፡

ጥላሁን፡- እንዲህ እያመመዎት መንገዱም ይጎዳዎታል...

ተሰማ፡- ምን ይደረጋል?...ሰርግም ሞትም አንድ ቀን ነዉ፡፡

እያሱ፡- አይ...ወይዘሮ በለጥሻቸዉም ታግዝዎታለች?

ተሰማ፡- እሷስ አትሄድም…መንገዱን አትችለዉም…ደሞ በጋሪ ካልሆነ በቅሎዉን አትወደዉም፡፡…መንገዱ እንጂ…ሁለት ሶስት ቀን ያህል ብቆይ ነዉ እኔም፡፡

ጥላሁን፡- አይ ጥሩ ነዉ፡፡ እንደዛስ ከሆነ ምንም አይደል፡፡ ጣሴ እየሄደም እንዲጠይቃት እና የሚቸግር ነገር ካለም…

ተሰማ፡- ኧረ ምንም አትሆን እሷ…

እያሱ፡- እንግዲህ ሰላም አግብቶ ይመልስዎት፡፡

ተሰማ፡- አሜን ሰላም ያሰንብተን…(ተሰማ እጅ ነስተው ይወጣሉ.. ፋታ)….እሺ ፊታውራሪ ጥላሁን…

ጥላሁን፡- እሚገርም ነዉ…ከመሬት ተነስቼ ፊታውራሪ ሆንኩኝ??..(ፊቱን ይይዛል)

እያሱ፡- ለፊታውራሪነት ምን ያንስሃል?….ከድሃ መወለድህ፤ የእናቴ አሽከር ልጅ ከመሆንህ ውጪ ከሌላው ባላነስ ታስባለህ…ለዚች አገር አርቀህ አስበህ ትዉላለህ፡፡ ጨዋ ከሚባለዉ ዘር አለመወለድህ ካለሆነ….

ጥላሁን፡- አይ ከነ ፊታውራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ተራ ስታቆምኝ…ምን ይባላል አሁን….

እያሱ፡- ምን ይላሉ? ምን ይሆናሉ?…እነ ዲታሞ፤ ዋቅጂራ፤ ጀሞ ፤ ሸጌሙ፤ ቃ-ወጀሌ አብዱላሂ ሽርከዳ የሚባለዉ ሁሉ ቀኛዝማች ደጅአዝማች ሁነዋል፡፡

ጥላሁን፡- አቤት አቤት…አሁን ይሄ ሁሉ መኳንንት ቀሳውስት ምን ይላሉ? ስለ አዲሱ ባላባት…የድሀ ልጅ ሰብስብ እልፍኝ ያለ አስከልካይ ሲርመሰመስ….ምንድነዉ የሚባለዉ?..ገሚሱ የወተሊክን ዕምነት ሊያጠክናር ነው ሲል፤ ገሚሱ…

እያሱ፡- እባክህ ይባላል ተፈርቶ ሳይደረግ አይቀርም፡፡ ትምህርትና እውቀት እንዲሁም ለብቃት ትኩረት ካልተደረገ፤ በዘመድ በወገን ብቻ ስልጣኑን ብትይዘዉ ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ ነዉ፡፡ የወጣዉ ሁሉ ተንከታኩቶ መዉረዱ አይቀሬ ነዉ፡፡ ይሄ ትልክስክሱ ጨዋ…ከዲቃላ በቀር ለዚች አገር ያበረከተው ነገር ብዙም የለም፡፡

ጥላሁን፡- መቼም ብዙዎች ማኩረፋቸው አይቀርም፡፡

እያሱ፡- ብዙዎቹም ይደሰታሉ፡፡ ይሄ ሙክት የሚያካክለዉ ባላባት ቢያኮርፍ ምን ያመጣል?

ጥላሁን፡- የወንጀለኛ ንብረት ከነሚስቱ መውረስ መከልከሉ…በጅሮንድ እንዳይላሱን ሳይቀር የሚያናድድ ነው፡፡

እያሱ፡ ልጃቸው አስካለ ማርያም ትደሰታለች፡፡ ሌላው ደግሞ በዚህ በግቢ በቤተመንግስት ያለው መሳፍንት በከተማው በግብር የሚኖረው ባላባት ቁጥር፤ የቂስ የቀዳሹ ሳይቀር እንዲቀንስ ይነገራል፡፡…በቀረጥ ግብር ተቀምጦ የሚበላዉ ተሚሰራዉ ከበለጠ፤ የሚሰራዉን አጫጭቶ ይገለዋል…ሁላችንም እንጠፋለን ከዛ በኋላ

ጥላሁን፡- ይሄ የሚሆን አይመስለኝም…አፄ ቴዎድሮስ ሞክረውት ጠላት አብዝቶባቸው እንግሊዝ ከጓሮአቸው መጥቶ እስኪሰፍር ድረስ ወሬውን አልሰሙትም ነበር ይባላል፡፡ እሚነግራቸዉ ጠፍቶ፡፡ ይሄ ሁሉንም የሚያስነሳሳ ነዉ፡፡ ራስ ተሰማ ‹በእርጋታ› የሚሉት ትክክል ነዉ፡፡…እቴጌን ጭምር የሚያስቆጣ እና

እያሱ፡- እቴጌ ምን ያመጣሉ?

ጥላሁን፡- ቀላል ሴት አይደሉም፡፡ እሳቸዉንም በመላ ብትይዛቸው ይሻላል፡፡

እያሱ፡- የለም ቦታው ይፈለጋል፡፡ ብዙ ባላገር አምጠቼ ነው የምሞላበት፡፡ መጥተዉ ከትምህርት ይገባሉ፡፡…አዲሱ ትውልድ ለውጥ ይፈልጋል፡፡ አዲስ ሹማምንት ማየት

ይወዳል፡፡ እንደ ዘመነ መሳፍንት የዘር ሐረግ እየቆጠሩ መዋጋት ያበቃል፡፡ ሁሉም ብሄር ራሱን ያስተዳድራል፡፡ ፌዴራሲዮን ይኖረናል፡፡ ...ጊዜው ተለውጧል...ሹመት ያዳብር ፌታዉራሪ!!

ጥላሁን፡- ፊታውራሪ?! ይገርማል!... ምን እላለሁ ጌታዬ...ጦር ሳልሰብቅ ሳልገድል... እኔም ከሰው ተራ ልሆን እኮ ነው...ይገርማል...(እጅ ይነሳል...ይስቃል)

እያሱ፡- ቅድም አልኩህ እኮ...የቆቱውም.. የጅሌው...የመቱ የነቀምቱ...የሊባቦሩ የሀረሩ...የጊሚራው.. የሻንጉላው የዘላኑ የአፋሩ ልጆች ሁሉ ፊታውራሪ ደጃዝማች ይሆናሉ፡፡ ይሄ የሰሜኑም የመሀል አገሩም ሰዉ አብዛኛዉ ድሀ ነዉ፡፡ ፍትህ የለዉም፤ በቅን የሚያስተዳድሩት የሚያግዙት የለዉም፡፡ ኩራት ራት አይሆነዉም፡፡ ...ፍርሀቴ ግን ምን መሰለህ?

ጥላሁን፡- እቴጌ?

እያሱ፡-አይደለም...ጣልያኑ እና እንግሊዙ ነዉ፡፡ ቅድምም ብዬሀለሁ...እዚች ከጎናችን ተቀምጦ የጥላቻ መርዙን ሳይበትን የጠረፍ አገርን ለመጠበቅ የላላውን ማጥበቅ፡፡ ሁሉንም በእኩል ጥቅም ማስተዳደር..(ጣሴ ይገባል)...ማን መጣ?

ጣሴ፡- ሰኞር ባንተሎኒ...ጃንሆይን ማየት አለብኝ ብሎ ዉጭ ተቀምጧል...‹ዛሬ ደግ አይደሉም› ብለዉም አልሄድም ብርቱ ጉዳይ አለኝ ነዉ የሚለዉ፡፡

እያሱ፡-አስገባዉ ይሄ ነጫጭባ...የጣልያንና የእንግሊዝ አለው ገና ብዙ መዘዝ...ምን ብታርቃቸዉ ፊት ብትነሳቸዉ...አይለቁንም...አንድ ነገር አላቸዉ፡፡ እዚች አገር የሚያልከሰክሳቸዉ፡፡(ጣሴ ፓንታሎኒ አስከትሎ ይገባል፡፡ እጅ ይነሳል)..ምን ብናደርግ በር ብንዘጋ...ጭራሽ አትመልሳቸዉም፡፡

ጣሴ፡- (ለፓንታሎኒ)...ጃንሆይ ልጅ እያሱ ‹እንዴት ከርመሃል› ይላሉ፡፡

ፓንታሎኒ፡- (እጅ ይነሳል)...ደህና ነኝ ጌታዬ፤ የእርስዎ አምላክ ይመስገን በጣም ደህና ነኝ፡፡ ‹እርስዎስ እንዴት ከረሙ?› በልልኝ...

እያሱ፡- በጎን በሶማሌ ቆቱዎቹ ያሳድማሉ በምዕራብ ሻንጉሎቹን ሱዳንን ተቀላቀሉ ይላሉ፤ የማህዲን ሽፍቶች ይልካሉ፡፡ ከላይ ከመረብ ምላሽ ያሉ ትግሬዎችን ሆድ ያሻክራሉ፤ እዚህ መሃል ደግሞ አንድ ውዳቂ የእህል ወፍጮ አምጥተው ስሰ ስልጣኔአቸዉ ይደሰኩራሉ!!...

ጣሴ፡- (ለፓንቶሎኒ)...‹በጣም ደህና ነኝ... በደህና ነኝ፡፡ በደህና ነው ወይ አመጣጥህ› ይላሉ፡፡

ፓንታሎኒ፡- የጃንሆይን አልጋ ወራሽን ደህንነት ለመጠየቅ እና በአገርዎና በታላቁ የጣልያን አገር መንግስት መሀል ያለውን ግንኙነት፤ በዳግማዊ ምኒሊክ ዘመን ከነበረው በበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል የመንግስታችንን መልካም ፈቃድ እንዳቀርብ በመታዘዜ፤ ከፊትዎ ቆሜ ይሄንኑ መልዕክቴን ለማድረስ የርስዎን ፈቃድ እሻለሁ፡፡ (እጅ ይነሳል)

እያሱ፡- ‹‹በአገርህና አገሬ ያለውን መልካም ግንኙነት›› አለ? በጉልበታችን በአንድነታችን በአድዋ በዉጫሌ በየዱሩ፤ በየቱቦዉ ስር በወደቁት ልጆችዋ የተገኘ እንጂ፤ እንደ እናንተማ ቢሆን ዛሬ እንደ አህያ ጭናችሁ ወገኔን እንደ በሬ ታሳርሱት ነበር፡፡ ይሄ አበሻ አሳፍሮ ነው የሰደደው፡፡ ግን የቆሰለ ቂም አለው፡፡ መቼ እንደሚወጉን አይታወቅም እንጂ የጣልያን በቀሉ የማይቀር ነው፡፡

ጣሴ፡- (ለፓንታሎኒ) ‹መልካም ነው! መልካም ወዳጅነታችሁን በመከባበር ላይ የተመሰረተ በመሆኑ እኛም ፈቅደነዋል› ይላሉ ጃንሆይ፡፡(ፓንታሎኒ እጅ ይነሳል)

ፓንታሎኒ፦ ባለፈዉ ጊዜ ኢታልያ ሮማ ለጉብኝት ከመሄዴ በፊት በጃንሜዳ ያነሳኋቸውን ፎቶዎችን እንዳሳይ ይፈቀድልኝ፡፡...(ከቦርሳው አውጥቶ ብዙ ፎቶዎች ያቀርባል)... (ሁሉም ወደ ፎቶው ያተኩራል...ፓንታሎኒ የተጣለውን ጋዜጣ አንስቶ እየተመለከተ)...ጃንሆይ ይሄንን መጥፎ ጋዜጣ ባያነቡት ጥሩ ይመስለኛል፡፡ ይሄ የጀርመን ኮምኒስቶች ‹ሶሻሊዝም› የሚባል መጥፎ በየትም አለም ያልተሞከረ፤ የበዘኔ መናፍቃን ስርዓት ለመፍጠር የሚጥሩ፤ መልካም ያልሆኑ ሰዎች የሚፅፉት አሳሳች ፕሮፓጋንዳ በመሆኑ፤ ጃንሆይ እንዳይሳሳቱብን ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

እያሱ፦ ውነትህን ነው? መች አውቄዉ ብለህ....

ፓንታሎኒ፦ ፍቃድዎ ከሆነ በታላቅዋ ሮማ ምርጥ ምሁራን የሚታተሙ መልካም ትምህርት ያላቸው መጣጥፍት፤ ከጀርመንና ከኦስትርያ አደናጋሪ ፕሮፓጋንዳ የፀዳ፤ መቶ በመቶ ታማኝነት ያላቸውን ሳይንሳዊ ጽሁፎችን ለእርስዎ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ ዘንድ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡

እያሱ፦ (ፎቶዎቹን እየተመለከተ)... መልካም ነው....(ፎቶዉን ከጥላሁን ጋር ይቀባበላሉ)...ንሳማ ይሄን እየዉ...( እየተመለከቱ ይሳሳቃሉ)

ፓንታሎኒ፦ ጃንሆይ...የጣሊያን ህዝብ ይወድዎታል፡፡

እያሱ፦ እውነት?

ፓንታሎኒ፦ በሚገባ ጃንሆይ.. የርስዎን ፎቶ ያዩት ሁሉ...እንዲህ ያለ መልከ መልካም ንጉስ በአፍሪካ መኖሩ ይገርማል በማለት ነዉ የሚናገሩት፡፡

እያሱ፦ ይሄኔ ‹ቁርስ ራቱን፤ የሰዉ ሥጋ ነዉ የሚበላዉ› ተብያለሁ....

ጥላሁን፦ እሱማ እንግሊዝ ፈረንሳይ ቤልጅግና ፖርቱጋል መላዉ አፍሪካን የተካፈሏት ..ነዋሪዉ ህዝብ እርስ በርሱ እንደ ጅብ ተበላልቶ እንዳያልቅ መልካም የሚሲዮን የማሰልጠን ስራ ለመስራት ነዉ፤ እያሱ እኮ ነዉ፡፡

እያሱ፦ (ፎቶ እየተቀባባሉ...ጣሴም እየተቀበለ ይመለከታል)...በላይ በሰማይ ሊጠድቁበት...እያሰሩ እየገረፉት፤ መርዝ በሽታ ከሆዱ እየቀበሩበት...

ጣሴ፦ ተበተቡት...በግና ፍየል የት ሄዶ ነዉ ሰዉ ሰዉን የሚበላዉ? ...ከተቸገረማ እንግሊዙም እንግሊዙን ይበላዋል፡፡ ምን ያረገዋል ጠኔ ከያዘዉ?..ሶሪ ታንኪዉ ብሎ ነዉ የሚዘነጥለዉ!...(ከፓንታሎኒ በስተቀር ሁሉም ይስቃሉ)

ፓንታሎኒ፦ ምንድነዉ?...የሚያስቅ ፎቶ የቱ ነዉ?

እያሱ፦ ሁሉም ግሩም ነዉ...ንሳማ ይሄን እየዉ../ፎቶ ይቀባበላሉ/...

ፓንታሎኒ፦ ጃንሆይ...በተለይ ይሄን ፎቶ ያዩት የጣልያን ቆነጃጅትና የመሳፍንት ሴት ልጆች ... በሮማና በፓሌርሞ እና ሚላኖ ያሉት ሁሉ፤ መልኩ ሲሲሊያኖ ..ይመስላል..ቆንጆ ቤላ ቤላ! ልጅ ነዉ..ይላሉ ፎቶዉን እየሳሙ፡፡

እያሱ፦ ይሄን ያህል?

ፓንታሎኒ፦ በጣም እንጂ ጃንሆይ...በተለይ ልዕልት ዮላንዳ የምትባል ታላቅ ውብ ልዕልት... (ፎቶ ይሰጣል)... ይቺ ውብ ልዕልት መቼም ጃንሆይ እርስዎን ለማግኘት በጣም ነው የምትጓጓዉ...(እያሱ ፎቶዋን በአድናቆት ይመለከታሉ፡፡) መቼም አግቢኝ እንኳ ቢሏት እምቢ የምትል አይመስለኝም፡፡

እያሱ፦ ዉነትህን ነዉ?..አገሬ ስንት ቆንጆ ሞልቶ፤ ምን ትሰራልኛለች...

ፓንታሎኒ፦ በጣም እንጂ ጃንሆይ..ለምን ደብዳቤ አይፅፉም?...እኔ ራሴ ዛሬ ማታ

በቴሌግራም እልከዋለሁ...እሷን ቢያገቡ እኮ ኢትዮጵያና ኢታሊ አንድ አገር ጎዶኛ ይሆናሉ፡፡

እያሱ፡- ጎዶኛ...ጎዶኛ ጥሩ ነበራ...ግሩም ነበር፡፡ ይልቅ ባለፈዉ ከዋና ዉሃዉ ልገባ ስል በቁምጣ ያነሳኸኝ የታለ?...

ፓንታሎኒ፡- የትኛዉ ጃንሆይ?

እያሱ፡- ራቁቴን ያነሳኸኝ...‹ወዲህ በል፤ ተንጋለል፤ ሳቅ በል› ስትለኝ ዉለህ...

ፓንታሎኒ፡- እሱ ፎቶ ገና እየታጠበ ነዉ..ሮማ ነዉ ያለዉ..እሱ ቀጥሎ ይመጣል...ይልቅ አሁን ብዙ ፊልም ስላመጣሁ ብዙ ፎቶ አነሳዎታለሁ....ፎቶ ማንሳትና ማባዛት ሁሉ አስተምርዎታለሁ...አዲስ ካሜራ ፎቶ የሚያነሳ አምጥቼለዎታለሁ፡፡

እያሱ፡- ግሩም ስጦታ ነዉ...አመሰግናለሁ፡፡....ግና ምናለ የሚጠቅመን..አንዲት በዉሀ የምትሰራ ወፍጮ ወይ በፀሀይ ብርሀን ብቻ ዉሀ የምናፈላበት ማንቆርቆሪያ ቢያመጣልን....ንሳማ ይሄን እየዉማ...

ጣሴ፡- /ለተመልካች/...በዉሀ እና በፀሀይ ኃይል ብቻ ማረስ መቆፈር እና መብራት አብርተን ምግባችንን ከአበሰልንማ ራሳችንን እንችላለን...ግን ማን ይፈቅድልናል?.../ልጅ እያሱ እና ጥላሁን ፎቶ እያዩ ይስቃሉ/...

ፓንታሎኒ፡- ለጃንሆይ ልጅ እያሱ...ፎቶ የሚያትም ‹ፕሪንተር› የሚባል አስገራሚ ፎቶ የሚያትም ማሽንም አምጥቼለዎታሁ፡፡

ጣሴ፡- ምን አለ?...ፕሪንተር?....‹ስሪ ዲ› የሚሉትን ከሆነ ግሩም ነዉ!!!...አይሰጡንም እንጂ...

እያሱ፡- ጥሩ ነዉ....(ፎቶዎቹን በየተራ ከጥላሁን ጋር ሲቀባበሉ ራስ ተሰማ ተቻኩለው ይገባሉ)

እያሱ፡- ራስ ተሰማ?...ምነው ተመለሱ? በደህና?

ተሰማ፡- ደጃች ወሰን ፊታዉራሪ ሀብተ ጊዮርጊስን ስጠይቅ አግኝቻቸዉ...ብርቱ ጉዳዬን ዛሬዉን ካላደረስክልኝ፤ ቢሉኝ ያዉ በመንገዴ ሳልፍ ተመልሼ መጣሁኝ፡፡

እያሱ... ብርቱ ጉዳይ?

ተሰማ፡- ብርቱ የአገር ጉዳይ ስለሆነ እንግዳዉን ያሰናብቱት እና...

ጥላሁን፡- ኧረ እኔም ልሂድ እና ለተፈሪ ያልከኝን አደርሳለሁ...ከዚያ በፊትም ወደ ቤት እገባለሁ፡፡

እያሱ፡- እሺ...ፊታውራሪ ጥላሁን... የፖሊሶቹን ስልጠና ስትጀምር ትወስደኛለህ...(ጥላሁን ሁለቱንም እጅ ነስቶ ይወጣል.) ሚስተር ፓንታሎኒ ነገ ማለዳ ብትመጣ በጣልያን ስላለው ሁኔታ እንነጋገራለን...( ጣሴ በምልክት እንዲወጣ ያሳየዋል፡፡)

ፓንታሎኒ፡- አመሰግናለሁ ጃንሆይ...ግራሴ..ግራሴ!...(እጅ ነስቶ ይወጣል፤ ጣሴ ይከተለዋል፡፡)

ተሰማ፡- ደሞ ምን ሊሰራ መጣ ይሄ ባንተሎኒ?

እያሱ፡- አይ ፎቶ የሚሉትን አንስቶኝ የነበረዉን ሊሰጠኝ መጥቶ ነዉ፡፡ ...ይልቅ ምን ገጥሞዎ ከመንገድ መለሰዎ?

ተሰማ፡- ደጃች ወሰን ናቸዉ፡፡ እሳቸዉ የሚሉት (ግራና ቀኝ ተመልክተዉ..ለስለስ ባለ

ሁኔታ) ...እቴጌን ‹ከቤተ መንግስቱ ለቀው ይውጡ ማለት ዛሬዉኑ ይቁም› ነዉ የሚሉት።

እያሱ፡-ትተን የለም እንዴ እሱንማ?

ተሰማ፡- የለም...ገብረማርያም የሚባለዉ የላይ ቤተመንግስት የጠባቂዎቹ አለቃ....ጦር ቢጤ እየሰበሰበ...በቤተመንግስቱ ረብሻ ለማንሳትና..የታመሙትን ንጉስ ‹ልጅ እያሱ አዉጥታችሁ ጣሉ› ብሏል እያለ መኳንንት ባላባቱን ለሁለት ለመክፈል እየተሞከረ ስለሆነ...የልጅ እያሱ ሰዎች ለጊዜዉ ከዋናዉ ግቢ ይራቁ፤ ነዉ የሚሉኝ ደጃች ወሰን።

እያሱ፡- እንዴት ነዉ ይራቁ ማለት?...እሺ ብለን ተስማምተናል፤ ከእስዎም ጋር ተነጋግረናል። እንዲሁ ለወሬዉ ይበሉት እንጂ ማንም አይሄድም።

ተሰማ፡- እኔም አልኳቸዉ..ማንም አያደርግም አሁን ብላቸዉ፤ ግዴለም እንደገና አስረግጠህ አስረዳልን፤ በማለታቸዉ ነዉ የመጣሁት።...ለወሬ ቀዳዳ፤ ለጠበኛም ምክንያት መስጠት አይገባንም። የእርስዎን አልጋ ወራሽነት የሚወድ እንዳለ ሁሉ የሚጠላም ስላለ...መጠቀሚያ እንዳያረጉት..አንዳንድ ነገር ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ያስገድዳል።

እያሱ፡- ትቻለሁ...እሳቸዉም ይሄ የባቡር ስራ ገፍቶ እንዳያልቅ በጎን የሚልኩትን ሰዉር ተንኮል ከአቆሙልን...ከእንግዲህ ማእድም ቢሆን አብሬ አልቆርስም!...

ተሰማ፡- የለም መላ ዘዴኛ ነዉ መሆን ያለብዎት...ንጉስ አያኮርፍም...አገር ማስተዳደር ሆደ ሰፊ መሆንን ይጠይቃል። እቴጌ ሁላችንንም ነዉ የሚቆጡት። ሀዘንተኛ ስለሆኑ በሚናገሩት ማኩረፍ የለብዎትም። እኛም አለን ምክር ለማካፈል..እድሜ የሰጠንን ተሞክሮ ሌላዉ እንዳይሞኝ እንዳይሳሳት ምክር ብልሀት እንሰጣለን...ተሳሳትኩ እንዴ?

እያሱ፡- የለም ልክ ነዎት....እንዲያዉም ምክር ብልሀት ቢሉኝ፤ አንድ ነገር ትዝ አለኝ...ብቻ ከመንገድ እንዳላስረፍድብዎት...

ተሰማ፡- ኸረ ገና ሰአት አለን...ጓዛችነን ስለቀነስን ብዙም አንቸገር አሁን..ምንድነዉ የሚጠይቁኝ?

እያሱ፡- እንዲያዉ...የርስዎን ምክርም መጠየቅ እፈልግ እና መልሼ ፈራ ተባ ስል...

ተሰማ፡- ምኑ ነዉ ፈራ ተባ የሚያሰኝዎ?..ያሻዎትን እንዲጠይቁኝ አይደል ሞግዚትነቴ?

እያሱ፡- አንድ በልቤ የሚብላላ ጉዳይ...

ተሰማ፡- ምንድነው ይንገሩኛ...ብርቱ ጉዳይ ነው?

እያሱ፡- አዎ... በጣም ብርቱ ጉዳይ...

ተሰማ፡- እንግዲያው... ይንገሩኛ

እያሱ፡- (ጠጋ ይሉና) ...እንዲያው...አንዲት ልጅን ፈቅጃት ነበር ላገባት...

ተሰማ፡- ሰብለ ወንጌልን ትተዋት?

እያሱ፡- ለምንድነው የምተዋት?

ተሰማ፡- አልገባኝም የሚሉኝ...እንዴት?...በትዳር ላይ ትዳር ነው የሚሉኝ?

እያሱ፡- (ግራና ቀኝ ተመልክቶ) ...እንደሱ አይነት ነገር...

ተሰማ፡- እንደዚያማ እንዴት ይሆናል?.... የሰብለ ወንጌል አባት... ማለቴ የጎጃሙ ንጉስ

ራስ ሀይሉ...ምን ይላሉ? በልጃቸው ላይ ቢደርቡ?...ወይስ ሲቀልዱብኝ ነዉ?

እያሱ፡- ኧረ እኔስ ከምሬ ነዉ፡፡

ተሰማ፡- የለም መልካም አይሆንም ለስምዎ፡፡ በርስዎና በእመቤታችን መሀል ነገር ቢገባ እንኳ...ምህረት ማዉረድ ካልተቻለ እዚህ ከጨዋው ዘር ተመርጦ...ለንጉስ ምትሆን መልካም ሴት ከወሎ፡ ከትግሬ፡ከበጌምድር ወደ ካማራ ሳይንት...የምትሆን መልከ መልካም እመቤት፤ አትጠፋም ቆንጆ ሴት፡፡

እያሱ፡- ራስ ተሰማ...የሐረርዋን የሃጅ የአብዱላሂን ልጅ ቢያዩዋት...መልካም አባት ያሳደጉዋት መልካም ጠባይ ያላት፡፡ ብልህ አስተዋይ ልጅ ነች፡፡

ተሰማ፡- እና ሰብለወንጌልን ሊተዋት?

እያሱ፡- ምን አረገች ብዬ ነው የምተዋት?...ሁለቱንስ ባገባቸዉ?

ተሰማ፡- ሲቀልዱኝ ነው???.

እያሱ፡- ኧረ ከምሬ ነው...

ተሰማ፡- መቼም በትዳር ላይ ትዳር...እንኳን በንጉስ አልጋወራሽ፤ በማንም ተራ ገበሬ ወፍ ዘራሽ ዘንድ ጭምር ያልተለመደና ከባህል ወጋችን ውጪ የሆነ፤ እንግዳ ጉዳይ ነው፡፡

እያሱ፡- ምኑ ነው ከባህል ወጋችን ውጪ?...(ተሰማ ሊናገሩ ይቃጣሉ፡፡) አሁን ከእርስዎ ልጀምርና እስቲ እውነቱን ይንገሩኝ? እንዲያዉ ሳይደብቁኝ...ከሚሽቱ ውጪ አልሄድኩም ይሉኛል?? በማርያም ይምሉልኛል?...ይበሏ...

ተሰማ፡ መቼም ከወግ ከደንቡ ወጥቼ...በትዳር ላይ ትዳር አልደረብኩም...ወግና ስርአቱ አይፈቅድማ፡፡

እያሱ፡- (በርጋታ)....እኔ ይሄ ወግና ስርዓት የሚሉኝ ነው የማይገባኝ፡፡ የጭን ገረድ፡ አጉራሽና አልባሽ እያሉ ውሽማን ይዞ አገር መዞር... የተወለደውን ልጅ መካድ...ዲቃላ ማበራከት ከሆነ ወግና ስርዓቱ እኔ አይገባኝም፡፡ ከዚህ ሁሉ የምኒሊክ ባላባት መኳንንት ከጭን ገረድ ከአሽከሩ ከአልባሹ ያልወለደ ስንት ነው? ቁጥሩ በጣም ትንሽ ነዉ፡፡ ግን በእኔ ሲሆን ነው ነውር የሚሆነው?...

ተሰማ፡- አባባሌ...ዉሽማ መያዝ ማስቀመጡ...ማግባት አይደለም፡፡...ፈጣሪም አይፈቅደዉ፡፡

እያሱ፡- ፈጣሪ ምኑን ነዉ የሚከለክለዉ?...ወረቀት መፈራረሙን ነዉ?...

ተሰማ፡- በቅዱስ መጥሀፍም እንደተጠቀሰዉ፡፡

እያሱ፡- ቅዱስ መፅሀፍማ የሚለዉ..‹የቀኝ አይንህ ፍትወት ቢያስብ አዉልቀህ ጣለዉ› ነዉ..‹እጅህም ከሄደ ቁረጠዉ› ይላል..ማነዉ እሲቲ ቆርጦ የጣለዉ፤ አይኑን ፍትወት ተመኝቷል ብሎ አዉጥቶ የጣለዉ?

ተሰማ፡- መቸም እህ ብለው ከስሙኝ... የባህላችንን...የዘሬን ብተወው ያንዘርዝረኝ ሆኖብን፤ ከአባቶች ተቀብለን ሽፍነን ደብቀን የያዝነው ቢሆንም፡፡ ይህ የምናስተዳድረው ህዝብ እንዳይንቀን እንዳይርቀን...በመላ በብልሀት... የያዝነው፣ሚስጥር ነው፡፡

እያሱ፡- አይ አልሰሙምና...እረኛ የሚያወራውን አዝማሪ የሚገጥመውን የሚዘፍነዉን፡፡ ፀሃይ ሞቆ ያረጀውን፡፡ እርስዎ ስላልሰሙት ብቻ ነው ድብቅነቱ? ሚስጥር ይሆናል እርስዎ ፊት ስላልተናገሩት?

ተሰማ፡- ጌታዬ ልጅ እያሱ…ይሄ ከባህል ውጪ መሄድ ቤተ-ክህነትም የማትወደው… ኋላ አጉል ነው የሚሆነው፡፡ የኔ ተግባር እርስዎን መምከር መርዳት፡፡ የእርስዎ ከእስላሙ ጋር አብሮ መዋል ማደር፤መብላት መጋባት…ኋላ ሰለመ ከተባለ ችግር ነዉ፡፡ የሽሀ አብዱላሂን ልጅ ከአገቡ ‹አቤቶ ልጅ እያሱ እስላም ሆኑ› ተብሎ ሌላ መዘዝ ነዉ የሚመጣብን…ይልቅ ሌላ ነገር ከሌለዎት ሳይመሽ መንገድ መጀመር አለብኝ…ባይሆን ሌላ ጊዜ ቀስ ብለን እንመክራለን፡፡

እያሱ፡- እንግዲያውስ ይበሉ በጊዜ ይሂዱ በነገር አልያዝዎ…መንገድ እንዲይዙ ሳይመሽብዎ …አርብ ይድረሱ በጠዋት…ችሎት ይቆማል የዛን እለት..እኔም አብሬዎት እቀመጣለሁ፡፡

ተሰማ፡- አደርሳለሁ ሐሙስ ማታ፡፡ሰላም ያገናኘን የኔ ጌታ..(እጅ ነስተው ይወጣሉ፡፡…ፋታ…)

እያሱ፡- (ይንጎራደዳሉ)… እዳ የሆነ አገር፡፡…ሁሉ አዋቂ አይመከር፤ አሮጌ እውቀት አይቀየር፡፡ አይናማው እውር ተበራክቶ፤ ገደል ገባ ተንኮታኩቶ፤ የሚመራዉ ሞቶ፡፡ እንዴት ይዘለቃል ከቶ፡፡…ማ ነበር እንዲህ ብሎ የዘፈነው አዝማሪው?….

ጣሴ፡- (ይገባል)…የሚበላ የሚቀመስ ደርሷል…ገበታ ይቅረብ እንዴ?…./ፋታ/…ራስ ተሰማ አስር በቅሎና አሽከር አስከትለው…በሰላም የቀበናን ወንዝ ተሻግረዋል፡፡

እያሱ፡- መልካም ወሬ ጣሴ….

ጣሴ፡- ፊታዉራሪ ጥላሁን ነዉ የላከኝ ብላ አንዲት ሴትም መጥታለች

እያሱ፡- ማን ትባላለች?

ጣሴ፡- (በጆሮአቸዉ ሹክ ይላል)…በርግጥ ወጣት ናት፡፡

እያሱ፡-ጥሩ ነዉ…ብቻዋን በባዶ ቤት…እልፍኝ ትምጣና ትረፍ ትጫወትበት…እንደ ባህላችን እናስተናግዳለን…ጭካኔ ነው ዝም ማለት፡፡

ጣሴ፡- ፈጣሪም አይወደዉ፡፡ ‹ብዙ ተባዙ› ያለ ጌታ፤ መልሶ ያንኑ ትጋታችነን አይከለክለንም፡፡

እያሱ፡- ጥልቅ ትምህርት…አገራችን ሰፊ ነዉ..እኛን አትዋለዱ ብለዉ መሬቱን ሊወስዱት?…በበሽታ እየጠረጉን፤ ስደት እያጓጉን፤ አገራችንን እያስጠሉን….ጣልያን እንግሊዙ ፅሮ የሰጠንን ነዉ እኮ እንደ ስልጣኔ የሚያስተጋቡት…አይመስልህም??

ጣሴ፡- አልገባኝም…(ለተመልካች)…ገብቶኛል አዉቄ ነዉ፡፡

እያሱ፡- ይሄን አፍሪካን በቅኝ የያዙት ጆቦች ያመጡብን የስልጣኔ ወሬ ነዉ ሁሉም፡፡ የረቀቀ ጥበብ ነዉ፡፡ እኛን ለማደንዘዝ፤ አገራችንን ለመበርበር፡፡ ሁላችንንም አክስረዉ በገንዛ አገራችን ጭምር ስደተኛ ሊያደርጉን፤ እርስ በእርስ ሊያናቁሩን…

ጣሴ፡ እንዴት ማለት?…

እያሱ፡- ጣሴ…አሁን ይሄ ምኑ ይጠፋሀል?…ይልቅ እንግዳይቱን ወደ ዉስጥ አስገባት፡፡ ብዙ ደጅ አታስጠናት…(ጣሴ በፍጥነት ይወጣል…በአገር ባህል ልበስ የተሸፋፈነች ሴት ተከትሎ ይመለሳል፡፡ መድረኩን አቋርጣ አልፋ ትገባለች፡፡ ሁለቱም በአይን ይከተላሉ)….አህሀ…‹ጥበብን ስታልፍ ማየት የሚችሉ፤ መንገዷን የሚያቀኑ ጥቂት ናቸው፡፡ የተቀሩት ቀሚስዋን ይዘው የማያስኬዱ ጋሬጣ ናቸው፡፡ ለዝንብ መራቢያ የሚሆን የቆሻሻ ክምር እንጂ፤ ማር የሚሰራ፤ ንብ የሚያድርበት፤ መልካም መዓዛ ያለው ቀፎ መስቀል አይችሉም፡፡› ማን ነበር ፈላስፋዉ እንዲህ ያለዉ ጣሴ?

ጣሴ፡- ኧረ ምን አዉቄ ጌታዬ…(ለተመልካች)…ራሳቸዉ ልጅ እያሱ ናቸዉ፡፡

እያሱ፡- እና አሁን ንብና ዝምብ በአንድ ያድራሉ፤ ጣሴ?

ጣሴ፡- ኧረ በጭራሽ...ለየቅል ነው አዳራቸው፡፡ ንቢት...በዚህ ስትገባ (ሴትየዋ የገባችበትን ይጠቁማል)... ዝንቢት ግን... በዚህ በሌላው ገጥ ታልፋለች....

እያሱ፡- እንግዲህ ጤነኛ የሆነ ሰው አይኑ እያየ ዝምቢቱን ይከተላል??...(መንገድ ይጀምራሉ).....

ጣሴ፡- ኧረ በጭራሽ እንዴት ንቢት እያለች ዝንቢትን ይከተላል? ትክክል ብለዋል!

እያሱ፡- እንግዲያዉስ ንቢትን ላዋያት፡፡.

ጣሴ፡- ግን አሁን ባላባት መኳንንቱ ቢመጡ ምን ብለን እንመልሳቸዉ? ቃላችን ይሰማ፤ ብርቱ ጉዳይ ይዘናል ካሉስ ምን እንበላቸዉ?

እያሱ፡- ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? አሁን እኔም ብርቱ ጉዳይ ይዣለሁ፡፡ ባይሆን ነገ ረፋድ ላይ ተመለሱ በላቸው፡፡ ቢያሻህ...ንቢት በእልፍኝ ገብታበት እሷን ያባርራል ሊይዛት፤ በልልኝ፡፡ መቼም ‹የልጅ ነገር› ነው የሚሉት፡፡ አደራ ማንም እንዳያስተጉዋጉለኝ፡፡ በጣም ብርቱ ስራ ነዉ የሚኖረኝ፡፡

ጣሴ፡- ልክ ነዎት፡፡ ከዚህ በላይማ ምንም ብርቱ ጉዳይ የለም...(ጣሴ እጅ ይነሳል...እያሱ ወደ ውስጥ ሲያመሩ መብራት ይጠፋል)

<u>ገቢር ሁለት</u>

ትእይንት 1.

(ተኩስ ግርግር ይሰማል..በጨለማዉ የሚሮጡ መሳርያ የያዙ ሰዎች ይታያሉ፡፡ ተኩስ ጋብ ሲል፤ ድቤ መንዙማ ይሰማል፤ ከርቀት መስጊድ ‹አዛን› ፤የቤተ-ክርስቲያን ደዉል ይሰማል፡፡ .መብራት በዝግታ ሲበራ የተሸፋፈኑ ሰዎች ,ተቀምጠዉ ወዲህ ወዲያ ይወዛወዛሉ፡፡ እጣን ጭስ አለ፡፡ ጣሴ እየፎከረ ይገባል..መብራት ወደ ጣሴ ያተኩራል፡፡)

ጣሴ፡- ዘራፍ የእያሱ አሽከር!!..ዘራፍ ዘራፍ!! ማነህ አንተ!! ቁም!!! እንዳትበላሽ!!. ..(ይስቃል).. ልጅ እያሱ ራሳቸዉ..ቀን የሰለጠነዉን ቡሊስ ማታ ማታ ከጓደኞቻቸዉ ጋር ጥይት በአናቱ እየተኮሱ ያስበረግጉታል...ብቃት መለካታቸዉ ነዉ መሰል፡፡ አይ የልጅ ነገር፡፡ ይልቅ ዘመን ተቀየረ፡፡ ምኒሊክም ሞቱ፡፡ ወስደዉ በጨለማ ነዉ የቀበሯቸዉ፡፡...ሙሾ ረገዳ የለ፤ ነጋሪት ከበሮ መድፍ የለ፤ ምን የለ፡፡ ዛሬ የሚወራዉ ስለ እኩልነት ነዉ፡፡ ከባሮ ወንዝ ምላሽ የነበሩት፤ የሸህ ወጀሌ ባሮዎች ሳይቀሩ አዲሳባ መጥተዉ ከትመዋል፡፡ ሽጎሌ ሰፈር ተብሏል ሰፈሩም፡፡ ከዚያ ብረት ምጣድ ተመስለዉ ፊታቸዉ ያ ወተት የመሰለዉ ጥርሳቸዉ ሲከፈት..ስንቱን ጨዋ አስደነገጡት... (ይስቃል)፡፡ ‹ሰይጣን› መጣብን ብለዉ ስንቶች ሩሀቸዉን ስተዉ ወደቁ..(ይስቃል)...ሰይጣን አሁን ቤተሰኪያን ድረስ ምን አመጣዉ?...ብቻ ከተማዉ ቅዠት በቅዠት ሆኗል...ጠበሉስ ለዚህ ሁሉ ከየት ይምጣ?...ድርቅ ገብቷል፡፡ ይሄ የበሐር ዛፍ የሚሉት ስሩን አንዠርግጎ ምጥጥ አርጎ ምንጩን ሁላ ነዉ ያደረቀዉ፡፡ እንኳን ጋኔን የሚያወጡበት ዉሀ፤ የሚጠጣዉም እየጠፋ ነዉ፡፡ እህሉም ተወዷል፡፡ ‹ይሄን አራሽ ገበሬዉን ሁላ፤ ልጅ እያሱ ባላባት አርገዉት ማረስ አቁሟል ነዉ› የሚሉት፡፡ እቴጌም እንጠጦ የግዳቸዉን ከቤተ-መንግስት ወጥተዉ ሄደዋል፡፡ በጦርነት ነዉ የወጡት..ሐያ አምስት ነዉ ሰላሳ ሰዉ ነዉ የሞተዉ፡፡ የድሮ መኩዋንንት ብዙም አይታዩም፡፡ ቤተ-መንግስቱንም የኔ ቢጤዉ ሞልቶታል፡፡ ዳሩ ልጅ እያሱ አይቀመጡ...ከአገር አገር ሲሄዱ ነዉ የሚዉሉት፡፡..ተከተማዉ ቢጠፉም

ዝናቸዉ ገናና ነዉ። (ይስቃል)

እያሱ ደረሰ ጋለቦ በአባ ጤና፤ ግዛት እንዲሰጡህ ሹመት እንዲቀና፤የምኒሊክ ባላባት ምሽትህን ይዘህ ና!...እየተባለ ነዉ። ዘር አይለይ አቤቶ የሁሉም አባት፤ ጠረገዉ አጠበዉ ያዲሳባን ሴት። እንኳን የቦረና የነቀምት ቢሉት፤ የጅሌ ነዉ ቢባል የሸሆቹ ቤት፤አጅሬ ንስር ነዉ ዳሌ ባየበት፤ አነጣጥሮ ተኳሽ ከእግር ወደ ባት!!..(ይስቃል) ...ያገሬ ወንድ ሁላ ሱሪህን ወድር፤ ተንቧለል ቁምጣህን ተቤትህ አኑር። ፈጥኖ በሚጓዘዉ ከአገር አገር፤ በሚምዘገዘገዉ የእያሱ በትር፤ሁነህ እንዳትገኝ ድርስ ነፍሱ-ጡር!!. .(ይስቃል)...ፈደራሲዬን...ሁሉንም ማጋባት ነዉ ተብሏል።..ሙከራ ነዉ። ማን ያዉቃል? ይሰራ ይሆናል።....(መብራት የሚዘይሩት ላይ ያርፋል...አብሽር እያሱ ይንጫጫሉ...ከመሀል የነበሩት ልጅ እያሱ ራሳቸዉ ላይ የነበረዉን ጨርቅ ሲያነሱት ይታያሉ።)

እያሱ፡- አብሽር በእናንተ መጀን!../ያጨበጭባሉ/..

ሁሉም፡- አብሽር ተባሽር!!..( እጅ እየተጨባበጡ ይሳሳማሉ)

እያሱ፡- አንቺ ማን ነበር ስምሽ?

ሞሚና፡- ሞሚና...

እያሱ፡- ሞሚና!?..ሞሚና ሞሚና...እንግዲህ አርሂቡ አብሽር በይና!!..እንደገና!

ሞሚና፡- (ከሌሎቹ ጋር እየተቀባበለች)...አብሽር አብሽር..ጠላታችን እርር ይበል!..አድሩሱን አርጉት!...(ጢሱ ይሞቃል)..አብሽር!..ወሎ መጀን!...አፋር መጀን!...ጎንደር መጀን! ትግሬ መጀን! አሩሲ መጀን! ጅማ መጀን! አሰሳ መጀን! ሲዳሞ መጀን! ወለጋ መጀን! ሸዋ መጀን! አገዉ መጀን! ጎንደር መጀን! ሀረጌ መጀን! ሀድያ መጀን! ጉሙዝ መጀን! ወላይታ መጀን! ወሊሶ መጀን! (ድቤ ይመታል ይዘይራሉ)

እያሱ፡- (ተነስተዉ)..ሁሉም መጀን!..ኢትዮጵያን መጀን!...ይጣልልን ይዉደቅልን የማይበጀን!!...ጣልያን እንግሊዙን ይፍጅልን!!...ነገ ወደ አሳይታ እንሄዳለን!..(በደስታ ይንጫጫሉ)...ከዚያ ሶማሌ ገብተን በጣልያን እናሳምጣለን!...ከዚያ መለስ ጅማ ሄደን አቦል ቡና እንጠጣለን!!..በጂንካ በኩል ሱዳን ያሉ ወንድሞቻችንን እንጠይቃለን ..ከዚያ ሁላችንም ሽቅብ ባህረ ነጋሽ እንሄዳለን!!....

ሁሉም፡- አብሽር አንድ ላይ እንሆናለን!!..አብሽር!!...(እጅ ለእጅ ይሳሳማሉ...)

እያሱ፡- ማነሽ አንቺ....በሶማልኛ ‹ወንድሜ አመሰግናለሁ› ሲባል እንዴት ነበር? (ዝየራ ምርቃት ከቤተ-ክርስቲያን ደዉል ጋር አዛን ይሰማል....በቻቻታዉ መሀል መብራት በዝግታ ይጠፋል)

<u>ትዕይንት2 ቤተ-መንግስት</u>

(ሙሉ መብራት ሲበራ በርካታ መኳንንት ይታያሉ....ወዲህ ወዲያ ይላሉ.....)

ወሰን፡- ወይ ጊዜ... ወይ ጊዜ ወይ ነዶ! ያለውን አሳጥቶ አራቁቶ ትልቁን ጨዋውን አዋርዶ! ይሄን አጉራ ዘለል ባለጌ አሳድጎ...ያለ ዘሩ ያለ አቅሙ አስኮፍሶ፤ ጌቶችን አሳዳሪዎቹን አንኳሶ፤ ማሩን ለውጦ በኮሶ፤ እንካችሁ አለና ጊዜ ተመልሶ። አይ የምኒሊክ አምላክ...አሄሄሄ....ይሄ ትልክስክሱ አባቱን ብሎ አያቱን የማይደግመው፤ ዝም ትላለህ ቤተ መንግስትን ሲያረክሰው ሲያዋርድው። ችሎትህን ሲያሳንሰው ...አሁን እኒህ አላፊ ተብለው የተቀመጡትን... ምኑን ሲያውቁት?... ይማሩት?... ይልመዱት ተብሎ...ተበላሽቶ የችሎት ውሎ...ድንቁም የአገሩን ስርዶ በአገሩ በሬ...

ጥላሁን፡- (የፌታዉራሪ ማእረግ ልብስ ለብሷል)...ይሄን ያህልም አይማረሩ ደጃች ወሰን...ሁሉንም መፍቀድ እና ሰፋ አድርጎ ማየት ያሻል፡፡ እንዳለ የሚቆይ ነገር ድንጋይ ብቻ ነው፡፡ ለያውም ውሃ ካልነበኘው ጸሀይ ካላየው፡፡ እነኚህ አዲሶቹ አመጣጣቸው ከድሃው...አፍ አጥርቶ ከማያውቀው በመሆኑ አንዳንዱን ወግና ስርአት ለመልመድ ጊዜ ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከጊዜ ጋር አይጣሉ፡፡

ወሰን፡- እኔ ከጊዜ አይደለም ጠቤ...እኔ የሚከፋኝ ይሄ ባላገር ትልክስክሱ የሸዋን ባላባትና መኳንንት ደርሶ ማንኳሰሱ፡፡ እኛ ሄደን ባናቀናው... ይሄ ፊቱን በጭቃ የሚቀባው፤ አዳሪውን እንኳ ቆፍሮ የማይቀብረው፡፡ ስልጣኔን ጥዳት ባሳየነው፤ አበላል አጎራረስ፤ ብርሌ አያያዝ እንዳላሳየነዉ ሽሙጥና ዛቻ ነው ዛሬ ለኛ የሚከፍለው?

ደምሰዉ፡- አይ ሌላው እንኳን ቢቀር...ምግብ አበላል የአለባበስ ስርአት እኛ አይደልን እንጼ ያሳየናቸዉ፤በባዶ ሜዳ ተንጋለው የሚተኙትን ቤት መስራት ሳላስተማርንም?

ወሰን፡- እሱማ እኛ ነን ሄደን ልብስ ያለበስናቸው...ጋቢ ኩታ ብልኮ ያሳየናቸው፡፡ ታዲያ ታጥቦ ጭቃ እንዲሉ እዛው ከቆሻሻው ከአዳሪው፤ ደሞ ሰው ሆነዉ ሌላውን መጠየፋቸው? ጉድ ነው!...ኧረ...ኧረረረ...

ጥላሁን፡- ወገኖቼ ትልቅ መሳሳት ያለ ይመስለኛል ባነጋገራችሁ...ቡልኮ ኩታው ለአንኮበር ብርድ እንጂ አሳይታ ዱፍቲ ላለዉ ለአፋሩ አይሆነዉ፤ በውጋዴን ሙቀት ለሚኖር አይሆንም ሸማዉ...ጭቃውም የሚቀባዉ ለጠሀዩ መከላከያ ነዉ፡፡ ይሄን በሶ በቂቤ ቢበሉ ያላገሩ ያለ አየሩ ሆኖ ይታመማሉ፡፡ ውሃቸው ተኖ በላብ ወጥቶ ...በሰውን በሆዳቸው እንደ ድንጋይ አድርቆት...ትልቅ ፈተና ነው ጊላ አዳሪ መውጣት፡፡ እነሱ በልምድ አውቀው ተልምድ ተምረው የሚያደርጉትን ቢቀይሩት ይታመማሉ፡፡ ከተመቻቸው የዶሮዋን እንጀት ቢበሉ፤ ጥፍሯን ቀኑን ሙሉ እንደ መፋቂያ ቢያኙኩት ቢመጠምጡት እርስዎ ምን ተዳዎት? ማነው ለመሆኑ የዶሮ ብልት አስራ ሁለት ብቻ ነው ያለው? ሁሉም ምግብ ነው፡፡ ላባዋም ትራስ ፍራሽ ይሆናል፡፡ በኛ አገር የማንበላቸው...በሩቅ አለም ያሉ ሰዎች ይበሏቸዋል፡፡ እናም እኛ የለመደነዉን አይበሉም ተብሎ አልሰለጠኑም ማለት እንችላለን? አጉል እምነት የሚባል ሊሆን ነው ማለት ነው?

ደምሰዉ፡-እንዴት እንዴት ነው ነገሩ...አገር ማቅናት ማለት የአንዱን ልማድ...መጥፎ ባህል አጉል እምነት ማስቀረት አይደለም እንዴ? ይህማ ባይሆን በአድዋ ከጥልያን በአዙሌ...ከአሩሲ ጅሌዎች ጋር አራት አመት ደም የተፋሰስነው፤ ከሼክ ቃዋጀሌ በአሶሳ፤ በከፋ ከሺሮኮ የተዋጋነው? ጦናን ያስገበርነው? ስልጣኔን በጨለማ ተቀምጦ ያለውንና በወፍ ቋንቋ የሚናገረውን በአንድ የጋራ አፍ ተነጋግሮ ነጣ እንዲሆንም አይደል? ሌላ ምን አረግነው! ዛሬ የምኒሊክ ቅልብ ከብት ሙክት ተብለን እንሰደባለን?

መንገሻ፡- እንዲያዉ...ፊታዉራሪ ጥላሁን...ይሄ ተልምዳቸው አገኙት የምትለው ካፈሩ ካቡዋራው አርገዉ የሚበሉት...አሁን ማን ይሙት የጤፍ ቂጣ ሳይሻላቸው ቀርቶ ነው? ይሄ ስራስሩን ነቃቅለዉ የሚፈጩትን የሚቆራርጡትን ሁላ ምግብ ነዉ ልትለው ነው? እንዴት ነው የምትለን?...እናት ራስ ላይ ለራስ ምታት ቅቤ ይደረጋል እንጂ...እንዲያዉ የዶሮ ኩሱን በቅጠል ጠቅልለዉ በአናት ቢያስቀምጡት ያድናል?

ጥላሁን፡- ማን አዉቆት ቢትደድ?...ማን መርምሮት?

መንገሻ፡- እንዴት?....የዶሮዉ ኩስ ቆሻሻዉ ነዉ ወይስ ሰንሰል አጠፋሪስ ቅጠሉ?... (ይስቃሉ)...ይመረመራል?...(ይስቃሉ)...እንግዲያማ ስብራቱንም ቁስሉንም

በሽንታቸዉም ቢያጥቡት፣ ሊሆን መዳኒት?...(ይስቃሉ)....

ጥላሁን፡ መቸም አባባሌ...ይሄ አሁን አስተማርኩት አቀናሁት የሚሉት ህዝብ...በወፍ ቋንቋ ከሆነው የሚግባባው፣ ከእህሉ ላይ አፈር ቀላቅሎ ሲበላ ከሆነ በሆዱ የሚረጋው...የዶሮዋን ሳምባ በከሰል እሳት ጠብሶ ሲበላ ከሆነ ከበሽታ የሚፈወሰው፣ ጭቃውን በማር ለውሶ እንደ ድፎ ዳቦ ቢገምጠው፣ ካሳመመው፣ ሰንሰል አጠፋሪሱን አድርቆ ከቁስሉ ቢያደርገዉ ከአዳነዉ፣ ‹እንግዲያው ይተውት› ነው የተባለው፡፡ ኋላ ላይ የገመጠው ጭቃ ሲያሳምመው፣ ይሄ ምንምንቴ የሚሉት ፈውስ ካልሰጠው፣ ይመጣል ወደ እርስዎ፡፡ እድል ይጡት ተስህተቱ ለመማር፡፡ የኛ ሃላፊነት...ሁሉ እንደ ባህሉ ተከባብሮ እንዲኖር ማስቻልና አገሪቱንም ከባዕድ ወራሪ ማዳን ብቻ ነው፡፡

ወሰን፡-ፊታውራሪ ጥላሁን...አንተ እንዲህ ያለ ነገር መናገርህ መችም ግር ያሰኛል፡፡ አገር ሲፈርስ የተገነባው ወግ ስርዓት ሲናድ ከዳር ቆሞ፣ ቤት እየፈረሰ ወግ ስርአት እየጠፋ፣ እንዳሻው ተመልሶ ይደናቆር ማለቱ ለሰሚ ግራ ነው፡፡ የተሰፋዉ እየተቀደደ፣ ሁሉም እንዳሻዉ በራሱ ባህል ይኑር ማለት፣ ኋላ ይሄ ሁሉ ሰው በምን ቋንቋ ተግባብቶ ሊነጋገር ነው? ክተት አዋጅ በምን ሊነገር ነው?...መቸም የዛሬውን ብቻ ተመልክተን፣ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል.... እንዳለችው አህያዋ..(ሌሎች ይስቃሉ)...

ጥላሁን፡- ደጃች ወሰን አህያ አይበሉኝ.... ልጅ እያሱም ምንም ልጅነት ቢኖራቸው ያቃሉ ምን እንደሚበጅ ላገራቸው፡፡ የለም፣ ሀሳብ አለኝ ካሉ ሊነግራቸው ይችላሉ፡፡ ለሌላው ሰው ‹አገር ተበላሽ› እያሉ በማውራት...ንጉስ ለማማከር በተሰጣቸው ሃላፊነት ሳይጠቀሙ፣ ግና ከጥቅማ ጥቅሙ መዝገን ያላሰለሱት የሮማውያን ነገስታት አማካሪዎች፣ ሮማ ስትወቅ ቀድመው የተዋረዱት በክህደት የተደፈሩት እነሱው ነበሩ፡፡ በባህችንም እንደሚባለው...‹‹የሚወዱት ሰው ቤት መቼ ቢሆን ርቆ አያውቅም ነው›› ከነተረቱ...ይህንን በብዙ ብሄር የተሰባሰበ አገር አሁን ከታሰበዉ መንገድ ሌላ፣ አንድ የሚያደርገዉ መላና ዘዴ ካለ ቀስ ብሎ መላዉን ማስረዳት ነዉ፡፡ አገር ከሚበትን የጎንዮሽ ንግግር፡ ይሻላል ቀርቦ መንገር...

መንገሻ፡- የሚሰማ ቢገኝ ነዋ...የማይደነብር!

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ጥሩ ነው...መልካም አሳብ ምክክር ነዉ የዛሬዉ፡፡ እኛም መሪያችንን ወደ ስህተት እንዳይሄድብን ማማከር ያስፈልገናል፡

ጥላሁን፡- ልክ ነዎት ፊታውራሪ...ኢትዮጵያ አሁን ግዛቷ ሰፍቷል፡፡ ይሄን አይነቱን ወሬ ጣልያንና እንግሊዙ ከግራ ቀኝ ወሬ አሉባልታ እየነዙ...እኛን ለመከፋፈል ብዙ ይሞክራሉ፡፡ አቤቶ ልጅ እያሱ ‹ከመረብ ምላሽ ጦር ይገቱ እዘምታለሁ› ብለዉ ከተናገሩ ጀምሮ... ብዙ ሀሳብ የሚበትን ወሬ ነው በከተማው የሚነዛው፡፡ የኛን ሀሳብ ለመበተን ዋናውን ትተን በተራ አሉባልታ እርስ በርስ እንድንጠላላ እንድንበተን፣ የማይተኙልን ብዙ ጠላቶች አሉን፡፡ አቅማችንን ተመልክተው ጉልበታችንን ህብረታችንን ፈርተው፣ በሀይማኖታችን በሱማሌና በባህረ ነጋሽ አድፍጠው ነው የሚጠብቁን፡፡ መሃል ላይ ቆመን ማየት የማንችልበት ዘመን ላይ ነን፡፣ ህጻናት ልጆቻችንን ማሰብ አለብን፡፡.

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እውነት አለው አባባልህ...

ጥላሁን፡- ጦርነት መምጣቱ አይቀሬ ነው...ጣልያን የቆሰለ አውሬ ነው፡፡ የተቀረዉ ብሄር ቀደም የቆሰለዉን ዛሬ በእርቅም በዳረጎትም ደጋፊ ወገን ማድረግ አለብን፡፡ አለበለዚያ ከጣልያን ወይ ከእንግሊዝ ጋር ሆኖ ነዉ የሚወጋን፡፡

ኃ/ጊዮርጊስ፡- በጣም ትክክለኛ አባባል፡፡ ...ልጅ እያሱ ግን ምነው ዘገዩ? ይሄንን

የጣሊያን ወራሪን ሊመክሩ ነው የጠሩን ዛሬ ወይስ......

ጥላሁን፡- የታመመ ጠይቀው ቀጨኔ መዳህኒአለምን ተሳልመው ሲያበቁ እመጣለሁ ነበር ያሉኝ፡፡ አሁን መምጫቸው ነው፡፡ ካልሆነም እኔ ሄጄ አስታውሳቸዋለሁ...

ኃ/ጊዎርጊስ፡- ቢሆንማ ጥሩ...በግዜ መክረን ጨርሰን በጊዜ መሰናዳትም ካለብን እንድንዘጋጅ...ወይ መላክተኛ ድጋሚ እንስደድባቸዉ?.

ጥላሁን፡- ግዴለም እኔዉ ሄጄ ላስታዉሳቸዉና...መጣሁ ተመልሼ...ከጨረሱም እሳቸዉን ይዤ..እመለሳለሁ፡፡...(ይወጣል)...

ደምሰዉ፡- (መራቁን አስተውሎ) እበላ ባይ የድሃ ልጅ!..ቆዳ!..እሱን ብሎ ፊታውራሪ! አብሮ እየዞረ በየጓሮው በሴት ማጀቱ ስለዳከረ ስለሰከረ? ፊታውራሪ?! አይ ጊዜ...ከጥልያን ተጋድለው አጥንታቸውን ከስክሰው ደማቸውን አፍስሰው ነበር ፊታውራሪነቱ...ዛሬ ተቀይሮ ሌላ ሆኗል መስፈርቱ! ...እንዲያዉ ጌታዬ ፊታውራሪ ኃብተ ጊዮርጊስ እንዲያው በሞቴ ምን አሉ? የዚህን የጥላሁንን ሹመት ሲሰሙት.

ኃ/ጊዮርጊስ፡- አይ ምን ይባላል...ዝም ነዋ...ራስ ምታት...

ደምሰዉ፡- ኧረ እኔም መስሎኝ ነበር ቅዠት...ያ ሁሉ ባላገርና ከዚህ ስሙ ከማይጠራዉ አገር የመጣው ሁሉ ተሰብስቦ ፊታውራሪ፤ ቀኛማች ፣ግራዝማች መባባሉ መቼም ህመም ነው፡፡ አይ ጊዜ...አይ አገር...አዬ ምኒሊክ!! ዛሬ ቤተ-መንግስትህን ባየኸው ተነስተህ!! ስልሳ ሰው እኮ ነው የሞተው...ስንቱ ቆሰለበት፡፡ እስቲ አሁን እቴጌይቱን ለማስወጣት...ይሄን ያህል ደም መፋሰስ ያስፈልግ ነበር? ያ ሁሉ ተኩስና ሁካታ......

መርዕድ፡- እቴጌም አጠፉ...ቀስ አርገው በመላ እንደመያዝ...ተኩስ ማስከፈታቸው ተገቢ አልነበረም፡፡ የሞተው ብቻ ሳይሆን ሰላሳ የሚሆን ቆስለው ስንኩል ሆነዋል ነው የሚባለው...አግባብ ነገር አልተሰራም፡

ደምሰዉ፡- ደጃች መርድ...ካቀኑት አገር ከሰሩት ቤት እንዲሁ ያለ ክብር ወጥተሽ ሂጂ ይባላል? አንድ የመንግስት አገልጋይ እድሜውን ሙሉ አገልግሎ ሲያበቃ...እንዲሁ በቃ ሄድልን ይባላል?

መርዕድ፡- ጥፋቱ የዘበኞቹ አለቃ...የንጉስ ወታደር ላይ መተኮስ ማስተኮስ አይገባውም አልኩ እንጂ...ነገሩን በብልሃት መያዝ ይገባ ነበር፡፡

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እኔማ የዘበኞቹ አለቃ...ማነው...ገብረ ማርያም...‹ልጅ እያሱን ተኩሶ ጣላቸው› ሲባል እውነት መስሎኝ...

ደምሰዉ፡- እኔሳ...ምን ያረጋል ታዲያ.....

መርዕድ፡- በስማም....እኔም ስሰማ ውነት መስሎኝ ደንግጬ ነበር...ግና የዚች አገር ትንሳኤዋን ጌታ ስለፈቀደው፡፡ ‹ምን ቢያረጉት ቢለኩሱት ኢትዮጵያ እንደሁ አትሞት› አልኩኝ፡፡ ይሄን ልጅ መሪዋን ደሞ ቢባርክላት፤ ልብ ቢሰጠዉ ቢያሳድግላት ትልቅ ቦታ ትደርሳለች ማን ያውቃል?

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ጎሽ እሰየው...እንግዲያውስ ላልሰማችሁ መርዶ ልንገራችሁ፡፡ ኢትዮጵያ መሪዋ ሞቶ ተቀብሯል፡፡ እሷም መቃብር አፋፍ ላይ ናት፡፡

መርዕድ፡- ፊታውራሪ ሁሌም ወደኂላ እያሰቡ መኖር አይቻልም፡፡ መቸም...

ኃ/ጊዮርጊስ፡- የወደፊቱኮ ነው ያስፈራኝ ...በቀደም ማታ በቱርክ ቆንስላ ትልቅ ፈንጠዝያ ትልቅ ድግስ ሆኖ...የከበረዉ የኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ፤ ‹አላህ ይክበር› የሚል በእስላሙ ቋንቋ ተለጥፎበት፤ ‹የአቤቶ እያሱ ስጦታ› ተብሎ....ያ ባንዲራችን

አርማዉ ጌጡ ተንቆ አላህ ይክበር! ሆኗል ነገሩ ሁሉ። (አንዳንዱ ባለሟሎች እያማተቡ ይወድቃሉ)... አላህ ይክበር! (ሌላ ይወድቃል)....ዙሪያዉን ቢሽሚላ የሚለዉ ተጠልፎበት...ስንቱን ጠላት ያርበደበደው ባንዲራ፤ ስንቱ የወደቀለት እያረገን ባለ አደራ። በቱርክ ቆንስላ ጠረጴዛ ላይ ተነጥፎ...የእስላም ስጋ መጠቅሊያ ጨርቅ ሆኖ አይቻለሁ› ባይኔ በብረቱ ብሎ ነው አንድ ባለሟል የነገረኝ (የወደቁትን ውሃ ከኮዳ እያቀመሱ እያራገቡ የነበሩ አንዳንዶቹም ይወድቃሉ...ያነሷቸዋል...ትንሽ ትርምስ ይሆናል)

ደምሰዉ፡- ጉድ ጉድ...ማረን ጌታዬ..

ወሰን፡- ‹‹ምን ቢያጠምቁ ቢቀድሷቸው ሁሉም ያዉ›› ናቸዉ› ነው ያሉት እተጌ። ሁሌም ትክክል ናቸው። ልጅ እያሱ አሁንም እስላም ናቸው።

መርዕድ፡- የለም የተረጋገጠ ነገር ሳንይዝ ብዙ ማለት የለብንም። እተጌ ስልጣኑ ከሸዋ ወደ የጁ እና ሰሜን እንዲሄድ ነበር የፈለጉት...አሁን ያሉት ወሉን ማመን ከንቱ ነው የሚባለውም ተራ ወሬ ነው። አሉባልታ። ይሄ ጠላት እኛን ለመከፋፈል ንጉስ ሚካኤልን ከዬሃንስ ዘመዶች፤ ከላይ ከትግሬዎች ጋር ለማዋጋት ታስቦ የሚያወራው አሉባልታ ነው። ሊያምኑትም አይገባም ፊታዉራሪ።

ደምሰዉ፡- አሉባልታ? ስንቱን ጨዋ በሽተኛ ያረገው ውስጡን የሚያቃጥለው እውነት ነው። ጌታዬ ደጃማች ያገር ፍቅር ህመም ጠባሳ ነው። ማንም ቢሆን የማይረሳው...የወሎ ምንድንና ምንድነው ይባላል...

መርዕድ፡- ደጃች ነሲቡ...መቼም ጥላቻ ደግ አይደለም። ጥላቻን ይዞ መኖርም...የሚፋጅ እሳት በጅዎ ይዘው እንደመቀመጥ ነው። ያለፈውን ትተው፤ መልካሙን ቀናውን ማሰቡ፤ ለጤናዎም ቢሆን መልካም ነው። ክፉ ጥላቻ የልብ ህመም ነው የሚያመጣብዎት። መካሪ አባት እንደመሆንዎ...

ደምሰዉ፡- ደጃች መርድ ተሳስተዋል...እኔን የሚያመኝ ውስጤ በጥላቻ ተሞልቶ አይደለም...እተጌም መንገዱን ነዉ ያሳዩን። የማያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ ያስታዉቃል። እኔን የሚያመኝ የሚያንገበግበኝ...(ትልቅ የጥይት ሩምታ ተኩስ ከቅርብ ርቀት ይሰማል። ባለ ስልጣናቱ ይደናገጣሉ መደበቂያ ይፈልጋሉ። ጣሴ እየሮጠ ገብቶ ተመልሶ ይወጣል...ተኩሱ ትንሽ ጋብ ይላል...ጣሴ ተመልሶ ይገባል።

ጣሴ፡- ልጅ እያሱ ናቸው! (ይርበተበታል)..ዉይ...

ሁሉም፡- ሞቱ?! ሞቱ!? ሞቱ!?

ጣሴ፡- ከቡሊሶቹ ጋር ሲታኩሱና ሲባረሩ...ከላይ ከታች ሲተኮስ... ምንድነው?? ....ሲታኮሱ እና ሲሯሯጡ..ዉይ ዉይ...

ጋ/ጊዬርጊስ፡- ምንድነዉ?....ወይ ሞቱ በል!

ጣሴ፡- ማለቴ...የባሩዱ ሽታ....(በርካታ ባለሟሎች ታጅበዉ ከጥላሁን ጋር ልጅ እያሱ ይገባሉ ሌሎች እጅ ይነሳሉ፡)

እያሱ፡- (ከት ብለው ይስቃሉ)...የፊታዉራሪ ጥላሁን ወጥቶ አደሮች ቤተ-መንግስቱን ጥለዉት ስላሴ ግቢ ነዉ የተደበቁት...(ሳቅ)....ምን ነካቸው?? (ይስቃል)

ጥላሁን፡- አንዳንዶቹ ግን ለመከላከል ሞክረዋል ጌታዬ.....(ቅር ብሎታል)...

እያሱ፡- ምኑን ነው የሞከሩት? የመሳሪያ ግምጃ ቤታቸውን ጥለውት ነውኮ የሄዱት...(ይስቃል..ሌሎቹም ይስቃሉ)...አንዳንዶቹማ፡ አንገታቸውን ከትቢያ ሸጉጠው እኮ ነው ሽቅብ የሚተኩሱት...እኔና ጣሴ ብቻ ሃያ እሚሆኑትን ነው ወንዝ ያሻገርናቸው። ፊታውራሪ ጥላሁን...መርቀን ሽልመን አዲስ አበባን አደራ

ብለን የሰጠነው ፓሊስ እንዲህ በሁለት ሶስት ጀሌ የሩምታ ጥይት የሚፈታ ከሆነ፤ ይፍረስ አሊያም እንደገና ይከለስ። ካልሆነም ከተማችንን ለቀን ሐረር ወይ ተመልሰን አንኮበር ልንሄድ ነው ማለት ነው። ደሴም ውብ ነው...ለዋና መንግስት መቀመጫነት አያንስም...ቢቻልማ ጠላት ባያጠቃው ወደ አፋሩ አገር ነበር...ወዲያም ወደ ባህር ውሃው ተጠግቶ መቀመጥ ለንግድም ለሌላዉም ጥሩ ይሆን ነበር....(ግራ ይጋባሉ ሌሎቹ)...ለሁሉም ነገር ቅርብ እንሆን ነበር...

መርዕድ፡- ጃንሆይ...ለአየሩም ለውሃውም አዲሳባ ነው ጥሩ አገር። ዙሪያ ተራራ ሰንሰለቱ ለጠላት እሺ ብሎ የማይሰበር ነዉ።

እያሱ፡- ምን ፓሊስ፤ ወጥቶ አደር አለዉ የሚጠብቀው?...አሁንማ ጦር ሜዳ ነዉ የሚመስለዉ።

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እኔምለው አቤቶ...ይሄ ቡሊስ የሚባለው ባላባት ጢሰኛ የሌለው፤ አንዱ ከአንዱ ቀኛማች ግራዝማች የሚባል የሌለውን...ይሄ ባተሌው....የሚገዛትበት ነፍስ አባት ቄስ የሌለዉ እዉን ታማኝ ታዛዥ ሆናል ብለው ነው?

እያሱ፡- በሚገባ...ዘመን እየተለወጠ ነው ፊታውራሪ...ከተማ ደግሞ የፖሊስ ግዛት ነው፡፤ ሌላ የአገር ድንበር የሚጠብቅ ወጥቶ አዳሪ የመንግስት ተሁሉም ዘር እና ጎሳ የተዉጣጣ አገር ጠባቂ ሀይልም ያስፈልገናል። ይሄ ዛሬ ያለው የየባላባት ጦር፡ እርስ በእርስ እየተዋጋ ይከፋፈላል አገር። ወደፊት ያመጣል ብርቱ ችግር...

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ታዲያ ይሄ ወጥቶ አደር የሚሉት...እንዲሁ ጠመንጃውን እንካ ካሉት፤ በማንም የማይገዛት፤ ነገ ጎልብቶ ቢያፈርስስ መንግስት? ያቆመውን ስርአት መልሶ ቢጥለው፤ በማን ቄስ ሊያዝ ሊገዛት ነው? ... መቼም እምለው፤ ለእስዎ ያደረዉ ባላባቱ መሳፍንቱ ያለዉ ተዋጊ ጦር ይበቃል ስርአት ለማስከበር። ይሄ ወጥቶ አደር የሚባል፤ የጀሌ ስብስብም አያስፈልገን። ኋላ ተደራጅቶ ሽፍታ ሆኖ ስርአት መንግስት ቢያፈርስ ምን ልንሆን ነዉ?

እያሱ፡- ልክ ነዎት ፊታውራሪ፤ ነገሩ ያሳስባል። ግና ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም። ይህንን ብሄረ ብዙ አገር በስርአት ለማስተዳደር ሰፋ ያለ ውክልና ያለው ለስርዓቱ የሚቆም ሰራዊት ደንቡን አጥንተን ከናንተና ከሌላውም ጋር መክረን ፈጥነን ማቋቋም ይኖርብናል። የእገሌ ባርያ የእገሌ አሽከር የሚባለዉ ጦር መሳፍንቱ በተከራረፉ ቁጥር ጦርነት ነዉ የሚተርፈን። ይልቅስ ዛሬ ያስጠራኋችሁ ድንገት በራስ ተሰማ ናደው ሞት ደንግጣችሁ...

ሁሉም፡- አረፉ እንዴ? መቼ?...(ይተያያሉ)

እያሱ፡- የመንግስት ስራ እንዳይጓደል ፊት በቀላጤ የምትሰሙትን እኔ ዘንድ መጥታችሁ እንድትሰሙት ይሄንኑ እንድታውቁት ብዬ ነው። ከእንግዲህ የምትፈልጉትን ሁሉ ለእኔ ልትነግሩኝ ትችላላችሁ።

ሁሉም፡- ዉይ ዉይ...ሞቱ ምን ሆኑ?

ጥላሁን፡- ታመዉ እንደነበር ሁላችንም የምናዉቀዉ ነገር ነዉ።

ወሰን፡- አይይይ...መቼ ነው ቀብራቸው?

ጥላሁን፡-ደብረ ሊባኖስ ትናንት ተቀብረዋል።

ወሰን፡- አልፈጠነም ቀብሩ?

ጥላሁን፡- በጣም።

ወሰን፡- ይገርማል።

ጥላሁን፦ በኑዛዜአቸው መሰረት ነው የተፈጸመው።

መርእድ፦ ባለቤታቸውስ...ወይዘሮ ማናት...በለጥሻቸው እንዴት ትሆን?

ጥላሁን፦ አዝናለች በጣም...መቼም በእድሜ ልጅ ስለሆነች...

እያሱ፦ ለዕዝን የሚደረገውን አድርጋችሁ...ከፈለገችም ብቻዋን ከምትሆን እዚህ ከእልፍኝ መጥታ...ሰብለ ወንጌልም እንድታስተዛዝናት ይሁን። (ጣሴ እጅ ይነሳል)

ፊታውራሪ፦ መቼም የንጉስ ባለሟል የዘውድ ጠባቂ የምኒሊክ ባላደራና የርስዎም ሞግዚት የሆነ ሰው ህይወቱ ስታልፍ...ነፍሱን ወደ ፈጣሪ ለመሸኘት፤ አገር አውቆት አስከሬናቸው በሰረገላ ፈረስ ባደባባይ ታጅቦ ቢሄድ ደስ ይል ነበር። ለነፍሳቸውም ማዕረግ።.

እያሱ፦ ደብረ ሊባኖስ ማረፋቸውም ለዚሁ ነው። ቅዱስ አፈር እንዲቀምሱና ለነፍሳቸው ከዚያ የተሻለ ቦታ የለም በማለት...ከዚያ በላይ ደግሞ በኑዛዜአቸው የጠየቁት ነው የሚፈጸመው። ከቶ እኛ የአንድን ሰው ኑዛዜ መቀየር ይገባናልን?.

መርእድ፦ የለም...ኑዛዜአቸዉ እንደሱ ከሆነ መቀየር አይቻልም። የሚችን ኑዛዜ ማንም የማይሽረው የእምነት አደራ ነው!

ሁሉም፦ ትክክለኛ አባባል!

እያሱ፦ እግዚያብሄር ይባርካችሁ።

መርእድ፦ እንግዲህ አቤቱ እያሱ ከእንግዲህ ከርስዎ አፍ የምንሰማው ከሆነ፤ ለኛም ‹ይሄ ተባለ አልተባለ› ብለን እንዳንደናገር....ከእንግዲህም ሌላ ሞግዚት ባለአደራ ከመፈለግ... እሺ ይበሉና ለምን ስርዓተ-ንግሱን፤ አቡኑ አባታችን ጋር ተማክረን፤ በአለ ሲመቱን ለምን በቶሎ አናደርገውም? ህዝብም ይጓጓል ንግስናዎን ለማየት።

እያሱ፦የለም...ለንግስናው የሚያስቸኩል ነገር የለም። ከዚያ በፊት ይሄን ሁሉ የኢትዮጵያ ግዛት አንድ የሚያደርግ ዘዴና ብልሃት መፍጠር ያስፈልገናል። እንዲሁ ንጉስ ነገስት መባሉ ዘዉድ በራስ ጭኖ፤ በትረ ሙሴዉን ይዘዉ ቢቀመጡ ምን ይረባል?...ከመረብ መልስ ያልጨረስነዉ ጣልያን የያዘብን አገርና ይቺን አገር አገሬ የሚላት ህዝብም ይጠብቀናል። በሱማሌም ኦጋዴን ያሉ ወንድሞቻቸዉ ጋር በአንድ አገር የማድረጉ ስራና በደቡብ በሱዳን ያሉትም ወንድሞቻቸዉ በእንግሊዝ ስር ናቸዉ።...ያንን ጨርሰን ስናበቃ በጋራ አገራችን ሁሉም የመከረበት ንጉስ ይኖረናል።

መርዕድ፦ ንጉስ ነገስቱማ ያባትም፡ ያያትም፤ ማን ነዉ መክሮ የሚሰጥዎ? ያንንማ የሚሽር፤ ውጉዝ ነው በሰማይ በምድር...ይቀጣል በክፉ በትር!!.

ሁሉም፦ እውነት ነው።

እያሱ፦ አይ ደጃች መርድ...ቅጣት አስተሳሰብን ቢቀይር ዛሬ ሁላችንም አንድ በነበርን። ቅጣት ሰውን የከጀለውን ከማድረግ፤ ጊዜ እንዲጠብቅ እንዲያደፍጥ ያደርገዋል እንጂ፤ ሀሳብን በቅጣት መግታት ከቶውኑ አይቻልም። ይሄ ዛሬ፡ የምኒሊክን ጦር፤ የኛን በትር ፈርቶ ያለውን ሁሉ፤ እምነትና አስተሳሰቡን በቶሎ ካልቀየርነው፡ ይቺ አገር የጋራ ቤቱ መሆኗን ካላሳየነው፤ ዝምታው ፍርሃቱ የወደፊት አደጋ ነው።

ወሰን፦ ዛሬም ክንዳችን ሃያል ነው።ለአገራችን ለባንዲራችን ለመሞት ሁሌም ዝግጁ ነን፡

ኃ/ጊዮርጊስ፦ እንዴታ ማንም የማይደፍረው የማይሞክረው! የሚያደባይ ጉልበት በጦርነት የማይረታ ብርቱ ታማኝ ሰራዊት ዛሬም አለን! ሄደን እናሳየዋለን።

መርእድ፦ ዘራፍ የምኒሊክ አሽከር! ዘራፍ የእያሱ ባሪያ! አጋድሞ የሚጥል በዱር በገበያ!

አሳየው ክንድህን ይቅመሰው ወኔህን! ከትቢያ ደባልቀው ይወቀው ሃይልህን!
ዘራፍ የእያሱ ባሪያ! ይሄን መደዴ ያልታረመ ሁላ፤ አሳየው ደቁሰው ድፋው
እንዳተላ...እምቢኝ!...( ከኃብተ ጊዮርጊስ በቀር ሁሉም መርእድን ያበረታታሉ)
ሁሉም፡- ዘራፍ...የእያሱ ሎሌ...የእያሱ አሽከር!!...(ፊታዉራሪ እንደተከፉ ያስታዉቃል)

እያሱ፡- ይበቃል...(ፋታ) በጣም የሚያኮራ ነው ወገናዊነታችሁ። ጦርነትን ማሸነፍም የጎበዝ ስራ ነው። እናንተም ጀግኖች ናችሁ። አሁን ግና ማሸነፍ ሰላሙን ነው። የዚች አገር ፈተና.. የእኛም ጥሪት፤ ከእንግዲህ ሰላሙን ድል መንሳት!

ወሰን፡‹ ጃንሆይ...በጦርነት የተሸነፈ ከሰላም ውጪ ምን ሌላ ይቀረዋል። ሰላሙን ይቀበሉታል እንጂ ምኑን ያሸንፉታል??

እያሱ፡- ሰላምም ጦርነት ነው ደጃች ወሰን። እንዲያውም የአንድ መሪ ብቃት የሚፈተነው ከጦርነት ድል በኋላ የሚመጣውን ፈተና አልሞ መጣሉ ነው። እንዲሁ ‹ጣትህን እቆርጣለሁ አይንህን አጠፋዋለሁ› ብሎ ስላለ ሰላምን አያመጣም። ይልቅ ሳልረሳው...አሁን በዚህ በሻንጉላው አገር ከዚህ ከጊሚራው አገር ጀምሬ ስለምንሄድ ስመለስ የማመጣቸው የአገሩን ሰዎች ለማሳረፍ ይሄ ቤተ-መንግስቱ ዙሪያ የሰፈረዉ የመንግስት ስራ የማያሰራው በዘኔ ቦታውን እንዲለቅ ይሁን።

ወሰን፡- ግንኮ አቤቶ...ባለፈውም ከሻንጉል ነዉ? ከደቡብ አገር ያመጡዋቸው...እዚህ ምንም አልተመቻቸው። አፍ አጣርተው አይናገሩም ከዚህ ከባላገሩ የባሱ...

እያሱ፡- አፍስ አጣርተውማ ይናገራሉ። እኛም የነሱን አፍ አጥርተን ለማወቅ እንጂ!.. እነሱም ባፋቸው...አፍ አጥርታችሁ አትናገሩም ነው የሚሉንኮ...( ይስቃል)

ደምሰዉ፡- በዚህ ላይ...ሃይማኖትም ስለሌላቸው እዛው ይሻላቸው ነበር ባገራቸው!

ፊታውራሪ፡- እንግዲህ ዞረን እንዳየናቸው...ገሚሱ በድንጋይ ገሚሱ በዛፍ በፀሀይ በጨረቃ እሚያምኑ እዚህ ያለቁርባን ያለክርስትና በደጀ ሰላሙ እየገቡ የሐይማኖት አባቶችን እያሳዘኑ ነው።...መቼም አቤቶ እያሱ ቢያስተውሉት...

እያሱ፡- ምን አሳዘናቸው? ክርስቶስ እንደሆነ ‹ወደ ቤቴ የሚመጡትን አስገቧቸው ነው› ያለው። ለምን አያስገቡዋቸውም ሻንጉሎቹን??...ረብሻ እና ሰላም የሚያደፈርስ ነገር እስካላደረጉ፤ የትምህርት ዘዴዉን ቄሶቹ መላውን ይምከሩት። ማደሪያቸውን ግን እዚሁ መጥተው በቤቱ ገብተው ይውደቁበት... እነሱም የዚህ አገር ሰዎች ናቸው። ግብሩን ቅቤና እህሉን ከብቱን ቡናዉን ተቀብለን ስናበቃ፤ ልጆቻችሁን ትምህርት እንዳይማሩ፤ ‹ባላችሁበት እዛው ቅሩ› አንላቸውም። ቦታ ማደሪያና ሌላም መስተንግዶ ያሻቸዋል።

ወሰን፡- (እጅ ይነሳሉ)...አሁን ቤተ-መንግስት ያሉት ሁሉም ይውጡ ነው የሚሉት?

እያሱ፡- አዎ። ቢያሻቸው ይሂዱ ወደ የርስታቸው። ቤቱ የመንግሰት ስርዓት የሚሰራበት ነው። ችሎት የማያስችለው፤ ወደየርስት አገራቸው ይመለሱ። ከባላገሩ የሚመጡት ይረፉበት በቤቱ፡

ወሰን፡- አቤቶ ሆይ...ከአንዳንዶቹ የሚሰማ ቅሬታ ኖሮ ሳለ እንደገና የተቀሩትንም ውጡ ብሎ ማሰናበቱ...

እያሱ፡- የሚሉሽን ከፈራሽ ገበያ ባልወጣሽ ነው የሚባለው...ምን ይሉኝን ከፈራን ስራም አይሰራ። ለማናቸውም ቦታውን ይልቀቁ.... ይልቅ መሸ በጣም...ሂዱ በየቤታችሁ ...ነገ ማለዳ ደሞ ሁላችንም የቀጨኔ መዳህኒአለምን ታቦት እናስገባለን..

ሁሉም፡- አዎ...እናነግሳለን...(እጅ ነስተው ይወጣሉ...)

እያሱ፡- እግዚያብሄር ይስጣችሁ! ማለዳ ያገናኘን....(ጥላሁን ብቻ ይቀራል የተቀሩት እጅ

ነስተው ይወጣሉ።…ፋታ…)…ፊታውራሪ ጥላሁን…የማይረባ ፖሊስ አለቃ…

ጥላሁን፦ መቼም ባትለኝም በዛሬው ሁኔታ አፍሬአለሁ…. ጠንካራ የፖሊስ ሃይል ያለን መስሎኝ ነበር…አንዳንዶቹ…በጣም…ብዙ ጉድለት አላቸው….

እያሱ፦ የለም በማንም አታመሃኝ። ውድቀት በራሱ መጥፎ አይደለም። ትምህርት ይገኝበታል። ከራስህ ውጪ… ውድቀትን በሌላው ስታመሃኝ ብቻ ነው ውድቀት አሸንፎህ፤ ውዳቂ የምትሆነው። ጥፋቱን ተቀበለዉና ስልጠናውን እንደገና ጀምሩ። ሰው ጨምሩ….ቀንሱ። ትምህርቱን ከልሱ። ውድቀቱን መማርያ አደርገው። ስልቱን መርምሩ። እመነኝ የሚቀጥለው የተሻለ ነው የሚሆነው።

ጥላሁን፦ እሺ…በነገራችን ላይ…ስለ ባንዲራ ስጦታው….ወሬው ከእነ ፊታውራሪ ዘንድ ደርሷል…ዘዴና ብልሃት ያስፈልጋል…ትንሽ እርጋታ ክፉ አይደለም።

እያሱ፦ እርጋታ? እነሱ ጃጅተው እስኪሞቱ ከጠበቅን አንድ ነገር ሳይሰራ ይነጋብናል። ከመቶ አመትም በሁዋላ የሚፈጠሩትም ስለ ብሄራዊ እኩልነት በማዉራት ጊዜ ማጥፋት የለባቸዉም።…ይቺ ድሃ አገር ናት! ሊጠቅማት ከሚችለው ጋር ሁሉ መዋደድ አለባት። አየህ ዛሬ ቱርክ የት እንደ ደረሰች? ባንዲራው ላይ ባስልበት ጨረቃ የሚያመጣልኝ ከሆነ መልካም የእርሻ ዕቃ፤ የጤና ባለሙያ፡ የጦር ምሁር አለቃ፡ የሚያመጣልን ከሆነ መንገድ ቤት መስራት የሚያስተምረን ምንድነው ችግሩ? ባላገሩን በየአመቱ የተስቦ በሽታ እየጠረገው፡ ባንድ ዶማ ወገቡን በመጫኛ አስሮ ገደሉን የሚያርሰዉ፤ ልጆቹን ወደ ትምህርት መስደድ ያልቻለው። በሚድን በሽታ የሚማቅቀው። በጠኔ የተከበበው፤ ከኩራቱና ከእራቱ እስቲ አስመርጠው? …ስንቱ ነው በረሃብ ለመሞት የሚፈቅደው? ከቁጣው ይልቅ ባንዲራዬን ስጠኝ የሚለው?…የቱነው?…

ጥላሁን፦ እሱስ ባይበዛም፤ አይጠፋም የባንዲራው ፍቅር ያለው። በምስሉ መቀየር የሚከፋዉ፤ አሁን አንተ ያልከዉ የማይገባዉ።…(እያሱ ራሳቸውን በአሉታ ይነቀንቃሉ)…በተለይ ከአድዋ ድል በኋላ ባንዲራችን ምስሉ ሆኖአል የአፍሪቃ የትግል አርማ። አንተም ስትነግረኝ ባንዲራችን ለመላው የጥቁር ህዝብ የነጻነት ተምሳሌት ምኞቱ ናት ነው የምትለኝ። እንዲህ መፍጠን መቸኮሉ …ሳያስተውሉ …በርጋታ በብልሃት አለመጓዙ በስሎ ሊበላ ያለ ዳቦን ያበላሻል። የእነኚህን ሰዎች እድሜና ያካበቱትን ልምድ መናቅ አይገባም…እድሜአቸውን በሙሉ የሰሩበት…

እያሱ፦ ምንም ቢቆዩበት ቢተኙበት…ልቦና ከሌለበት ዋጋ የለውም እድሜ ብቻውን። አንድ የዛፍ ግንድ መቶ አመት ውሃ ዉስጥ ቢቀመጥ አሣ ይሆናል?…መብሰል ከእድሜ ብቻ የሚመጣ ቢሆን፤ከዚህ ከተገተረው ትልልቅ ዋርካ ቅርንጫፉን እየዘነጠፍን ጠላ ባስጠመቅንበት ነበር። ምን ቢከርም ቢዘረጋ ዋርካ፤ ጌሾን እንዲሁ አይተካ!…(ጣሴ በዋንጫ የሚጠጣ ይዞ ይገባና ለሁለቱም እጅ ነስቶ ይሰጣል)… ጣሴ…ከጌሾ እና ከዋርካ ማነዉ ጎበዙ?…ትልቁ ዋርካ ወይስ አጭሩ ጌሾ?

ጣሴ፦ አጭሬ ጌሾ ነዉ እንጂ!

እያሱ፦ (ለጥላሁን)..ይሄዉልሃ!…(ይጠጣሉ)

ጣሴ፦ (ለተመልካች)…ዋርካም ከወደቀ ቤት ያፈርሳል!..ግን ንግግር ማብዛት ነዉ!…ለዛሬዉ ጌሾ ያሸንፋል..(ለራሱም ይጠጣል)…

ጥላሁን፦ (ይጠጣል)..መቸም በርጋታ ይሁን ነው አባባሌ..አለበለዚያ

እያሱ፦ ወጣቱ ትውልድ ለውጥ እየፈለገ እንዴት ነው በርጋታ በዘዴ የምትለኝ? ዛሬስ አነጋገርህ ደጃች ተፈሪን መሰልከኝ…እንዲህ አድርጎ መለማመጥ አይገባኝም።

እሱም ከየት እንዳመጣዉ ከትናንት በስትያ ‹ቀስ ብለህ ተጓዝ› ሲለኝ ነበር፡፡ ይሄ ዘገምተኛ ሁላ...ይቺ አገር ቀስ ብሎ ለመሄድ ጊዜ የላትም፡፡ ዛሬ የምናየውን ችግር አለባበስን ለሚቀጥለው ትውልድ ለማሳለፍ...በዱቤ እየበላን እዳን ለልጆቻችን ለማውረስ ካልሆነ በቀር ሌላ መላ የለውም...

ጥላሁን፡- ተፈሪ ብልህ ነው፡፡ ‹ቀስ እያልን› እንሂድ ማለቱ የአያያዝ ብልሀት ነው፡፡ በዚህ ላይ እቴጌን ጭምር እንጦጦ ድረስ እየሄደ ነዉ የሚጠይቃቸዉ ይባላል፡፡

እያሱ፡- እንጦጦ የሄደ እንደሁ ምን ታደርግለታለች?..ለራሷም አሮባታል እንኳን ለእሱ ልትሆነዉ፡፡

ጥላሁን፡- ከአሮጌዉ ሳይጣላ አዲሱን ትዉልድ ለመያዝ የሱ መላ ጥሩ ነዉ፡፡ ተፈሪ...

እያሱ፡- ተፈሪ ምንም ቢል ምን የሚያመጣዉ ነገር የለም፡፡ አሁን ከሐረር አንስቼ ወደ ከፋ እሰደዋለሁ፡፡ ቀስ ብሎ መጓዝን ከመረጠ ከአባ ጅፋር ጋር አስሞክረዋለሁ፡፡

ጥላሁን፡- ሐረርን ለማን?

እያሱ፡- ለማንስ ቢሆን? ጅማ ገብቶ ቀስ ብሎ መጓዝ ከቻለ ‹ተራማጅ ተስፈንጣሪ መሀል ሰፋሪ› እያለ የሚደሰኩረውን ከዓመት በኃላ ደግመን እንጠይቀዋለን፡፡

ጥላሁን፡- ሐረርጌ የአባቱ እርስት ነው፡፡

እያሱ፡- አሚር አብዱላሂም ‹ሐረርጌ የአባቴ ነው› ይላል፡፡ ከሐረር ህዝብ የተሰበሰበውን ግብር ‹በቁሶች አስነጠቀን› ብለው ተማርረው መልዕክተኛ ሰደውብኛል፡፡ ሐረርጌ አምጦ ወደ ግብጥ ከሚመለስና፣ የዚች አገር ድንበር ከሚገመስ፣ እሱ የአባቴ ነዉ የሚለዉን እርስት ቢያጣ ይሻለኛል፡፡

ጥላሁን፡-ተፈሪ...ልጁ ስራው ልዩ ነዉ፡፡ ምን እንደሚፈልግ አይታወቅም፡፡ ጠላት ማበራከት እንዳይሆን ብልሃት ይፈልጋል፡፡ እቴጌንም በቀላል ማየቱ...

እያሱ፡- ተፈሪ ምንም አያመጣም፡፡...የምኒሊክ ባላባቶች ፊታዉራሪ ሀብተ ጊዮርጊስ ጨምረሀ...ከእቴጌ ጋር መተያየትም መነጋገርም አይፈልጉም፡፡ ብቻቸዉን አንድ የወንድ ሰራተኛ እንኳ እንዳይኖራቸዉ አድርገዉ፣ ወደ የትም እንዳይሄዱ እንጦጦ በግዞት መልክ ነዉ ያስቀመጧቸዉ፡፡ በጌምድር ወይ ቡልጋ እንኳ እንዳይሄዱ ነዉ የከለከሏቸዉ፡፡ ...ተፈሪ ሄዶ እጅ ቢነሳ ምን ያገኛል ከመቀላወጥ በቀር?...ይልቅ ሳካሜ እንዴት ሰነበተች?

ጥላሁን፡- ደህና ነች..አሁንም ከወጭ ደጅ ጥናት ላይ ነች...ባለፈዉም እንግዳ በዝቶ ሳታይህ ተመለሰች...

እያሱ፡- ጣሴ ንሳማ አስገባት....(ጣሴ ይወጣል)...በጣም ነዉ ያፈርኩት፡፡ ራሴ ሰድጄባት ስንት ቀን ሳላናግራት...(ሳካም የለሽ የተለያየ ቀለም ያለዉ የባህል ልብስ ለብሳ ትገባለች፡፡ እጅ ስትነሳ..እያሱ ከወንበር ወርደዉ ቀና ያደርጓታል)...እንዴት ከረምሽ ሳካሜ?

ሳካሜ፡- ክብሩ ይስፋ በጣም ደህና ነኝ፡፡

እያሱ፡- እባክሽ ይቅርታ አድርጊልኝ፡፡

ጥላሁን፡- እንዴት...ለምኑ ጌታዬ?

እያሱ፡- አንቺ ንፁህ ሰዉ ነሽ፡፡ ዘረ ሐረግሽ ከንጉስ ሳህለ-ስላሴ፣፣..የእስራኤል ነገድ ዝርያ ያለሽን እመቤት፣ ደፍሬ ያለ ቦታሽ ለወንድሜ ለጥላሁን ሳጭሽ...ምንም ኩርፊያ አልሰማሁብሽ...እጅግ ትልቅ ሰዉ ነሽ፡፡ ጥላሁን ለአንቺ ያለዉን ፍቅሩን ሲነግረኝ፡፡ ማነቆዉ ችግሩ የዘር ሀረጉ መሰረቱ ድሀ መሆኑ እንጂ ሌላ እንደሌለ

ሲያስረዳኝ...በጣም ነበር ያሳዘነኝ...ይሄን አንዱን የተባረከ ሌላዉን የረከሰ ዘር የሚያደርገዉን ስርዓት እንዲህ በተምሳሌት በመስዋእትነት ነዉ የምንቀይረዉ፡፡ ግን አንቺም ተስማማሽ? ወይስ ትእዛዝ ነዉ ብለሽ ነዉ የገባሽ?....አጠፋህ ካልሺኝም እለምናሁ ከይቅርታሽ...

ሳካሜ፡- ኧረ እኔ ነኝ ጌታዬ አመስጋኟ፡፡ ሰንሰለቱን ከእግሬ ነዉ የተነሳልኝ፡፡ መኪንንት ባባባቱ በተከራረፉ፤ አንዱ ዘር ከአንዱ ሲጣላ፡፡ ሁሌም ይዘን መሄድ ነው ወደ አንዱ፤ ተሸክመን ያንዱን ዲቃላ፡፡ ሴት እንደ ሌላዉ ንብረት እቃ የሚቀባበሏት እንጂ ሰዉ ማን አድርጓት? አንዱ ሲጥል ሌላው ሲያነሳን፡፡ ‹ሴትና አህያ ማደሪያዋ አይታወቅም› እየተባለ...ከቶ እንደ ሰው ልጅ ፍጡር መቼ ተቆጠርን? የዘር ግንድ ማቀጣጠያ፡ የፍላጎት ማርኪያ የወንድነት መፈተሻ፤ የዘር መተኪያ ማባዣ ማራቢያ እንጂ እንደ ሰውም አልተቆጠርንም ነበር፡፡ ዛሬ ከዘር ማቀጣጠያ መዉጣቴ ለእኔ ነዉ ልደቴ፡፡ ይሄ ብርሃን በሁሉም ተዳርሶ...ሴት ልጅ እንደ ሰዉ የምትቆጠርበት ...ከዘር ይልቅ ሀሳብ እና ፍላጎት የሚጠየቅበት ዘመን እንዲመጣ ምኞቴ ነዉ፡፡ ሁሌም የአንተ አገልጋይ ባርያ ያድርገኝ (እጅ ትነሳለች)

እያሱ፡- በይ ይበቃሻል...(ይደግፏታል).. የለም የኔም ባርያ አይደለሽም፡፡ ነፃ ሰው ነሽ፡፡ የማንም ባርያ አገልጋይም አይደለሽ፡፡ ድንገት እንኳ ትዳሩ ባይመችሽ፡ የእሱ አመል ተለውጦ ቢጎረብጥ ቢያሳምምሽ፤ ፈቅደሽ ጥለሽ ለመሄድ ሁሉ ነፃ ነሽ፡፡ ለዚህም የእኔን ፈቃድ እንዳትሺ፡፡ የእናንተ ጋብቻ ተምሳሌትነቱ ትልቅ እንደሆነ ሁሉ፡ ፍቺውም ሰንብቱም ታላቅ ትምህርት ነው የሚሆነው፡፡ አንተም ምንም ብትወዳትም ብታፈቅራትም፤ እሷ ካልተመቻት፤ ነፃ እንድታደርጋት፡፡ ከወደድካት ‹ለኔ ካልሆነች› ብለህ ጭራሽ እንዳትጎዳት፡፡ ትዳር ምንድን ነው?

ጣሴ፡- ሁለት ሰዎች ተስማምተው የሚጫወቱት ጨዋታ ነው፡፡ (ይስቃሉ)

እያሱ፡- ተስማምተዉ!....በሉ ጫጉላው ይድመቅላችሁ፤ ትዳራችሁ ይስመር፡፡ ፍቅራችሁም ከእንግዲህ ገሃድ ነው፡፡ ውህደታችሁን ያኮሰሰ ያዋረደ አይቀጡ ቅጣት ነው የምቀጣው፡፡ ብዙም አይምሸባችሁ፡፡ (ጥላሁንና ሳካምየለሽ እጅ ነስተው አብረው ይወጣሉ)....

እያሱ፡- ጣሴ..አሁን አንተ ከንጉስ ሰለሞን ዘር ነህ ወይስ ከመሀዲ..

ጣሴ፡- ምን ዘር አለኝ እኔ ከአስሩ ተቀይጬ...

እያሱ፡-እና አሁን የኔ ልጅ፤ከአፋሯ የሚወለደዉ አድጎ ቢነግስ አትቃወምም ማለት ነዋ..

ጣሴ፡- ምን ተዳዬ ብዬ...ከሐረርም ከጅማም ቢመጣ ለዚች አገር ችግር መፍትሄ ካመጣ...ምን አለኝ ጣጣ!

እያሱ፡-በል እንግዲያዉ እንጠጣ...(ለጣሴ በዋንጫ ይቀዱለታል)...ሐጅ አብዱላሂም..‹እዉነት ወገኔ ዘመዴ ከሆንክ ልጄን ልዳርልህ› እያሉኝ ነዉ..ምንድነዉ የምላቸዉ?

ጣሴ፡- እንዴት ይባላል...ማግባት ነዋ..ቆንጆ ናት?

እያሱ፡- አዎ ቆንጆ ናት...የከፋዉም አባ ጅፋር...በሚቀጥለዉ ልትጎበኝ ስትመጣ ልጄን እድርሃለሁ ብለዉኛል...

ጣሴ፡- ማግባት ነዋ...ቆንጆ ናት?

እያሱ፡- አዎ በጣም ቆንጆ ናት...ጦናም የደረሰች ልጅ አላቸዉ...ከጠየቁኝ እምቢ አልላቸዉም!

ጣሴ፡- እንዴት እምቢ ይባላል?...እሷም ቆንጆ ናት?

እያሱ፦ አዎ...በጣም ቆንጆ ናት...አገራችን ቆንጆ ናት...ህዝቦቿም ቆንጆ ናቸዉ...

ጣሴ፦ (እየተጎነጨ)...ሁሉንም ማግባት!...ለፌዴራሲዮን!

እያሱ፦ ለፌደራሲዬን?....(ከዉጭ ዉርክብ ይሰማና አባ ማቴዎስ ይገባሉ....ሁለቱንም ያሳልማሉ)....እንዴት ሰነበቱ አባታችን?

ማቴዎስ፦ ክብሩ ይስፋ..እርስዎስ እንዴት ሰነበቱ?

እያሱ፦ ደህና ነኝ...ምነዉ ከመሸ መጡሳ?

ማቴዎስ፦ ብርቱ ጉዳይ ገጥሞን ነዉ።

እያሱ፦ ምንድነዉ ታዲያ እንስማዉ...

ማቴዎስ፦ (ተናደዋል)...የቤተ ክህነት የበላይ ጠባቂ አባት በመሆንዎት...ዛሬ የሚሰራዉን ስራ ዝም ብለዉ አያዩትም። የቱርክ ቆንስላ...ለድሀ መርጃ ማስተማሪያ ብሉ የወሰደዉን ቦታ መስገጃ ሊሰራበት ነዉ ተብሎ ምእመኑ ተቆጥቷል። በነቢያት በቅዱሳት አገር እንዴት ከታቦት ማለፊያችን ላይ መስጊድ ይሰራበታል?...ደሀ መርጃ ቦታ ብሎ እንዴት መስገጃ ያደርገዋል?...ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ያሻዋል!

እያሱ፦ ይሄ አግባብ አይደልም።...ጉዳዩን ለአዛዥ ዳምጤ ነግሬ ከቤተስኪያኑ ፈቀቅ እንዲሉ እና መስገድም ከፈለጉ እንዳሻቸዉ ይሆኑበታል። አጠጋግቶ መስራቱ መጫጫህ ነዉ ለሁለታችሁም።

ማቴዎስ፦ ልጅ እያሱ...መቼም ቱርክ ሲባል መቼም ቱርክ ነዉ! ቱርኮችየሚታመኑ ሰዎች አይደሉም። ቱርክ እና እንሽላሊት ይባላል..

እያሱ፦ ለእኔ ሁሉም አንድ ነዉ። እንግሊዙ ጣልያኑ ቱርኩ...አቅም ቢኖረኝ እርዳታቸዉን ባልሻ፣ በእንጨት አልነካዉም ነበር የነሱን ስጦታ ጉርሻ። ግን አባቴ እስቲ ልጠይቅዎ?...እርስዎ የክርስቲያን መሪ አገርዎ ግብጥ ዝርያዎ የአረብ ነዉ።

ማቴዎስ፦ እሀ..ልክ ነዉ።

እያሱ፦የቱኮችም ቆንስላ እንዳጫወተኝ...ሀይማኖቱ ይለይ እንጂ ዝርያዉ የአረብ ነዉ...

ማቴዎስ፦ ቱርክ ክርስቲያን አረቡን የወጉ አረመኔዎች ናቸዉ።

እያሱ፦ ገባኝ...ክርስቲያን አረብ..ሙስሊም አረብ። በሀይማኖቱ ተለያያችሁ እንጂ እኮ የተቀረዉ አንድ ነበር እኮ...

ማቴዎስ፦ እንዴት የተቀረዉ አንድ ነዉ?...አልገባኝም። አሁን ክርስቲያኑ የባረከዉን እነሱ ይነካሉ?..ሙስሊሙ ቤት ገብተዉ እርስዎ ይበላሉ?...

እያሱ፦( አስበዉ)...ኧ...እሱስ ልክ ነዎት...

ማቴዎስ፦ እስቲ እኔ ልጠይቅዎት?..መቼም ተጠራጠረኝ አይበሉና....የሀይማኖትም ጠባቂ አባትዎትም ስለሆነኩኝም መጠየቅ ማትጋትና ማስተማርም ስለ አለብኝም...

እያሱ፦ ግዴየለም ይጠይቁኝ።

ማቴዎስ፦ በርግጥ በእግዚአብሄር ያምናሉ?

እያሱ፦ በሚገባ!...ይቺ አገር እስካሁን ያለችዉ በእሱ ምህረት ነዉ...የማንኛዉ እግዚአብሄር እንደሆነ አላዉቅም እንጂ..በእሱ መኖርስ ጭራሽ አልጠራጠርም።

ማቴዎስ፦ እንግዲያዉስ ይቺን አገር ለሶስት ሺህ አመታት ጠብቆ ያኖራት የክርስቲያን አምላክ መሆኑን መጠራጠር የለብዎትም።

እያሱ፡- ይሄ የሙስሊሙሳ? አገራችን የጋራ ነች...ለሁለታችንም ባርኮን እንደሆነስ የሰጠን?...የሁለቱም እግዚአብሄር አንድ እንደሆነሳ?

ማቴዎስ፡- ለእሱ መጠሀፉን በትክክል ቢመለከቱ መልስ ያገኛሉ...የእስራኤል አምላክ ሀያልና ስራዉ ረቂቅ ነዉ...

እያሱ፡- የኢትዮጵያን አምላክ ነዉ እኔ የማመልከዉ፡፡

ማቴዎስ፡- እሱ ጥሩ ነዉ፡፡ ያዉ አንድ እኮ ነዉ፡፡

እያሱ፡-እናንተም የሐይማኖት አባቶች እንዳትጣሉብኝ እፈልጋለሁ፡፡ እናንተ ስትጓተቱ ስትጣሉ፤ ማደጋችን ይቆምና ሁሌም ድካማችን እርቀ ሰላም ለማስፈን ብቻ ይሆንና የዉጭ ሀይሎች በዚያ ቀዳዳ ከፋፍለዉ አሽከር ባሪያ ያደርጉናል፡፡ ለአሁን ለቱርክ የተሰተጠዉ መሬት ይመለስና ለእነሱ ራቅ ተደርጎ ሌላ ቦታ ይሰጣቸዋል ..የሀይማኖት ክፉ የለዉም...

ማቴዎስ፡- አሁን ስለመሸ...ይሄንን ትምህርቱን ሰንበት ሥላሴ ሲመጡ በሰፊዉ እንማረዋለን...ይቺን የክርስቲያን ደሴት የሆነች አገር እንዴት መጠበቅ እንዳለብን በምሳሌ እናስረዳለን፡፡ ለአሁኑ እኔም በጊዜ ልግባ እርስዎም ይረፉ...ነገ ጧት ደሞ የቀጨኔን ንግስ ዘንግተዉት እንዳይቀሩ..

እያሱ፡- እሱንማ እንዴት እዘነጋዋለሁ....(ተነስተዉ ይሳለማሉ..ማቴዎስ ቅር እንዳላቸዉ ይወጣሉ...ፋታ)

እያሱ፡- (ከመጠጡ ይጎነጫሉ)...ጣሴ...ደግመህ ጠጣ...

ጣሴ፡- ዛሬስ በቃኝ...

እያሱ፡- ምነዉ ፈራህ እንዴ?

ጣሴ፡- ለምኑ ጌታዬ?

እያሱ፡- አልጠድቅም ብለህ?

ጣሴ፡- እንደሱስ አላሰብኩትም

እያሱ፡- አንተ ከየቱ ነህ?...ምንድነዉ ሀይማኖትህ? ከሁለቱ የትኛዉ ነህ

ጣሴ፡- እኔ ሶስተኛዉን ነዉ የማምነዉ....

እያሱ፡- ሶስተኛም አለ እንዴ?..ማነዉ የሚባለዉ እሱ ደግሞ?

ጣሴ፡- መልካም ማድረግ ይባላል፡፡

እያሱ፡- መልካም ማድረግ?

ጣሴ፡- አዎ መልካም ማድረግ..መልካም ነዉ፡፡ የራስ ያልሆነዉን አለመንካት፤ የሚተርፍ ካለ መስጠት፡፡ ሲቻል ወገንን ማትጋት መርዳት፡፡ ጥሩ እንቅልፍ መተኛት፡፡

እያሱ፡- ጥሩ ሀይማኖት ነዉ፡፡

ጣሴ፡- ሽልማትም ቅጣትም የለዉም፡፡ ሰላም ነዉ፡፡

እያሱ፡- እንግዲያዉ ለሰላም እንፀልይ፡፡

ጣሴ፡- እሺ...(ሁለቱም ይንበረከካሉ)...ሰላም ያዉርድልን!

እያሱ፡- ሰላም ያዉርድልን!

ጣሴ፡- አሜን!

እያሱ፡-አሜን!...(ሲተያዩ መብራት ይጠፋል፡፡)

<u>ትእይንት 3</u>

(መብራት ሲበራ በርካታ መኩዋንንት በችሎቱ ወዲህ ወዲያ ሲሉ ይታያሉ፡፡...ጣሴ ገብቶ እጅ ይነሳል)

ወሰን፡- የት ናቸዉ?..ይመጣሉ ወይስ ምንድነዉ ነገሩ?

ጣሴ፡- ልጅ እያሱ ዛሬም አልመጡም...

መንገሻ፡- ታዲያ ለምንድነዉ የሚላክብን?

ደምሰዉ፡- ትናንትናም ከትናንት በስትያም...‹ድረሱ ትፈለጋላችሁ› እየተባል የሚላክብን ምንድነዉ?

ወሰን፡- መቀለጃ መጫወቻ ነን እኛ?...

መርእድ፡- ደሴን ነዉ? ጣርማ በርን አልፈዉ ዛሬ ማለዳ ይገባሉ ነበር የተባለዉ?

ጣሴ፡- ልጅ እያሱ...ሶማሌ ሚባለዉ አገር ቆይተዉ..

ሁሉም፡- ሱማሌ??

ወሰን፡- ምን ሊደረግ ነዉ ሱማሌ..

ጣሴ፡- በቅኝ ገዢ ጥልያን ላይ ያመጡትን የሶማሌ ሰዎች ለመርዳት..

መንገሻ፡- የራሷ ሲያርባት፤ የሰዉ ታማስላለች አሉ..

ወሰን፡- እና ሱማሌ ተቀምጠዉ ነዉ እኛን እዚህ ‹በቶሎ ድረሱ› የምንባለዉ?

ጣሴ፡- ከሶማሌማ ወጥተዉ ትናንት ሐረርጌ ገብተዋል...

ሁሉም፡- ሐረርጌ?...

ወሰን፡- አይ መዋረድ...አገር በጭንቅ ተይዛ የሚመራት ጠፍቶ ሁሉም ሲንጠራወዝ...

ጣሴ፡- ለሁሉም ነገር ነጋድራስ ሀይለ ጊዮርጊስ አሉኮ...

ወሰን፡- የምን ነጋድራስ...አገር ሲፈርስ ምን ይሰራል አንድ ነጋድራስ?

መንገሻ፡- እንግዲያዉ እዉነት ነዉ...ደጃች ገብረስላሴ ባርያ-ጋብር ሸፍተዋል...ሲሉኝ አላመንኩም ነበር፡፡

ደምሰዉ፡- እኛም የቀረነዉ መተባበር አቃተን፡፡

መንገሻ፡- አይ ደጃች ደምሰዉ...መተባባርማ ቢኖር እንዲህ ባልተዋረድን ነበር፡፡ ደጃች ገብረ ስላሴም ዱር ገብተዉ ባልሸፈቱ ነበር፡፡ ሌላዉ ቢቀር ጉግሳ ወሌ መንገዱን ሲያሳየን መች ተከተልነዉ፡፡ ይሄዉ በቁም እስር አይደል ያለዉ?...ሚስቱን ዘዉዲቱን እዚህ አስቀምጠን...አትመጣትም ሲባል ማን ረዳዉ?....እቴጌም በጠና ታመዋል ነዉ የሚባለዉ፡፡..እንዲያዉ እንዴት ግን መላ ጠፋ?...ይሄ ሁሉ ጀግና እንዴት አንቀላፋ?

ወሰን፡- አዎን አንቀላፋን...አሁን የሚቀረን አንድ መንገድ ነዉ...(ፊታዉራሪ ኃ/ጊዮርጊስ ይገባሉ፡፡ እጅ ይነሳሳሉ)..ፊታዉራሪ..

ኃ/ጊዮርጊስ፡- የታሉ ልጅ እያሱ?

ወሰን፡- መች ተቀምጠዉ ልጅ እያሱ...እኛን እያሉ፤ ገስግሱ ድረሱ፡ እሳቸዉ ዉሎአቸዉ ደጅ ነዉ...ኤድያ ሁሉም ነገር የልጅ ጨዋታ ነዉ የሆነዉ፡፡

መንገሻ፡- ታዲያ ወትሮም ከልጅ ምን ጠብቀዉ?...እኛ ነን ይልቅ ልጅ የሆንነዉ፤ ለልጅ ጨዋታ የወደቅነዉ

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ከአለም ጤና አልተመለሱም?

ወሰን፡- ኧረ እሳቸዉ...ሱማሌ ናቸዉ...የለም ሐረርጌ ናቸዉ፡፡...ከአብዱላሂ መደብ ተቀምጠዉ ነዉ እዚህ የሚጠሩን...ምን ማድረግ እንችላለን?

መርእድ፡- ወይ ንጉስ ሚካኤልን እናማክር?...አባት እና ልጅ ተነጋግረዉ...

ወሰን፡- ኧረ ኤዲያ...ቀልድ ነዉ..የልጆች ጨዋታ፡፡ በጣልያን መርዝ ጢስ ያልተፈታ አገር...እንዲህ በመሪ እጦት ይበታተን?

መንገሻ፡- ፊታዉራሪ...አንድ ነገር ማድረግ ይኖርብናል..አለበለዚያ እንደ ገብረ ስላሴ ሙላችን ጫካ ገብተን መዋጋት ይኖርብናል፡፡

ወሰን፡- ተዋረድን..ለዚች አገር ዳገት ቁልቁለቱን ወርደን ጠላትን እንዳልመከትን፡ ዳር ድምበሯን እንዳላስከበርን..እንዳልደማን እንዳልሞትን፤ የምኒሊክ ሙክት ቀልብ ሰንጋ እየተባልን...ከዚህ በላይ ዉርደት የለም፡፡

መንገሻ፡- ምን እስከሚሆን እንደምንጠብቅ አይገባኝም?

መርእድ፡- በጭንቅ ሰአት በጠሎት መትጋት ነዉ..እሱ መንገዱን እስኪከፍትልን... ልጃችንም ቀልብ ብልሃት እንዲሰጠዉ እና...

ወሰን፤- ሽቅብ አንጋጠን ስንጠብቅ...በመከራ የተገኘዉ አገር እየተከፋፈለ...ከተማ በጠጉረ ልዉጥ እየተወረረ...እንደ ገብርዬ ጫካ ገብተን

ፊታዉራሪ፡- የለም፤ የለም ጫካስ አንገባም..እዚሁ መላ አይጠፋም፡፡

መርእድ፡- አይ ፊታዉራሪ ዲነግዴ...ይንገሩና መላ ካለዉ ዘዴ....

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እምዬ ምኒሊክ...ይሆናል ይበጃል ያለዉ ስርአቱ ተፈቶ፡ ተበትኖ ከላይ ሆኖ ሲያየዉ...እንዴት ያሳዝነዉ?? ( መርእድ እንባቸዉን ያብሳሉ፤ ሌሎችም ያዝናሉ)...እንጃልኝ ምን እንደምለዉ፡፡ የዛች የፍርድ ቀን ዕለት ስንተያይ፡፡ መቼም አይኑንም አላይ፡፡ አንድ መላ ካለበጀንማ፤ ካላወረድን ይህን ማቅ የእፍረት ሽማ፡ ምኑን ኖርነዉ፡፡ የቁም ሞት ነዉ የምንኖረዉ፤ መላ ዘዴዉን ካላወቅነዉ፡፡

መንገሻ፡-እግዜር ይባርክዎ ፊታዉራሪ፡..ሁሌም መላ ዘዴን ለሚፈልጋት አይከብድም ብልሀት..ባለፈዉም እንደ ጀመርኩት...እንዲሁ ተቀምጠን...‹‹ልጆቹ የት ይደርሳሉ›› እያሉ ከማናናቅ...ከሁለቱ የአንዱን ቡድን ይዘን ይሄን ባዶ ቤት ጣራ ማልበስ አለብን፡፡

ኃ/ጊዮርጊስ፡- አይ ቢትወደድ...የልጅ ነገር ሁለት ፍሬ፤ አንዱ ብስል አንዱ ጥሬ.. እንደሚባለዉ...የአባቶቹን ገድል የአገሩን ታሪክና ስርአት የሚያዳብር እንጂ፤ ይሄን የባእድ አገር ጋኔን የሚስብ፤ ለዚች አገር አይበጅም፡፡ አሁን በልጅ እያሱ እና በዚህ ተፈሪ በሚሉት የምናየዉ የልጆች ፋክክር ፍሬ እማይሰጥ፡ የራስን ትቶ የሰዉ የባእድን አገር መቀላወጥ፡፡ እዚህ በዘመናት ተሞክሮ ያስጨበጥናቸዉን ትተዉ፤ ፈረንጅ በፃፈዉ ወረቀት ያዩትን ለመጨበጥ መሞከር የጅል ህሳብ ነዉ፡፡

ወሰን፡- እኔ መቸም የእናንተን ባለዉቅም፡፡ ደጃች ተፈሪ መኮንን..ስርአት የሚያዉቅ፤ ለሁላችንም ፍቅር ከበሬታ አሳንሶ የማያዉቅ...እንኳንስ ለእኛ ልጅ እያሱ ከሀረርጌ አንስተዉ ከፋ ሲሰዱት...ምንም አልከፋዉ፡፡ እሺ ብሎ አራስ ወላድ ሚሽቱን ህጣን

ልጁን ይዞ ነዉ ወጥቶ የሄደዉ።...ታዲያ ይሄን ስርአት የሚያዉቅ ልጅ ማግዙ መልካም ነዉ።

መንገሻ፡- ንጉስ ቢሆን ተፈሪን እመርጣለሁ...ጥሩ ሽግግር ነዉ።

መርእድ፡- እንዴት ነዉ አባባላችሁ??...የምን ሹም ሽር ነዉ ነገራችሁ። ልጅ እያሱ ሳይሞቱ የምን ሽግግር ነዉ...ልጅ እያሱ ተከተማዉ ጠፉ ማለት ታመሙ ሞቱ ነዉ እንዴ?

ኃ/ጊዮርጊስ፡-መታመሙንስ ታመዋል..ደጃች መርእድ...የእሳቸዉ ህመም በአገር ሳይዘምት፤ መዳኒቱ ነዉ የቸገረን። በማን እንተካቸዉ እያልን ነዉ...ደጃች ብሩ፤ ደጃች ኀይሉ፤ ራስ ስዩም፤ ደጃች ወሌ ወይ ራስ ወልደ ጊዮርጊስ አቦዬ.. ወይ ታየ ጉልላት?

መርእድ፡- እንደዚያማ እንዴት ይሆናል? የእምዬ ምኒሊክ ኑዛዜ ቃሉን መሻር። የገባነዉንም ቃል ኪዳን ማፍረስ ይሆንብናል። በዚህ ቢቀርልን በላይ በሰማይ ቤት ያስጠይቃል።..አባት ለልጁ የሰጠዉን ማን ይነጥቃል? እምዬ ምኒሊክስ ምን ይላል?....የጌታዬ የመጨረሻ ቃሉ የማይታጠፍ ነዉ።

ደምሰዉ፡- እምዬ ምኒሊክማ ምን ይላል? አገራቸዉን ከማንም አብልጠዉ ይወዳሉ። እኛንም ‹ሙቱላት ጠብቋት› ብለዉን ነዉ አደራ የሰጡን። ታዲያ ዛሬ የምኒሊክ አገር ሲጠፋ ዝም ብለን እንቀመጣለን??

መርእድ፡- መምከር መገሰጥ ማስተማር፤ የተጣመመን ማስተካከል እንጂ..የሟችን ቃለ ኑዛዜ እንደገና ተመልሰን...

መንገሻ፡- ደጃች መርእድ...ምኒሊክ ቢናዘዙም ወዲያዉ አልሞቱ..እንዲያዉም በተደጋጋሚ ሲጠየቁ...ለእቴጌ ብዙ ሞክረዉ ያልነገሩአቸዉን አንደበታቸዉ ታስሮ እንጂ ደስተኛ አይመስልም ነበር አይነ ዉሀቸዉ።

ወሰን፡-እኔም ስምቻለሁ ቅር መሰኘታቸዉን፤ ከጅምሩ ሁናቴዉን አለመዉደዳቸዉን

መርእድ፡- እኔ እማዉቀዉ በአገር ፊት የተናዘዙትን ነዉ። እንዴት ነዉ ያንን ጥርጥር ዉስጥ የምንከተዉ? ማቆሚያዉ ምን ጋር ይሆናል ይሄን ከጀመርነዉ?

መንገሻ፡- (በቁጣ)...እና አገር ይፍረስ ነዉ!!

መርዕድ፡- እምነታችን በሱባኤ በፀሎት በአማላጅ በምክክር እንጂ...

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ምክርማ ሞከርን..አሁን ማን ይምራን ነዉ ችግራችን...

መርእድ፡- የልጅ እያሱን ደጋፊ ምን ልንለዉ ነዉ? ..ወጣቱ አገሩን የሚወደዉ...ባላገሩ ምኒሊክን የሚወደዉ?..ልጅ እያሱን የምኒሊክ ወራሽ ብሎ የተቀበለዉን ምን ልንለዉ ነዉ?..ኂላ ሌላ ችግር እንዳይመጣ ነዉ፤ ይሄንን የምለዉ። በዛም ላይ...

ወሰን፡- ደጃች መርእድ አርቆ ማሰብዎ ትልቅነትዎትን ያሳያል..ይሁን እንጂ ወጣቱ ያሉት ለሁለት ተከፍሏል።....የምኒሊክም ወዳጅም፤ ልጁ ሐይማኖቱን ለዉጦ ስለመብን እያለ ስለሆነ በአሳቡ ተቸግሯል። አገር ሙላዉን ታምሷል። ሁላችንም እንደ ደጃች ገብረስላሴ አምጠን ዱር ጫካ ከመግባት፤ ወይ ሌላ የሚበጅ ሰዉ ከማምጣት ሌላ መፍትሄ የለም።

መንገሻ፡- ለዚህ ነዉ ደጃች ተፈሪ ይሁንልን የምንለዉ። የሳህለ-ስላሴ ዘር ግንድ አለዉ። የዘመኑንም ትምህርት የተማረ ነዉ

ኃ/ጊዮርጊስ፡- የለም ተፈሪ ልጅ ነዉ።...አንዱን ልጅ በሌላ ልጅ መተካቱ ዋጋም የለዉ። እሚያስፈልገን ቀስ ብሎ የሚያስተዳድረንን ነዉ። የተማረ የሚባለዉ አንድም ግራ

የገባዉ፤ ወይ ጨርሶ የተጣመመ ነዉ።...ህግ ዳኝነት የተማረዉ ፍትህን ይበድላል፤ ህክምና የተማረዉ ጤናን ያቃዉሳል፤ አስተዳደር የተማረዉ ጉቦና አድልኦን ያሰፋል፤ ...ባይማሩ ነበር የሚሻለዉ።

ወሰን፡- ታዲያ ማን ይሆነናል? ደጃች ይልማ..ወይ ደጃች ታዬ ጉልላት?..

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ዘዉዲቱ

ሁሉም፡- ማን አሉ??...ዘዉዲቱ??

መንገሻ፡- ማሚቴ?...ዘዉዲቱ?

ኃ/ጊዮርጊስ፡- አዎ ማሚቴ...ዘዉዲቱ...

ወሰን፡- እና ጉግሳ ወሌ አዲሳባ ሊመጡ?

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እሳቸዉማ ፍርድ ላይ ናቸዉ...ማንም የለም ወዲህ የሚያመጣቸዉ። ....ማሚቴን እናነግሳለን...የተፈሪ ሰዎች እንዳያኮርፉ የዘዉድ አማካሪ እናደርገዋለን። የብዙ መኳንንት የሚስጥር አሳብ ይሄዉ ነዉ።

መርእድ፡- የልጅ እያሱንስ ደጋፊ ምን እናደርገዋለን?

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እሱን በግዝት እንይዘዋለን...የተቀረዉን በተባባሪ ክንዳችን እንደቁሰዋለን!

ወሰን፡- ዘራፍ!...የምኒሊክ አሽከር!...(ከመርእድ በስተቀር ሁሉም ዘራፍ! ይላሉ)

መርእድ፡- (ያማትባሉ)...እኔ መቸም ምንም አልገባኝም...እንዴት ተእምነታችን ተንሸራተን..ቃል እምነት አፍርሰን፤ በወግ ባህላችን የሌለ...የአገርን ሆድ የሚያሻክር፤ መጠፋፋትን መካካድን የሚያስተምር፤ አጉል ክህደት ነገር ነዉ ለልጆቻችን የምናስተምረዉ። የክርስቶስ ትምህርቱ ይህ ነዉ?

ደምሰዉ፡- ደጃች መርእድ...የዚች አገር ወግ ባህል ከረከሰ ቆይቷል...በዚህ በወተሊኮች ቤተ-ክርስቲያን ሳይቀር ‹ልጅ እያሱ ገብተው...ሱሪት ሲጃራቸውን አጭሰውበታል› ብሎ ሲኞር ባናተሎኒ እንኳ አዝኖ... ‹እንዴት በክርስቲያን አገር እንዲህ ይደረጋል ተብሎ፤ ሙላዉ የአለም ክርስቲያን እንዳዘነብን ነው የነገረን። ይሄ መልሶ የውጪ ጠላት የሚያመጣብን ሌላ መዘዝ ነው።

ወሰን፡-የእስላሙን የአረቡን ልብስ ለብሶ የሚዞር። ምግባቸውን የበላ የዚች አገር ንጉስ አይሆንም። እመስጊዳቸው ገብቶ የሰገደ የአገሩን ባህል ያዋረደ፤ ዙፋኑን ትቶ በየእስላም አገሩ የሚዞር ሊገዛት አይገባም...(ዱቤና ዝየራው በትንሹ መሰማት ይጀምራል)... እምቢ ለነጻነቴ!...እምቢ ለእምነቴ!...እምቢ ለሀይማኖቴ!..እምቢኝ!

ደምሰዉ፡- ያገር ወግና ባህል የሚያጠፋ... ክብር ኩታውን ትቶ የሴት ኩታ፤ አርበ-ሰፊ ጥለት የሚያጣፋ። በሚስቱ ላይ ሚስቶች የሚደርብ፤ ይሄ አይደርስም ለክብር። አሳፋሪ ነው የአገር።

መንገሻ፡- እምቢ ለነጻነቴ...እምቢ ለእምነቴ...እምቢ! (ድቤውም ይሰማል)

መርእድ፡- ታዲያ ኑዛዜው...ግዝቱ.. ምህላው...

ደምሰዉ፡- ደጃች መርእድ ኑዛዜ በኑዛዜ...ይሻራል...ግዝትም በግዝት ይነሳል።

መርእድ፡-ጌቶቼ...እስቲ አንድ ጊዜ ብቻ አድምጡኝ...የጨዋ ስርዓት ስረ መሰረቱ፤ ቃል ነው አንድነቱ። እናንተ ይሄን ቃል፤ ይሄን እምነት ከሻራችሁ...የእናንተም ቃል ይሄው ይሆናል፤ ስታረጁ በተራችሁ። ትልቅ የእምነት ማጉደል ተምሳሌት ነው የምናሳልፈው ለልጆቹ። በቃላቸው ተማምነው፤ እንደ አባቶቻችን ጠንተው እንዳይሄዱ መዋሸትን እንዲለምዱ፤ በሆነ ባልሆነው እንዲካካዱ ነው

የምናደርጋቸው፡፡ የአቤቱ እያሱ ችግራቸው፤ ልጅ መሆናቸው፡፡ እየበሰሉ ሲሄዱ.....

ነሲቡ፡- ደጃማች...የበሰበሰውን ነው እርስዎ ይበስላል የሚሉት፡፡ ክርስቲያኑ ጨዋዉ በእኒህ በምናንቴዎች እየተናቁ ቦታቸዉን እየተነጠቁ፤ ምኑን ነው ደጃች መርእድ ይበስላል የሚሉን? እኛም ርስት ጉልበታችንን ተነጥቀን...እንደ እተጌ አሽቀንጥረው እስቲ ወረውሩን እንቀመጥ?

መርእድ፡- እንደሱም አይደል አባባሌ...ወገኖቼ...እንዲህ በስሜት ተናደን የምናደርገው መልካም አይሆንም፡፡ የተናደደ ሰው ‹አይኑን ጨፍኖ አፉን ብቻ ይከፍታል› ይባላል፡፡ ለአፍታ አይናችንን ብንከፍት ስህተት ተመስራት እንገታለን ለማለት እንጂ...

መንገሻ፡- ደጃች መርእድ...ያሁኑ ምክር ሳይሆን ዘለፋ ነዉ...ምንድነዉ አፋችሁን አትክፈቱ አይናችሁን ዝጉ ብሎ ምክር...ምክክር አብቅቷል፡ እንግዲህ ወይ ከእኛ ነዎት ታልሆነም በተቃራኒዉ ነዎት፡፡

መርእድ፡- እንዴት ማለት?

ወሰን፡- ሚናዎትን ይለዩ...ተእኛ ጋር ነዎት ወይስ ከጥላሁን እና ከጆሌዎቹ...

መርእድ፡- እኔ ተአገሬ ጋር ነኝ፡፡ ከማንም አልወገንኩኝ፡፡

ኃ/ጊዮርጊስ፡-...በስንቱ ደም ያቀናነው አገር...ምኒሊክ የቆመለት የቆሰለለት ደብር፤ ያቀናው መንደር በባዕድ እንዳይወረር...ለልጆቻችን እንድናሳልፍ የተረከብናትን አገር...በአለም ፊትም እንዳንዋረድ...ይችን የክርስቲያን አገር የመጠበቅና የማቅናት ከምኒሊክ የተሰጠን አደራ አለብን... ሁሉም መኳንንት የተስማማው...ለአገሩ ከአለው ፍቅር እንጂ ለራሱ ብቻ አስቦ አይደለም...

መርዕድ፡- እንግዲያዉ እንደራሴ አስተዳዳሪዉ ነጋድራስ ይምጡና ምክር ይደረግ፡፡ አሁን እምቢኝ ቢለው...መልዕክት ለልጅ እያሱ በጎን ቢሰዱባቸው...የዚህ ሁሉ ነገር ወሬ ቢናፈስ በወሎ...በደቡብ በምስራቅ በምራብ አገር እርስ በርሱ ቢዋጋ...ህዝብ ቢጨራረስ...መጥፎ ነዉ የሚሆነዉ፡፡

መንገሻ፡- አይ...ሁሉም ነገር መጥፎ ይሆናል ብለው ከፈሩት አንዱንም ሳያከናውኑ ይቀራሉ፡፡...ሁሉም ውጣ ውረድ አለው፡፡ ፍሬ ከህመም ነው፡፡ ፅንስ ያውካል ምጥ ያሳምማል፤ ግና ልጅ ተወልዶ ሲያዩት ደሞ ፍሬዉ ደስ ይላል፡፡ ከዛ ሁሉም ይረሳል፡፡ አሁን እርስዎ ያሳሰበዎት፤ ያዩታል ውጤቱን፤ ሲያልቅ ማማሩን፡፡

ኃ/ጊዮርጊስ፡- ደጃች መእርድ እንግዲህ ይወስኑ...ይሄም ጦርነት ነው የያዝነው፡፡ ምኒሊክን እምነው. አድዋን ተደጋግፈን እንደወጣነው... ዛሬም ያው ፈተና ነው፡፡ የለም...እኔ ምን ተዳዬ አገር ሲፈርስ ሊበተን የጨዋ ደንብና ስርአት ሲዋረድ፤ የምኒሊክ አገር ሲፈርስ እምነትና ማተብ ሲበጠስ፤ የክርስቶስ ቤት ሲዋረድ፤ ባንዲራችን የቱርክ መቀለጃ ይሁን ከሆነ የሚሉት....

መርእድ፡- እንደሱማ ማለት እንዴት ይቻለኛል ፊታውራሪ? ከእናንተ ተወገኖቼ ተነጥዬማ አልቀርም፡፡ ሁኔታው ቢያሳስበኝ፤ ዳግም እንደሽፍታ እዱር ላለመግባት፤ ለሁላችንም የሚበጀውን መላ እንምታ አልኩ እንጂ....

ወሰን፡- እምቢኝ! ዱር እገባለሁ!... እምቢኝ! ለማተቤ እምቢኝ! ለነጣነቴ እምቢኝ!..እምቢኝ!

ደምሰዉ፡- ይሄ ሁሉ መኳንንት ጫካ ከዱር ከገባ...የማን ሰራዊት ነው መጥቶ የሚገጥመው? ይሄ የከተማ ‹ቡሊስ ወቶአደር› ያሉት...ሱሪውን እንኳ በቅጡ የማይታጠቀው?? ይምጣና ይግጠመና!! እምቢኝ! በጃንሜዳ....ባንከበር ሜዳ ....

ባሻው ተራራ እንገጥመዋለን። ዘራፍ...የምኒሊክ አሽከር...ይምጣ የእያሱ ቀሚስ ለባሽ ወታደር!! ጠላ አረቄውን ልፎ ሲዝረበረብ...እለምጠዋለሁ በከዘራ...ለሱ አላበላሽም ጎራዴና ካራ፤ ዘራፍ...(የጦርነት ሽለላ ቀረርቶ ያሰማሉ..ጣሴ አቡነ ማቴዎስን እና እጨጌን ይዞ ይገባል።..ፉከራዉ ይቆማል ሁሉም በክብር መስቀል ይሳለማሉ)

ማቴዎስ፡- ምንድነዉ ነገሩ?...በደህና ነዉ ስብሰባችሁ ፉከራችሁ...ምን ችግር መጣባችሁ?... ብርቱ ጉዳይ ነው ብለው ቢሉኝ ቅዳሴን አስተጓጉለን፤(ሁሉንም በተራ እያሳለሙ)... እጨጌንም ይዤ ነዉ የመጣሁት።...ብርቱ አይደላችሁም ፈታውራሪ??

ጎ/ጊዮርጊስ፡- ክብሩ ይስፋ ለአንድዬ፤ እኛ ደህና ነን... ብቻ አንድ ብርቱ ጉዳይ አገራችንን ስለገጠማት አሱን ስናንሰላስል እረፍት ስለ አጣን የርስዎ የአባታችንን ቡራኬ ለማግኘት እንፈልጋለን...

ማቴዎስ፡- ምንድነው?...ምንድነዉ የተቸገራችሁበት ምክንያቱ?

ጎ/ጊዮርጊስ፡- አባታችን...እንደ ክርስቲያን ወጉ ቁርባኑን ንስሃውን...ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ እንዳስተማረው...ከሁሉም በላይ ፈሪሃ እግዚያብሄር ያደረበትን ሰው እንድንሰማውና እንድንከተለው ያዘናል። እናም አባታችን... ዛሬ ያለ ክርስቲያን አባት እንዳንቀር አምላክ እርስዎን ስለሰጠን እናመሰግነዋለን። ...(ድጋሚ ይሳለማሉ)

ማቴዎስ፡- ምንድነዉ የተቸገራችሁበት ምክንያቱ?

ጎ/ጊዮርጊስ፡- ክርስቲያን ህዝብዎ እያለቀሰ ነዉ። ገንዘቡን ንብረቱን እየተቀማ፤ በተሰኪያኑ እየተናቀ። የክርስቲያኑ ርስተ ጉልት በአረመኔዉና ባልተጠመቀዉ እየተወሰደ.. ክርስቲያን ህዝብዎም ከቦታዉ እየተፈናቀለ እየተሰደደ በመሆኑ ..እርስዎም የዚህ ህዝብ እረኛ የነፍስ ጠባቂ በመሆንዎ፤ ባለብዎት መለኮታዊ አደራ እና አባትነት እንዲረዱን እንማጠናለን።

መንገሻ፡- ልጅ እያሱ ሰልመዋል!...(ሁሉም ያማትባሉ)

ወሰን፡- ከመስጊዱ ገብተዉ ይሰግዳሉ..ያልተባረከዉን ይበላሉ!

ደምሰዉ፡- በሰማንያ ምሽታቸዉ ላይ ደርበዉ፤ ሌሎች ሰባት ምሽቶችን ማግባት ሳያንሳቸዉ...ቤተ መንግስቱ ድረስ ጥሩወርቅ አሊጋዝን ከወሎ አምጥተዉ አስቀምጠዋል!

ወሰን፡- ባለቤታቸዉን..የራስ ኃይሉን ልጅ አሳፍረዉ፤ ወሎን ከፋፍለዉ ለማዋጋት፤ ጎጃም እንዲሸፍት...አገር በእሳት እንዲነድ እንዲቀጣጠል...እምዬ በደም እና በእንባ ያጣበቁትን አገር ለማፍረስ...ማንም ዝም የማይለዉ ግፍ በተለይ በክርስቲያን ህዝብ..እንዴት አስችሎን ዝም እንላለን?...እንደ ገብረ ስላሴ ዱር ጫካ እንገባለን!!

ጎ/ጊዮርጊስ፡- አባታችን መሀላ ግዝታችንን ያንሱልን!..የምኒሊክን ኑዛዜ ለመጠበቅ የገባነዉን ያዉርዱልን!!..(ሁሉም ይንበረከካሉ፤..ማቴዎስ ይሸሻሉ)

ማቴዎስ፡- እንዴት ነዉ የምትሉኝ?..የምኒሊክን ኑዛዜ ትተን፤ ልጅ እያሱን ከዙፋን ልንሽር ነዉ?

ወሰን፡- በዙፋኑማ ሰዉ የለም...በየአገሩ እየዞረ ድቤ የሚመታ፤ አዶ ከብሬ የሚል ሰዉ..ዙፋኑ መች ታየዉ...አባታችን ይቺን የክርስቲያን ደሴት የሆነች አገር ያድኗት!

ማቴዎስ፡- መቸም ይህንን እኔም ሳልሰማ አልቀረሁም..ግና...

ወሰን፡- እንግዲያዉ እርስዎም አገሪቷን ትተዋታል ማለት ነዉ... በቃኝ እኔ እሄዳለሁ! ...ምኒሊክ የሰጠንን አገር የሚጠብቃት ከሌለ..ተዋግተን እናስመልሳታለን...ገብርዬን እከተላለሁ!....(መንገድ ይጀምራሉ)

ኃ/ጊዮርጊስ፡- (መንገድ ይዘጋሉ)..የለም ደም አናፈስም፡፡..አባታችን ይረዱናል፡፡ ስኞር ባንታሎኒን ደጅ ጥዬዉ ነዉ የገባሁት፤ ይግባና ማስረጃዉን ያቅርብልን፡፡ ...(ጣሴ ይወጣል) ..መቸም ባታዩት ነበር ጥሩ፤ ግና እንየዉ ካላችሁ፤ አለም ያየዉን ዉርደታችንን ማየት ከፈለጋችሁ እንዳሻችሁ..(ፓንቶሎኒን ይዞ ይገባል)..ስኞር ባንቶሎኒ...ያን አገር ያፈረበትን ምስል ፎተግራፍ...አምጣዉ እስቲ

ፓንታሎኒ፡- (እጅ ይነሳል..ከቦርሳዉ ብዙ ፎቶዎችን አዉጥቶ ያድላል)...እሺ....

ኃ/ጊዮርጊስ፡- የለም፡፡ ለእኔስ እንዳትሰጠኝ...የስኞር ባንቶሎኒ ዘመዶች ከባቡሩ ስራ ላይ ያሉት ናቸዉ የሰበሰቡት...(ብዙዎች እያዩ ያማትባሉ)

ወሰን፡- እፍረት ነዉ...እስቲ እንዲህ እርቃኑን...ከዚህ ሁላ ሴት ጋር ፍትወተ-ስጋ ነዉ ወይስ ምንድነዉ?

ኃ/ጊዮርጊስ፡- መርከስ ነዉ..የሀይማኖታችን ጠባቂ ንጉስ እንዲህ ሲታይ...

ነሲቡ፡- (ለመርእድ ፎቶ ያቀብላቸዋል)..ይሄንን አዩት?...

መርእድ፡- (ያማትባሉ ፎቶዉን ይወረዉሩታል)...ስብአት ለአብ..ምን ሆኑብን?...ግን ይሄ ዉነት ነዉ?

ፓንቶሎኒ፡- በሚገባ...ፈረንጅ አገር ፊልሙ ሄዶ የታተመ ፎቶ ነዉ፡፡ የእሳቸዉ ፊት ነዉ....ሁሉም የእሱ ነዉ!..../ፎቶዎቹን በየተራ እያዩ እየተደናገጡ ይቀባበላሉ/...

ኃ/ጊዮርጊስ፡- እና ምንም አይደል ብለን የክርስቲያን ህዝብ እያፈረ ቤተክህነቱን ጥሎ ይጥፋ ነዉ የምንለዉ??

ማቴዎስ፡- የኔ አባባሌ..ጉዳዩን ከስሩ ተመልክተን...

እጨጌ፡-( ፎቶዉን ወርዉረዉ መስቀላቸዉን በድንገት አዉጥተዉ)...አቡነ ማቴዎስ አንድ ነገር ያድርጉ..(በመስቀል ደግነዉ ይዞሯቸዋል..ይፋጠጣሉ)....እርስዎ የምኒሊክን ኑዛዜ ለመጠበቅ ያሰሩትን ግዝት ያንሱላቸዉ!...(አቡኑ ይደናገጣሉ፡፡ ተፋጠዉ ይዞራሉ)..እርስዎ ያንሱት...ካላነሱት እኔ አነሳዋለሁ!!

መርእድ፡- ከቀኖናዉ አይወጣም?...ጳጳስ እያለ እጨጌ ግዝት አያወርድም!!

መንገሻ፡- ደጃች መርእድ፤ ምናለ በአባቶቻችን ስራ ባይገቡ!?

መርእድ፡-ወግ ስርአት ደንብ መጠበቅ አለብን!..ስርአት ለማስከበር ስርአተ-አልበኛ መሆን የለብንም፡፡

ኃ/ጊዮርጊስ፡ (ለማቴዎስ)..አባታችን እባክዎ ህዝብዎትን ከጦርነት ከመከራ ያድኑት!

ነሲቡ፡- እኛንም ልጆችዎትን በግዝት ሊያስሩን አይገባም፡፡

ማቴዎስ፡- (ተከበዋል..ግማሹ ተንበርክኳል)...እንግዲያዉ ልጅ እያሱ ከሐረርጌ ሲመለሱ ጠብቀን..ፊት ለፊታቸዉ ተነጋግረን ስናበቃ...

ሁሉም፡- ( ከመርእድ በስተቀር) ምኑን ነዉ የምንነጋገረዉ? እርስዎ አገርዎትን አይወዷትም!!? ../ፋታ..መፋጠጥ ይኖራል)..ምንድነዉ የሚሉን አባታችን??

ፓንታሎኒ፡- (ከቦርሳዉ ተጨማሪ ፎቶ እያወጣ)...ይሄን ተጨማሪ ፎቶ....

ሁሉም፡- ፎቶ ይበቃል!!!.../ፋታ/...ይበቃናል!

እጨጌ፡- አቡነ ማቴዎስ አንድ ይበሉ..../በመስቀላቸዉ ይደግፍሉ፤ ድቤ ዝየራ ይሰማል/...ጊላ ቤተ ክህነት ብትጠፋ እንደ ግራኝ ዘመን ብንቃጠል ኩነኔ ሐጥያቱ የማንም ሳይሆን የእስዎ ነዉ..../ፋታ..ድቤ ዝየራ ሞቅ ይላል)...

ማቴዎስ፡- እንግዲህ ከቆረጣችሁ.../መስቀላቸዉን ያወጣሉ..ሁሉም በዙሪያቸዉ ይንበረከካሉ)..ግን ለአፍታ ብትታገሱ.../ሁሉም ይነሳሉ/...

ሁሉም፡- (ከመርእድ በስተቀር በምሬት)..አባታችን ትእግስታችን አልቋል!!

ማቴዎስ፡- እሺ.../መስቀላቸዉን ሲያነሱ በዙሪያቸዉ ይንበረከካሉ/......በስራችሁት ስራ ፈጣሪ ይቅር ይበላችሁ። እኔም ያሰርኩትን ግዝት አንስቻለሁ! በአሻችሁ መንገድ ሰላም እንድታመጡ ስራችሁን እባርካለሁ...ከስርአታችን ከእምነታችን የወጡትን ልጅ እያሱን ከእንግዲህ የተከተለ፤ ነፍሱ ፍታት አታግኝ!...ይህን ግዝት አገር ይስማዉ...የናንተንም ህብረት እና ጉልበት እሱ ይባርከዉ!!

ሁሉም፡- አሜን!..../ድቤ ዝየራዉ ይደምቃል፤ ደዉል ያስተጋባል፤ ባሉበት ቡራኬዉ እንደቀጠለ መብራት በዝግታ ይጠፋል።

ገቢር 3

አሮጌ መኖሪያ ቤት ነዉ።

(አጭር መብራት ጣሴ ላይ ይበራል።)

ጣሴ፡- አዋጅ አዋጅ...ልጅ እያሱን ንጉስ ብለሽ የተከተልሽ እስከ ሰባት ዘርሽ ጥቁር ዉሻ ዉለጂ!...(ይስቃል)...ልጅ እያሱ በአዋጅ መሻራቸዉን ሲሰሙ፤ ከሐረር ገስግሰዉ ቁልቢ ይገቡና ‹ክርስቲያን ነኝ› ብለዉ እዛ በአሉት ቀሳዉስትን ፊት ቅዱስ መጥሀፉን አስመጥተዉ ቢምሉም ማንም አልሰማቸዉም። ይልቁንስ ሙስሊም ናቸዉ ብሎ የተከተላቸዉን ሁሉ አስከረፈባቸዉ።...(ይስቃል)...ሁለቱንም ነዉ በአንድ ጊዜ ያጡት። ከዚያ በላይ በደንከል በረሃ አድርገዉ ደሴ ሲገቡ ደግሞ አባታቸዉ አዲሳባ ቀድመዉ ሄደዉ ኖሮ ሳይገናኙ ተላለፉ። ቋራ ድረስ ሄደዉ ትግሬ ላይ ተያዙ። አባትና ልጅ ዛሬ ሁለቱም የቁም እስረኞች ናቸዉ። ልጅ እያሱም ከእዚች ቤት ርቀዉ መሄድ አይችሉም። አክስታቸዉ ንግስት ዘዉዲቱ የምትልክላቸዉን ስንቅ እና ጨርቅ ተቀባይ ናቸዉ።..../ሙሉ መብራት ሲበራ..ልጅ እያሱ እጆቻቸዉ እና እግሮቻቸዉ ሰፋ ባለ ሰንሰለት ታስሮ ይገባሉ።/

እያሱ፡- እንዴት ነህ ጣሴ?

ጣሴ፡- ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ..እርስዎስ?

እያሱ፡- ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ!...ምን ይባላል በከተማ በባላገሩ?

ጣሴ፡-ምንም የለም..ዝም ነዉ።

እያሱ፡- ዝምታ መጥፎ ነዉ።..

ጣሴ፡- የአንዱ መጥፎ..ለሌላዉ መልካም ነዉ።

እያሱ፡- ተፈሪ ነገሰ የሚሉት ምኑን ነዉ?.

ጣሴ፡- ተማሪዎቹን እና ዱርዬዎቹን አስተባብረዉ በንግስት ዘዉዲቱ ላይ አመፃ ቀሰቅሰዋል ሲባል ቆይቶ...ንግስት ዘዉዲቱን ከማዉረድ ደጃች ተፈሪን፤ ንጉስ ተፈሪ ተብለዉ ባለ ሙሉ መብት እንደራሴ አርገዋቸዋል።...ዘንድሮ እሳቸዉን የማይደግፍ ‹መሀል-ሰፋሪ› ነህ እየተባለ ይጉላላል።

እያሱ፡- ተማሪዉንና በዘኔዉን ሁሳ ሰላማዊ ሰልፍ ረብሻ እያስነሳ..ኋላ በዙፋኑ ቢቀመጥበት፤ በእሱስ ተራ ደሞ ያዉ ቢሆንስ?...ይሄዉ ያመጣዉ መልሶ ቢወስደዉስ?

ጣሴ፡- ‹ተራማጅ ወገን› የተባለዉ እሳቸዉን ነዉ የሚደግፈዉ..ንግስት ዘዉዲቱ ከቤተ-ክህነት በፆም በጠሎት በመዋላቸዉ የመንግስት ስራዉ እንዳይበደል ሲባል ተፈሪ ዛሬ ሙሉ ስልጣን አላቸዉ።

እያሱ፤- ታዲያ ሰልፍ ረብሻዉን ለምን አያስቆምላትም?

ጣሴ፡- ምን አዉቄ.....ይልቅ እንዳይደነግጡ እንጂ...ፊታዉራሪ ኃብተጊዮርጊስ ዲነግዴ አርፈዋል

እያሱ፡- ዉይ መቼ አረፉ?

ጣሴ፡- ትንሽ ቆዩ...የእሳቸዉንም ጦር..ተፈሪ ወስደዉታል...‹ጠቅል› ተብለዋል በቅጥል ስም...አባ ጠቅል!

እያሱ፡- ‹ጠቅል›?....ጠቅልል...ህም...የሚገርም ነዉ። እና ህዝቡ ዝም ነዉ ያለዉ?

ጣሴ፡- ምን ይላል...መሀል ሰፋሪ እንዳይባል...ያሉትን መልሶ ይደግማል።...አዲስ የተባባሩት መንግስታት የሚባል የአለም ማህበር ይቋቋማል ተብሎም...ኢትዮጵያም ትግባበት እየተባለ ‹ተራማጅ› የሚባሉት ትምህርት እየሰጡ ነዉ።

እያሱ፡- የተባበሩት መንግስታት?..ይሄ እንግሊዝ፤ ፈረንሳይ እና ጣልያን የሚያቋቁሙት ነዉ?

ጣሴ፡- አዎ። ትልቅ የአለም አቀፍ መንግስታት ማህበር ነዉ የሚሆነዉ ተብሏል። አንዱ ትልቅ አገር ድሀዉን አገር ቢበድል አቤት የሚባልበት እና ፍትህ የሚገኝበት ቦታ ነዉ ተብሎ መቼም...

እያሱ፡- አሁን ተኩላዎች የሚያቋቁሙት ማህበር ለበጎች ተቆርቋሪ ሆኖ ፍትህ ሊሰጥ? ..( ይስቃሉ)....የተባበሩት መንግስታት ከሚያስገባን ምናለ እዚህ ያለዉን ጎሳና ብሄር አንድ የሚያረግ ማህበር ቢከፍትልን?

ጣሴ፡- የተባበሩት የአለም ማህበር ፍትሀዊ ዳኝነትና ፍርድ ይገኝበታል ተብሎ ነዉ የሚነገረዉ።

እያሱ፡- እኮ...አሁን የጣልያን ጦር ቢወርረን ሌሎች ይገስጡታል?....የቀልድ ነገር ነዉ። አሁን በጉልበታቸዉ የተያዘዉን አገር ኋላ በማህበርተኛ ስም አዙረዉ ቅኝ ለመግዛት የተወጠነ የተኩላዎች ማህበር ነዉ። ሲፈልጉም የአፍሪካ ማህበር ብለዉ አሁን ለጥቅማቸዉ የከፋፈሉትን፤ የሚያበጣብጥ ድንበር፤ ህጋዊ አድርገዉ..አምሳ ወንበር ያለዉ ማህበር አቋቁመዉ የብጥብጥ ስራቸዉን ለመቀጠልም ይመቻቸዋል።

ጣሴ፡- እንግዲህ አባ ጠቅል...መተዳደሪያችንም የጃፓን ህግ ይሆናል ብለዋል..ያዉ እኒህ የተማሩ ተራማጆቹም...

እያሱ፡- የጃፓን?

ጣሴ፡- አዎ...በስልጣኔ ከሌሎች ጋር እንድንገዝ ከተፈለገ...በአለም ማህበራት ገብተን..

እያሱ፡- እኛን ወደ ስልጣኔ የሚወስድ አንድም ማህበር በእንግሊዝ እና ፈረንሳይ በሌላዉም አይፈጠርም...ቅዠት ነዉ።...(ይንጎራደዳሉ)...ይልቅ በመከባበር የተመሰረተ አዲስ የጋራ ብሄራዊ ማንነት፤ ቶሎ ሳንከበብ ብንፈጥር ነበር ጥሩ...የአገር ዜጋ የምንሆነዉ...አገራችንን ከወራሪ የምናድነዉ...አሁን የእንግሊዙ የጃፓኑ የፈረሳዩን እያሉ ቢጠሩት ሁሉም የፈረንጅ ስርአት አንድ መሆኑን

ቢያዉቁት...እዚሁ አገር መፍትሄዉን ቢፈልጉት ነበር መልካም፡፡ ተኩላ ለበግ አዋላጅ ሆና፤ ተኩላ ለበጎች ማደሪያ መጠለያ ስትሰራ፤ ተኩላ በጎችን ስታስተምር እና የሚበጃቸዉን ስታሰለጥን..በህልሜ ብቻ ነበር ያየሁት...!

ጣሴ፡- /ለተመልካች/...እዚህ ላይ ልክ ነዉ፡፤ አሁን እኮ ‹አለማቀፋዊ ዜግነት› የሚሉት ይቺን አገር ‹አገሬ› እንዳንላት የታቀደ ማደናገሪያ፤ ፕሬዲቶሪ ስልት ነዉ፡፡ ልክ እንደ እርዳታና ብድሩ!

እያሱ፡- እና የፊታዉራሪ ኃብተጊዮርጊስ ጦርም ዝም ብሎ ገባለት?

ጣሴ፡- አዎ...የሳቸዉም...የባልቻ አባ-ነፍሶም ሰራዊታቸዉ ንፋስ ስልክ ላይ እጁን ሰጥቶ ተበትኗል፤ አባ ነፍሶም እንጦጦ ራጉኤል ቁም እስር ላይ ናቸዉ፡፡..አባ ጠቅል የዋዛ አይደሉም፡፡ ሁሉንም ይዘዋል፡፡

እያሱ፡- ዘዉዲቱ ብቻዋን ቀርታለቻ...አባ ጠቅል...አባ ጠቅልል...

ጣሴ፡- ከተማዉ ገበያ በዋለ ቁጥር የአባ ጠቅል ደጋፊዎች ሰልፍ እያደረጉ ‹ጠቅል ይንገስልን! ዘዉዲቱ ትዉረድልን!› እያሉ ነዉ...

እያሱ፡- አባ ጠቅል..ጥሩ መላ ነዉ የፈጠረዉ!...ከዘለቀለት ጥሩ ነዉ!!...(ሁለት የተሸፋፈኑ ሰዎች ይዞ ጥላሁን አሮጌ የገበሬ ልብስ ለብሶ ይገባል፡፡ እጅ ይነሳሉ)

እያሱ፡- ኧረግ....ጥላሁን እንዴት ከረምክ?..እንዴት ናችሁ?

ጥላሁን፡- ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ...(ትከሻ ለትከሻ ይሳሳማሉ)

እያሱ፡- ባለቤትህሳ?

ጥላሁን፡- ደህና ነች፡፡ ቤቴ አልመለስም ከአንተ ጋር እሸፍታለሁ ብላ አብራን ነች፡፡

እያሱ፡- ጣሴ..ደጃች ተፈሪ አገሩን እንደጠቀለለዉ ሲያወጋኝ ነበር፡፡

ጥላሁን፡- ከተማ ያለዉ ተማሪ በዘኔዉ ነዋ...ባላገሩ በተፈሪ እያመጠ ነዉ፡፡ ምኒሊክን የሚወድ የሚያፈቅረዉ ተፈሪን አይንህ ለአፈር እያለዉ ነዉ፡፡ የዉጭ መንግስታትም ለህጋዊ የዙፋን ወራሽ እንጂ አንተን አናዉቅህም እያሉት ነዉ፡፡

እያሱ፡- እንግዲያዉስ አልተመቸዉም...

ጥላሁን፡- ምንም አልተመቸዉም...ይልቅ አሁን አመጣጤ ለሊት ማታ...ከኤርትራ አዉሮፕላን አምጥተዉ..ይዘዉን የሚሄዱ ሰዎች አግኝተናል፡፡

እያሱ፡- ኤርትራ?...ምን እንሰራለን ኤርትራ?

ጥላሁን፡- ከዛ ሆነን ጦር ማሰባሰቢያ ቦታ ይሰጡናል....እዚህም በከተማዉ መነሳትና ማመፅ ለሚፈልገዉ ድምፃችነን እናሰማበታለን፡፡ ድንገት ተፈሪ ቀንቶት ዘዉዲቱን ካነሳት እዚህ መገኘት የለብንም...አደገኛ ነዉ የሚሆነዉ፡፡

እያሱ፡- እና ጣልያን ይሄን ሁላ የሚረዳን...ከእኛ ምን ፈልጎ ነዉ?..አዉሮፕላን ጭምር የሚልክልን?..እንዲሁ ለጥድቅ አይመስለኝም፡፡

ጥላሁን፡- ከተፈሪ ጋር ተኳርፈዋል፡፡ የህዝብም ድጋፍ የለዉም...እኛ ከዚህ ከቁም እስራት ከወጣን ምን አሳሰበን? ያሰቡትን ቢያስቡም ዉጤቱን ነዉ የምናየዉ፡፡ ይልቅ መሰናዳት አለብን...አሁንም ተከልለን ነዉ የመጣነዉ...ለሊት በጨለማ ተመልሰን እንመጣለን.../ተሳስመዉ ጥላሁን እና ሰዎቹ ይወጣሉ/...

ጣሴ፡- አስመራ ከደረሱ ማንም አይነካዎት...

እያሱ፡-( ወዲህ ወዲያ ይላሉ)...አስመራ?...እነሱ ምን ያገኛሉ?..እኔ ነፃ ብወጣ?...ነፍስ

ሳይጠፋ አንዱ ሌላዉን ሳይጎዳ ሳይገድል የሚኖርበት ስርአት ላይኖር ነዉ ማለት ነዉ?... ማቆምያም የለዉ፡፡ ሁላችንም በኪራይ በስጋት ልንኖር ነዉ...ለልጆቻችን ስደት መከራን ልናወርስ ነዉ፡፡

ጣሴ፡- ጠሎት ማድረግ እንዳይረሱ...

እያሱ፡- አደርጋለሁ..የዚችን አገር አምላክ ሁሌም እለምናለሁ...

ጣሴ፡- ደህና ሰላም እንዲያደርግዎት...በሰላም ለአገርዎ ለታቦትዎ እንዲያበቃዎት...

እያሱ፡- ሰላም በአገሬ እንዲያሰፍን እለምናለሁ፡፡ እኔስ ሰዉ ነኝና እሞታለሁ፡፡ በትንታ ልሙት ወይ በበሽታ በጣር..አለዚያም ከሌላ የተወረወረ ጦር ይግደለኝ ባላዉቀዉም፤ ብዙም ከእንግዲህ የምኖር አይመስለኝም፡፡...ጣሴ? ያ ፀሎት ጠፋብኝ..እስቲ እርዳኝ

ጣሴ፡- የትኛዉ?...‹ሰዉ አታድርገኝ› የሚለዉን?

እያሱ፡- አይደለም...‹ሰላም ለተራራዉ..ንፋስ ጠላት ለሚመክተዉ...

ሁለቱም (በመቀባበል እና በጋራ)፡- ለወንዙ ዝናብ ምንጭ ፍሳሹን ሰብስቦ ከእርሻዉ ለሚያመጣዉ፤ ቆሻሻ ለሚጠራርገዉ፡፡ ለፀሐይ ለጨረቃ ለተሰጠን ብርሃን ለሙቀቱ፤ ለሚከልለን ለጨለማዉ ለሌሊቱ፡፡ እህል መዳኒቱን ለሚያበቀለዉ መሬት፤ ለሚያግዙን እንስሳት፤ ለበራሪ ንቦች ሳይቀር፤ ለበኩር አስተማሪዎች፤ለአዛዉንቱም ጭምር፤ እያወቁም ለተሳሳቱት፡፡ ሰላም ለወላድ እናቶች፤ ለልጅ አሳዳጊ አባቶች፤ ለእህት ለወንድሞች፤ ሳይሰስቱ ሁሌም ለሚሰጡት፤ የወደቀን የታመመን ለሚያነሱት፤ የተራበ የታረዘን ለሚረዱት፤ ሽልማት ለማይሹት...ሁሉንም ያበዛህ ፈጣሪ፤ ስምህ ይክበር ምግባርህ ይመስከር፡፡ እንደ ሰሜኖቹ ኩራትን፤ እንደ ደቡቦቹ ጉልበትን፤ እንደ ምዕራቦቹ ትእግስትን፤ እንደ ምስራቆቹ ቸርነትን ስጠኝ እና፤ ሁሌም ኢትዮጵያዊ አድርገኝ፡፡ .../የአዉሮፕላን ድምፅ ይሰማል...ሁለቱም ቀና ብለዉ ያዳምጣሉ/...

እያሱ፡- እዉነት መጡ እንዴ? ዉነት ጣልያን ለእኔ ብሎ አዉሮፕላን ላከ?.../የአዉሮፕላን ድምፁ እየቀረበ ይመጣል፡፡

ጣሴ፡- መጡ ማለት ነዉ?...(እያሱ ቀስ እያሉ ይወጣሉ..ፋታ...ያዳምጣል/...አዎሮፕላኑ ያለ ቦታዉ አረፈ መሰለኝ??.../የአዉሮፕላኑ ድምፅ ያዳምጣል/...ቆይ ቆይ ይሄ ቅርብ ይመስላል፡፡ የለም ማረፊያ አላገኘም፡፡../ያዳምጣል/...እዚህ ግድም አላረፈም...ይልቅ ነገር ተበላሸ አሁን፡፡ አይይ....የንጉስ ተፈሪ ሰዎች ጉዳዩን ከደረሱበት ..ያሳዝናል፡፡ የደም እዳ ሊቀጥል ይመስላል....የልጅ እያሱም ገመድ አጠረች.../እያሱ ተመልሰዉ ሲገቡ ሰንሰለታቸዉ ጠቦ ተጎሳቁለዉ በግድ እየተራመዱ ይገባሉ፡፡/...

እያሱ፡- እንዴት ሰነበትክ ጣሴ?

ጣሴ፡- ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ..እርስዎስ እንዴት ሰነበቱ?

እያሱ፡- ክብሩ ይስፋ ለፈጣሪ...ደህና ነኝ...አየህ ችግርን ካላየሸዉ...ነፃነት የሚሉትን ጭራሽ ማወቅ አይቻልም፡፡...(ፈገግታ)..የሚገርም ነዉ፡፡...ለመሆኑ በከተማዉ ምን ይወራል?..ንግስት ዘዉዲቱ መሞቷን ሰማሁ፡፡

ጣሴ፡- አዎ አረፉ፤ ጉግሳ ወሌ በጦር ተወግተዉ ከወደቁ በኋላ ብዙም አልቆዩ...ንጉስ ተፈሪም...‹ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ› ተብለዉ ንጉሰ ነገስታት ሆነዋል፡፡

እያሱ፡- ‹ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ›? ጥሩ ስም ነዉ የመረጠዉ፡፡ ዳግማዊ፤ ሳልሳዊ ኃይለሥላሴ የሚሆን ከተገኘ እና እሱንም እንደኔ እስር ቤት የሚከተዉ፤ በር በላዩ

ዘግቶ የሚቆልፍበት ካልመጣበት ጥሩ ነዉ። ለነገሩ ሽቅብ አጉነህ የወረወርከዉ ድንጋይ ይዘገያል እንጂ ተመልሶ መምጣቱ አይቀርም ነዉ የሚባለዉ።

ጣሴ፡- ባላገሩ አሁንም እንዳመጠ ነዉ...አገር ስልጣን አልረጋም።...የተማሩትም ተፈሪን ያልተከተለ ‹መሀል-ሰፋሪ እና አድሃሪ፣ ኋላ ቀር› እየተባለ ‹የፖለቲካ ሳይንስ› የሚባለዉ ትምህርት ለሙላዉ ሰዉ እየተሰጠ ነዉ።

እያሱ፡-‹የፖለቲካ ሳይንስ›?..እንዴት?..ሁለቱም ለየቅል መስለዉኝ?...ፖለቲካ የአንድ ዘመን መተዳደሪያ መርህ ከመሆን አልፎ፣ ‹ሳይንስ ነዉ› ከተባለማ...አምልኮ ነዉ የሚሆነዉ...ጭራሽ ሁለቱ አብረዉ አይሄዱም!

ጣሴ፡-ምን አዉቄ?.../ለተመልካች/...ልክ ናቸዉ፣ ከልት ነዉ።...አለምን የሚያፈርሰዉ ይሄዉ ቅዠት ነዉ።

እያሱ፡- አይኑን ጨፍኖ እንደ አዶ ከበሬ..ከአታሞዉ እኩል እያጨበጨቡ መናጥ ነዉ። ...ማታ የበሉት ጎመን ጥርስ ላይ ተለጥፎ አድሮ ከሩቅ እየታየ...‹አይ ፈገግታዉ› እያሉ መዝፈን ነዉ።

ጣሴ፡- ማን ደፍሮ ይናገራል?...አይንህን እንዴት ብትገልጥ ነዉ ይሄንን ጉድፍ ያየኸዉ? እንዳይባል፣ ጥርሱ እየዛገ በሰብሶ እስቲፈርስ ማንም አይነግረዉ...

እያሱ፡- አይ ተፈሪ፣...እንግዲያዉስ ወራሽም አይኖረዉ...

ጣሴ፡- እንደዛ ይሆናል ብለዉ ነዉ?...እንጃ.../ለተመልካች/...ልክ ናቸዉ...ንጉሱ ብራዚል በሚባል አገር፣ የራት ግብዣ ሊበሉ በተቀመጡበት፣ የገንዛ ልጃቸዉ ፣አልጋ ወራሹ፣ መፈንቅለ መንግስት አርገዉ ..../በሹክታ/....ኋላ ቦሌ አዉሮፕላን ማረፊያ ትልቅ ድንጋይ በትከሻቸዉ ተሸክመዉ ነዉ፣ ይቅርታ አባታቸዉን የጠየቁት...ሌላ ጊዜ ነዉ እሱን የምነግራችሁ።

እየሱ፡- መነንስ እንዴት ሆና ይሆን?

ጣሴ፡- አሁን እቴጌ መነን ተብለዉ፣ ስርአተ-ንግሱ ላይ መቼም...

እያሱ፡-እቴጌ መነን?...መነን..እቴጌ መነን አስፋዉ...ጥሩ ነች።..ዘመዴ ነች...የቅርብ ዘመድ...አዎ የቅርብ ነዉ የሚባለዉ...የእህቴ ልጅ እኮ ነች...ያዉ ዘመዴ ነች። ...አጎት ልትለኝ ትችላለህ.../ይስቃሉ/...

ጣሴ፡...ሰሞኑን ደሞ ጣልያን በአዉሮፕላን ወረቀት እየበተነ ህዝቡን እያነሳሳ ነዉ...

እያሱ፡- እያነሳሳ??...ምን ሁኑ ነዉ የሚለዉ?

ጣሴ፡- ህጋዊ አልጋ ወራሹን፣ እርስዎን ልጅ እያሱን መልሰን እናነግሳለን...ብለዉ ማይጨዉ ድረሰ...

እያሱ፡- (ወዲህ ወዲያ ማለታቸዉን ያቆማሉ)..ምን???...እነኚህ ሰዎች ለምን አልሞተም አልተገደልም ብለዉ ነዉ የኔን ስም አሁንም የሚያነሱት?....ከዚህ ያነሰ የእጅ እግር ሰንሰለት የለም። የሚቀጥለዉ አንገቴ ላይ የሚገባ ገመድ ነዉ። .../ይስቃሉ/... ጣልያን አታለለን!!....ምኑን ነዉ ነፃ የሚያወጡኝ?...ተፈሪ ፈርቶ ስልጣኔን ይቀማኛል ብሎ እንዲገድለኝና፣ እሱንም ኋላ ወንጀለኛ አድርገዉ ይቺን አገር ያለ መሪ እንድትበታተን ለማድረግ ካልሆነ በስተቀር፣ እኔ ከዚህ ብወጣ የምሰጣቸዉ ብጣሽ መሬት የለም። እነሱም ያዉቁታል ይሄን../ሳቅ/....ጣልያን በጦር ያቃተዉን በብልሀት አገኘን...ከእንግዲህ መረጋጋት አይመጣም...ያሳዝናል።

ጣሴ፡- ‹ወተሁ ሽገኔ ሉወምደ›..ይላል የመርካቶዉ ሰዉ...

እያሱ፡- ‹ወተሁ ሽገኔ ሉወምደ›?...ምንድን ማለት ነበር ጣሴ?

ጣሴ፡- ‹ወተሁ ሸገኔ ሉወምደ›? ማለትማ በመርካቶ ቋንቋ...‹ወገኔ ተሸወደ ሁሉም› ማለት ነዉ፡፡

እያሱ፡- ልክ ናቸዉ....ሁላችንም ጠፋን...ድንቅ አነጋገር፡፡

ጣሴ፡- አዎን...ንጉስ ነገስቱም መቼም በጣም ተበሳጭተዋል...ከማይጨዉ መልስ ‹የተፈሪ ጀሌ እያለ›፤ ባላገሩ ከጣልያን የተረፈዉን ጦር ብዙዉን ገደለባቸዉ፡፡

እያሱ፡- ይሄዋ..አሸነፉን፡፡ እርስ በእርስ አጣሉን፡፡ ያለመተማመን ዘር ነዉ አሁን የዘራነዉ፡፡ ...ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ፡፡..ያሳዝናል፡፡

ጣሴ፡- አዎ...ያሳዝናል፡፡...አሁን ደሞ ሰሞኑን የተባበሩት መንግስታት ሄደዉ አቤት ሲሉ ነዉ...

እያሱ፡- እኮ እነሱዉ ወራሪዎቹ ያቋቋሙት ማህበር??...ለተፈሪ ሊፈርድለት??..(ሁለቱም ከት ብለዉ ይስቃሉ)...

ጣሴ፡- እኮ ጥልያንን ሊገስጡት?!.. /ይስቃሉ)...

እያሱ፡- ተኩላዎች...ለበጎች ደህንነት ጤና ሰላምና መረጋጋት ያመጣሉ ብሎ መጠበቅ ጭራሽ ጅልነት ነዉ፡፡...ይልቅ..እዚህ በአገሩ ያለዉን የጎሳ ችግር መፍረትሄ ሰጥቶ ሲያበቃ ከአፍሪካ ወንድሞቻችን ጋር ብናብር ነበር ጥሩ፡፡

ጣሴ፡- ቢሆን ማ ነበር...

እያሱ፡- ...አሁንስ ፈራሁኝ...ለምን እንደሆን እንጃ እንጂ...ተሰምቶኝ የማያዉቅ አይነት ፍርሀት ነዉ የሚሰማኝ...

ጣሴ፡- እኔም ፈርቻለሁ እሱስ...

እያሱ፡- እንግዲያዉ ጣሴ ለምን አንፀልይም?

ጣሴ፡-.የትኛዉን?..‹ወንዝ ዳር አፈሩ› የሚለዉን?


እያሱ፡- የለም ..‹ሰዉ ነኝ እና ሰዉ አታድርገኝ› የሚለዉን

ሁለቱም፡- (ይንበረከካሉ)....አባቴ የኢትዮጵያ አምላክ፤ ምግባርህ ይመስክ፤ እንደ ሰዉ አታዉለኝ፡ ከማይጠግብ ስስት ከልለኝ፤ አይን በረከቱን ስጠኝ፤ ጎረቤቴ ያለዉን ሳይሆን፤ እኔ ያለኝን አሳየኝ፡፡ ስራ ጥረቴን ባርክልኝ፤መታደሌን መክበሬን አትሸሽገኝ፡፡ ከቁንጣን ከቃር ሰዉረኝ፡፡ መስጠት በረከቱን ደግነቱን ስጠኝ፡፡ ራሴን እንዳስተምር እንድገስፅ ብልህነት አትንፈገኝ፡፡ በዚህ ቅዠት ከሞላበት አለም፤ የቅዠታቸዉ ተመልካች እንጂ፤ ተሳታፊ አታድርገኝ፡፡ አቤቱ አባቴ..ሰዉ ነዉ ብለህ፤ እባክህ ሰዉ አታድርገኝ፡፡

እያሱ፡- (ፀሎቱን አቋርጠዉ ቀና ብለዉ)...ግና እዉነት አሁን እንግሊዝ ወይ ፈረንሳይ ለተፈሪ ሊፈርድልት?...(ሁለቱም ይስቃሉ)...እኮ ልክ ነህ ሊሉት?... (ይስቃሉ) ..እህል ጉርሱን ሊሰጡት?...እንግዲህ ፈረንጆቹ በሰማይ በሚበር ነገር ተሩቅ ሁነዉ መልካም ነገር ሲጥሉለት?...(ሁለቱም በእምብርክክ መሬቱን እየመቱ ሲሳሳቁ በጸሎቱ ወቅት በትንሹ ይሰማ የነበረዉ ድቤ ዝየራ፤ አዛን፤ ደዉል፤ የርቀት ቅዳሴ እየሞቀ ይሄዳል...ሁለት የታጠቁ ሰዎች ገብተዉ የሚስቁትን ልጅ እያሱን እየጎተቱ ይዘዋቸዉ ይወጣሉ፡፡ ጣሴ መሀል ስቴጅ ይወድቃል፡፡ ፀጥታ፡፡ መብራት ይጠፋል፡፡)

-መጋረጃ ይጣላል-


በጌታቸዉ ታረቀኝ
በቅርቡ
የሚወጣ
አባ ጠቅል




በአማዞን ገበያ ይገኛል።